ከአደጋው በኋላ አምስት ዓመት ያህል ቆይቶ፤ እኔና ዲክ ሁለታችንም ፓት ሮበርትሰንስ 700 ክለብ በሚል የቴሌቭዥን ፕሮግራም ቀርበን ነበር፡፡ የፊልም አንሺ ቡድን ወደ ቴክሳስ መጥቶ የነበረውን ክስተት እንደገና እንድንደግመው በማድረግ ፊልሙን አንስቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ ጠይቀውኛል፡፡ የ700 ክለብ ከዚያ በኋላ በነበሩ ሁለት ዓመታት ውስጥ ያንን ታሪክ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ በአየር ላይ ለቆታል፡፡

በሕይወት እጅግ አስደናቂ ከሆኑት እንቆቅልሾች አንዱ ተከናወነ፤ በ2001 ዲክ በልብ ድካም በሽታ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡ ሞቱን በሰማሁ ጊዜ እጅግ ማዘኔን እናዝዛለሁ፤ ነገር ግን አሁን በክብር ስላለ ደስተኛ ነኝ፡፡ ዲክ የእኔን ሕይወት አዳነ፤ እናም እግዚአብሔር እርሱን አስቀድሞ ወደ መንግስተ ሰማይ ወሰደው፡፡ ወደ መንግስተ ሰማይ የሚያደርገውን ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የእኔን ምስክርነት በመስማቱ ተደስቶ ነበር፡፡

ከአደጋው በኋላ አንድ ዓመት በላይ ቆይቶ ከአኒታ ጋር ያንን ጭውውት ካደረግን ወዲህ፤ እግዚአብሔር ወደዚህ ምድር የመለሰኝ ለዐላማ መሆኑ ከመቼውም ይልቅ እያሳመነኝ መጣ፡፡ መልአኩ የእኔን እጅ መያዙ፤ ምንም እንኳን ነገሮች ከባድ እየሆኑ ቢሄዱም እንደማይተወኝና እንደሚደግፈኝ እንዳውቅ የተጠቀመበት መንገድ ነበር፡፡

ምናልባትም ያ እጅ በእያንዳንዱ ቀን እንደያዘኝ አይታወቀኝ ይሆናል፤ ነገር ግን ከእኔ ጋር እንዳለ አውቃለሁ፡፡



# 14 አዲሱ ሕይወት

"እኔ ጤናህን እመልስልሃለሁ፤ ቁስልህንም እፈውሳለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር ማንም የማይሻት፣ የተጣለች ጽዮን ብለው ጠርተውሻልና"

ኤር 30፥17

ፈጽሞ ልናገግም የማንችልባቸው አንዳንድ ነገሮች ወደ እኛ ይመጣሉ፤ እናም የተለመደውን የሕይወት ምልልስ ያናውጣሉ፡፡ እንግዲህ ሕይወት እንዲህ ናት፡፡

የሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ የቀደሙ ነገሮችን መልሶ የመገንባትና የተውናቸውን ነገሮች ከጣልንበት ሥፍራ እንደገና የመሰብሰብ ዝንባሌ አለው፡፡ አስተዋዮች ብንሆን ኖሮ ነገሮችን ቀድሞ ወደነበሩበት ሥፍራ ለመመለስ ጥረታችንን አንቀጥልም (ብንሞክርም አይሳካም)፡፡ ከዚያ ይልቅ የቀደመውን የተለመደ ነገር እየረሳን አዲሱን ሕይወት መቀበል ይገባናል፡፡

ጤነኛ የነበርኩበትንና አንዳችም አካላዊ ችግር ባልነበረብኝ ጊዜ የነበረኝን ሁኔታዬን ብዙ ጊዜ በማሰብ እጅግ ብዙ ጊዜ አጥፍቻለሁ፡፡ በአዕምሮዬም፤ ሕይወት ምን መምሰል እንደነበረባት እንደገና እቀርጻለሁ፤ እውነታው ግን ከዚያ በኋላ ሕይወት እንደቀደመው እንደማይቀጥል አውቅ ነበር፡፡ አካላዊ ጉድለቶቼን እንደ አዲሱ ሕይወቴ

አንድ አካል አድርጌ መቀበልና ሁኔታዎችንም ከዚሁ አንጻር ማመቻቸት ነበረብኝ::

ልጅ በነበርኩበት ጊዜ በአያቶቼ ሳሎን ቤት በነበረ ቡና አይነት ምንጣፍ ላይ ከመሬት ተቀምጬ እነርሱ ስላሣለፏቸው መልካም ጊዜያቶች ሲያወሩ አዳምጥ ነበር:: በርካታ ታሪኮችን ካዳመጥኩ በኋላ እንዲህ ስል አሰብኩ፤ እነኝህ የሚያወሩላቸው ዓመታት መልካም ዓመታት አልነበሩም፤ ቢያንስ ቢያንስ በትዝታቸው ውስጥ የሚያወሩት ነገር መልካም አይደለም:: ምናልባትም ለእነርሱ በእውነትም መልካም ዓመታት ሆነውላቸው ይሆናል ወይም ደግሞ ምናልባት በጊዜያቸው የነበሩትን አሉታዊ ገጽታዎች እረስተዋቸው ይሆናል:: በሕይወታችን ወደ ኋላ ተመልሰን ወደ አንዳንድ ስፍራዎች ነገሮች ቀላል ወደነበሩበት ሁኔታ፤ ጤናማ ወይም ደስተኞች ወደነበርንበት ሁኔታ መመለስ እንፈልጋለን:: ልናደርገው አንችልም፣ ይሁን እንጂ አሁንም አንድ ጊዜ ሁኔታዎች እንዴት ጥሩ እንደነበሩ ማለማችንን እንቀጥላለን::

በሃያዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ሳለሁ፤ ዝማሬዎችን በምዘምርበት ጊዜ የቆዩ ግን ታዋቂ የነበሩ ዝማሬዎችን መዘመር እናዘወትር ነበር:: እነኛን ዝማሬዎች እንዲዘመሩ የሚመርጡ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ መዝሙሮቹ አሁን ካሉት ዝማሬዎች ይልቅ የተሻሉ እንደሆኑ አስተያየት ይሰጣሉ:: እውነታው ግን በቀደሙት ዓመታትም ቢሆን ጥሩም መጥፎም ዝማሬዎች ይዘመሩ ነበር፤ ይሁን እንጂ መጥፎዎቹ ዝማሬዎች አሁን እንደሚሆነው ሁሉ ከሰዎች አዕምሮ ውስጥ ፈጥነው ይደመሰሳሉ:: ስኬት ያልነበራቸውን ዝማሬዎች እንድንዘምር ማንም ጠይቆንም አያውቅም:: የቀደመውን ዘመን ተደናቂ የሚያደርጉት ጥሩዎቹ ዝማሬዎች ናቸው:: በዚህም የቀደመው ዘመን



ዝማሬዎች ሁሉ ጥሩ እንደነበሩ ይገመታል:: ተጨባጭ ሁኔታዎችን ካየን - ከሠላሣ ወይም ከሃምሳ ዓመታት በፊትም ጥሩ ያልሆኑ ዝማሬዎች ነበሩ:: እንዲያውም አብዛኞቹ ጥሩ ያልሆኑ ናቸው:: በሕይወት ልምምዶችም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: አሉታዊ ገጽታ የነበራቸውን ሁኔታዎች የመርሣትና አስደሣች ሁኔታዎችን ብቻ የማስላሰል አዝማሚያ እንወስዳለን:: እውነታው ግን - እየመረጥን የምናስታውስና - እየመረጥንም የምንዘነጋ መሆኑ ነው::

ይህ ዐይነቱ አመለካከት አንድ ጊዜ ወደ ውስጤ ከገባ በኋላ፤ ከኋላዬ አልፌ የመጣሁትን እንደገና መያዝ እንደማልችል ወሰንኩ:: ምንም ያህል በአዕምሮዬ እየደጋገምኩ ብሰለውም ያኛው የሕይወት ገጽታ ላይመለስ አልፎ ሄዷል፤ እንደገና ሙሉ ጤነኛ ወይም ጠንካራ ልሆን አልችልም:: ለእኔ የቀረልኝ ብቸኛው ነገር የአዲሱን ሕይወቴን አዲስ አቅጣጫ መፈለግ ነው::

“አዎን”፤ አልኩኝ ለራሴ፤ እንደገና ላደርጋቸው ፈጽሞ የማልችላቸው ነገሮች አሉ:: እንዲህ መሆኑን አልወደውም እንዲያውም እጠላዋለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ይህ ነገሮች ያሉበትን ሁኔታ አይለውጠውም:: ፈጥኜ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ሰላም ስፈጥርና ያለሁበትን ሁኔታ ስቀበል፤ ፈጥኜ ሰላም ወደምላበት ሕይወት እገባለሁ፤ ያለሁበትንም አዲስ ሕይወት በደስታ ማጣጣም እጀምራለሁ::

እየተናገርኩ ያለሁትን ነገር በምሳሌ ልግለጸው::

እ.ኤ.አ. በ2000 መግቢያ ላይ፤ የተወሰኑ የኮሌጅ ተማሪዎችን በበረዶ ላይ እየተንሸራተቱ እንዲዝናኑ ለማድረግ ከሀውስተን ወደ ኮሎራዶ ይዣቸው መጥቼ ነበር:: በበረዶ ላይ መንሸራተት በጣም ከምወዳቸው ነገሮች አንዱ ነበር:: ከእነርሱ ጋር መሳተፍ ባለመቻሌ

ከተራራው በታች ባለች አንዲት ክፍል ውስጥ ተቀምጬ በመስኮቱ አሻግሬ ቁልቁል እየተምዘገዘጉ ሲወርዱ እመለከታቸው ነበር። እናም ድንገት ውስጤ በንዴት ተሞላና፤ "ትልቅ ስህተት ነው የሠራሁት፤ ወደዚህ ስፍራ አብሬአቸው መምጣት አልነበረብኝም" አልኩ። እነርሱ በበረዶው ላይ ሲንሸራተቱ ደስተኛ የሆንኩትን ያህል፤ እኔ ልንሸራተት ባለመቻሌ ደግሞ እጅግ ነበር ያዘንኩት።

ከዚያ በኋላ ላደርጋቸው የማልችላቸውን በሽህ የሚቆጠሩ ነገሮች ማሰብ ጀመርኩ። በቤተክርስቲያኔ ዋነኛው መጋቢ በነበርኩበት ጊዜ፤ የእያንዳንዱ ማለዳ አገልግሎት ከተጠናቀቀ በኋላ፤ በእድሜ ከፍ ያሉት አባላት ከመግቢያው በር ላይ "በስብከትህ ደስተኞች ነበርን፤" "ታላቅ አገልግሎት ነበር" እያሉ ሰላምታ ሰጥተውኝ ይወጡ ነበር።

ልጆች ግን እንዲህ አይደሉም፤ ባህርያቸው የተለየ ነው። በእጃቸው ሲለው ቀለም የቀቡትን ሥዕል ይዘው ወደ እኔ እየሮጡ ይመጡ ነበር። ከአደጋው በፊት ህፃናቱ በዙሪያዬ ሲሰበሰቡ እደሰት ነበር፤ በጉልበቴ ተንበርክኬም ከእነርሱ ጋር አወራለሁ። አሁን ከአካል ጉዳቴ ካገገምኩ በኋላ እንደቀድሞው በርከክ ብዬ ደስታ የተሞላ ብሩህ ፊታቸውን እየተመለከትኩ፤ "በጣም አመሰግናለሁ፤ ይህንን ስዕል በእውነት ወድጄዋለሁ። በጣም ምርጥ ነው" ልላቸው አልችልም።

ከአደጋው በኋላ፤ ላደርግ የምችለው የተሻለ ነገር ወደ ፊት ጎንበስ ብዬ ከእነርሱ ጋር ማውራት ነው። ምናልባት ይህ እምብዛም ትልቅ ነገር ላይመስል ይችላል፤ ለእኔ ግን ትልቅ ነገር ነው። ከዚህ በኋላ መንበርከክ ፈጽሞ አልችልም። ልጅ በነበርኩበት ዘመን አደርገው



እንደነበር ሁሉ አሁን መንበርከክ አልችልም፤ ምክንያቱም የእግሮቼ ሁኔታ ያንን እንዳደርግ አይፈቅድልኝም።

ሌላ ምሳሌ ደግሞ ልስጣችሁ፤ ቀላል ምግቦችን ለመመገብ በመኪናዬ ውስጥ ሆኜ በምግብ ቤቱ አካባቢ ስስተናገድ፤ መልስ ለመቀበል ግራ እጄን መዘርጋት አልችልም። ማድረግ የምችለው የተሻለው ነገር ቀኝ እጄን በሰውነቴ ዙሪያ አሳልፌ መቀበል ነው። እንግዳ ነገር ነው የሚሆንባቸው በፊታቸው፤ ላይ ግራ መጋባት እያለሁ፤ ይሁን እንጂ ማድረግ የምችለው በቃ ያንን ነው።

ምንም እንኳን እነዚህ ምሳሌዎች በተለይ ከእንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ቢሆንም ሁልጊዜም የሚያስታውሱኝ ነገር አለ። አንዳንድ ጊዜ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን በቀላሉ እናደርጋቸው የነበሩ ነገሮች እስከ ፍጻሜው ከእኛ ይወሰዳሉ፤ ነገሩ የሚሆነው ድንገት ነው፤ እናም ለዘላለም እንለወጣለን።

ሆስፒታል በቆየሁበት ረዥም ጊዜ፤ አንድ ሰው የአይኑን ብርሃን ስላጣ ስለ አንድ ወጣት የሚያትት መጽሔት አምጥቶ ሰጠኝ። እጅግ መራራ በሆነና ድብርት በሞላበት ሁኔታ ውስጥ አለፈ። ይህ ሰው በጻፈው ጽሁፍ እንደገለጸው፤ ለእርሱ በጣም ይጨነቅለት የነበረ ጓደኛው፤ ከዚህ ዐይነት ሁኔታህ ፈጥነህ መውጣት ይኖርብሃል" በማለት እውነቱን በነገረው ጊዜ ስሜቱ እጅግ ተጎዳ።

መጽሔቱን ከማንበብ ቆም አደረኩና፤ "እውነት ነው፤ ከአደጋው በኋላ እኔም ይሰማኝ የነበረው እንዲሁ ነበር" አልኩ። ጽሑፉ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤ ይሁን እንጂ የአይነ ስውሩ ጓደኛ ተግባራዊ የሆኑ

መመሪያዎችን ሊሰጠው ስለፈለገ፤ አሁንም ማድረግ የምትችላቸውን ነገሮች ዝርዝር ሁሉ እንድትገልጽልኝ እፈልጋለሁ አለው::

"እነዚህ የምትላቸው ዝርዝሮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?" ሲል የተቆጣው አይነስውር ጠየቀ::

"በቃ ማድረግ የምትችላቸውን ነገሮች ለእኔ ንገረኝ:: መጻፍ አያስፈልግህም፤ ይሁን እንጂ በቴፕሪከርደሩ ላይ ዝርዝሩን መቅዳት ትችላለህ:: አሁንም ማድረግ የምትችላቸውን ነገሮች ሁሉ መዘርዘርህን አትርሣ:: እኔ እየተናገርኩ ያለሁት ቀላል ስለሆኑ ነገሮች ነው፤ አሁንም አበቦችን ማሽተት እችላለሁ የሚሉ ዐይነቶችን:: እስከቻልከው ድረስ ዝርዝሩን አርዝመው:: በጨረስክ ጊዜ ዝርዝሮቹን ማድመጥ እፈልጋለሁ::"

አይነ ስውሩ በመጨረሻው በነገሩ በመስማማት ዝርዝሮቹን ተናገረ:: ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ አይታወቅም፤ ነገር ግን ጓደኛው በተመለሰ ጊዜ አይነስውሩ ወጣት ፈገግ ብሏል፤ ውስጡም ሰላምን ተሞልቷል::

"ባለፈው ጊዜ ካየሁህ ይልቅ አሁን በተረጋጋ የአዕምሮ ሰላም ውስጥ ያለህ ትመስላለህ" አለ ጓደኛው::

"ትክክል ነው፤ በእርግጥም እንደዚያ ነኝ፤ ምክንያቱም የተሰጠኝን ዝርዝር እየሠራሁ ነበር::"

"በዝርዝርህ ውስጥ ስንት ነገሮች ናቸው ያሉት?"

"ከአንድ ሺህ በላይ ይሆናሉ"::

"ይህ የሚያስደንቅ ነው"::



"አንዳንዶቹ በጣም ቀላል ነገሮች ናቸው:: የትኞቹም ትልልቅ ነገሮች አይደሉም፤ ነገር ግን አሁንም ላደርጋቸው የምችል በሺህ የሚቆጠሩ ነገሮች አሉ::"

አይነስውሩ ሰው ስርነቀል በሆነ ሁኔታ መለወጡን ያስተዋለው ጓደኛው፤ እስኪ እባክህ ንገረኝ፤ እንዲህ የለወጠህ ነገር ምንድን ነው?

"ማድረግ የምችላቸውን ነገሮች ሁሉ ለመዘርዘር ወስንኩ፤ ብዙ እያሰብኩበት በሄድኩ ቁጥር፤ የማልችላቸው ነገሮች ጥቂቶች መሆናቸውን አየሁ:: በሺህ የሚቆጠሩ ነገሮችን ማድረግ እችላለሁ፤ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ደግሞ በቀሪው የሕይወት ዘመኔ ሁሉ አደርጋቸዋለሁ::"

ጽሑፉን ካነበብኩ በኋላ እንዲህ ስል አሰብኩ፤ አሁን በትክክል ለእኔ የሚያስፈልገኝ ይህ እንጂ፤ መሪር ህዘን፣ ያለፈውን ደጋግሞ ማሰብ ወይም ከዚህ በኋላ ላደርጋቸው በማልችላቸው ነገሮች መቆጨት አይደለም:: ከዚህ ይልቅ አሁን ያለኝ ነገር ምን እንደሆነ መፈተሽ ያስፈልገኛል፤ ይህንንም የማደርገው በእርሱ ለመደሰት ብቻ ሳይሆን ተስፋ ቢስ እንዳልሆንኩ እንድገነዘብ ጭምር ነው::

ይህንን ሃሣብ በጥልቀት ሳስብ፤ ከማስበው በላይ በፊቴ በርካታ ሥራዎች እንዳሉ ተገነዘብኩ:: ትኩረቴን ጫን አድርጌ የነበረው ባጣኋቸው ነገሮች ላይ ስለነበር፤ የቀሩኝን ነገሮች ፈጽሞ ዘንግቻቸዋለሁ:: እንዲሁም ሞክሬያቸው የማላውቃቸውን ነገሮች ለመሞከር እድል እንዳለኝም አላስተዋልኩም ነበር::

ባነበብኩት ጽሑፍ ውስጥ፤ አይነ ስውሩ ሰው፤ አሁን ማድረግ ስለማልችላቸው ነገሮች አልጨነቅም:: አሁን በደንብ ማድረግ

የምችላቸውን ነገሮች አደርጋለሁ የሚል ሃሳብ ይሰነዝራል:: እነዚያ ቃላት ቀላል ይመስሉ ነበር::

ያንን ጽሑፍ ያነበብኩት በትክክለኛው አስፈላጊ ጊዜ ላይ ነበር:: እነዚያ ቃላት የማይታመኑና ጥልቀት ያላቸው ይመስላሉ:: ያንን መልዕክት የላከልኝ እግዚአብሔር ነበር፤ የሚያስፈልገኝ ወሳኝ ጊዜ "በሕይወት መቀጠል አለብኝ:: ያለኝን የትኛውም ነገር እጠቀምበታለሁ፣ ደግሞም ማድረግ እስከምችለው መጠን ሁሉ እሰፋዋለሁ::" እንድል ያስኘኝ እጅግ ታላቅ መነቃቃት ውስጥ ከገባሁባቸው ጊዜዎች አንዱ ነበር::

"አሁን ጊዜ እየቀደመኝ ሄዷል፤" ስል አሰብኩ፤ "ይሁን እንጂ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ነው":: እንዲያውም ከሌሎች ሰዎች ይልቅ በሁለት ምክንያቶች እኔ ስለ ጊዜ ያለኝ ግንዛቤ የተሻለ ነበር:: የመጀመሪያው፤ በአደጋው ምክንያት ከሕይወቴ ዋነኛውን ክፍል አጥቼዋለሁ:: ሁለተኛም፤ በዚህ ምድር ላይ ብዙ እንደማንቆይ አውቄአለሁ:: ብዙዎቹ የቀደሙ ዝማሬዎች እንደሚናገሩት፤ እኛ እንግዶችና ተላላፊ መንገደኞች ነን:: እነዚህን ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች ጽሑፎችን በማንበብ ሁላችንም እናውቃቸዋለን፤ ይሁን እንጂ እነዚያ ማሳሰቢያዎች ለእኔ የማንቂያ ደወሎች ሆነውልኛል::

በተጨማሪም እነዚያ የምወዳቸው ሰዎች በመንግስተ ሰማይ መግቢያ በር ላይ እንደሚጠብቁኝ አውቃለሁ::

እንደገናም ደግሞ እግዚአብሔር እንደገና እስኪመልሰኝ ድረስ መጠበቅ ያስፈልገኛል::



እኔ በሆስፒታል ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን አባላት ቤተሰባችንን ወደ ሌላ ሥፍራ አዛውረውት ነበር:: እኛ እንኖር የነበረው ፍሬንድስውድ በተባለ ከተማ ውስጥ ሲሆን፤ ከቤተክርስቲያናችን አስር ማይልስ ያህል ይርቃል:: ወደ ቤተክርስቲያናችን ቀረብ ያለ ቤት ብንፈልግም አላገኘንም:: በሆስፒታል በነበርኩበት ጊዜ የቤተክርስቲያናችን መሪዎች አንድ ቤት አገኙ፤ ተከራዩትም፣ ያለንን ንብረት ሁሉ ጭነው ወደአዲሱ ቤት አዘዋወሩን:: ከሆስፒታሉ በወጣሁ ጊዜ የገባሁት አንቡላንሉ የሆስፒታል አልጋ ወዳለው አዲሱ ቤት ካደረሰኝ በኋላ፤ ተሽከርካሪ ጎማ ባለው ቃሬዛ እየተገፋሁ ገባሁ:: ያኔ ነበር ቤቱን ትኩር ብዬ መመልከት የጀመርኩት::

ፈጥኜ ከቤቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ጋር ተላመድኩ፤ ምክንያቱም ለረዥም ጊዜ ያየሁት የሆስፒታል አልጋውን ያኖሩበትን የሳሎኑን ክፍል ብቻ ነበር::

በአንዳንድ መንገዶች ወደ አዲሱ ቤት መዛወራችን ከእኔ ይልቅ ጫን ያለውን ችግር የፈጠረው በቤተሰቦቼ ላይ ነበር:: በእኔ ህመም ምክንያት ባለቤቴ ማስተካከል የነበረባትን አንዳንድ ሁኔታዎችና የምታልፍበትን ችግር ተረድቻለሁ:: ኢቫ አብዛኛውን ጊዜዋን ከእኔ ጋር ታሳልፍ ስለነበረ ሥራዋን ልታጣ ምንም ያህል አልቀራትም ነበር:: የስብሰባ ጊዜዎችን፤ የዕረፍትና የሕመም ፍቃዶቿን ሁሉ ከእኔው ጋር አሳልፋቸዋለች:: አንዳንድ አስተማሪዎች የራሳቸውን የህመም ፈቃዶች አሳልፈው ለእርሷ ይሰጧት ስለነበር ወደ ሆስፒታሉ መጥታ ከእኔ ጋር እንድትሆን ረድቷታል:: በመጨረሻው እነዚያ የፈቃድ ጊዜዎች ሁሉ በማለቃቸው ወደ ሥራዋ መመለስ ግድ ሆነባት:: በዚያ ላይ የመጀመሪያዋ የገቢ ምንጫችን እርሷ ነበረች::

በአልቪን ከተማ በሮበርት ሉዊስ ስቲቨንሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የነበሩ የኢቫ ጓደኞች፣ ብዙውን ጊዜ የእርሷን ተማሪዎች የፈተና ወረቀቶች ያርሙላታል፤ ዕለታዊ የትምህርት እቅዷን ያዘጋጁላታል፤ እንዲሁም ማልዶ እኔን ለማየት ወደ ሆስፒታሉ በምትመጣበት ጊዜ የእርሷን ክፍሎች ይሸፍኑላታል። ከዚህም አልፎ የቅርብ ጓደኞቿ የሆኑት አስተማሪዎች ለልጆቻችን በየዕለቱ የምንሰጣቸውን ጥቃቅን ስጦታዎች ይሰጧታል፤ በመሆኑም ልጆቻችን ስለመጭዎቹ ቀናት ተስፋን የተሞሉ እንዲሆኑ አድርገዋል። ስጦታዎቹን "አስደናቂ ሳጥኖች ነው" የሚሏቸው። አስተማሪ ጓደኞቿ ከቤተክርስቲያን አባላት ጋር በመሆን ቤታችንን ለማጽዳትና ምግባችንንም ሊያዘጋጁልን ወደ ቤታችን ይመጣሉ። እንደ አስተማሪዎቹና እንደ ቤተክርስቲያን ትጋት ባይሆን ኖሮ ኢቫ ያለ ምንም ጥርጥር ሥራዋን ታጣ ነበር፤ የእኔም እጣ ይሄው ከዚህ አይዘልም። ይሁን እንጂ ከዚህ ሁሉ አስደናቂ መስዋእትነት የተሞላ ስጦታና ድጋፍ ጋር ያንን የ1989 የጸደይ ወር የትምህርት ወቅት ያሳለፍንበት ሁኔታ እንደ ተአምር የሚቆጠር ነው።

አንድ ጊዜ ኢቫ ለእኔ እየተሰጠኝ ስላለው የረዥምም ጊዜ የህክምና ክትትል በጠየቀችበት ጊዜ፤ ነርሷ እንዲህ ስትል ተናገረች፤ "የኔ ወለላ፤ ይህንን ሁሉ ነገር ልታውቂ አያስፈልግሽም፤ አንቺ እኮ ሚስት ነሽ"።

ለዚያች ነርስ፤ እርሷ ምናልባትም "ሚስት ብቻ" ነች፤ ይሁን እንጂ ከአደጋው በኋላ ኢቫ የሁለታችንንም ሃላፊነት ደርባ እየተወጣች ነበር። ከአደጋው በፊት እኔ ሁልጊዜም የተለያዩ የውጭ ክፍያዎቻችንን፣ የባንክ ሂሣባችንን፤ የኢንሹራንስ ጉዳዮቻችንንና አብዛኛዎቹን ቤተሰባዊ ጉዳዮች እሸፍን ነበር። ምንም ምርጫ ስላልነበራት እነኝህን ሁሉ ተግባራት ደርባ ትሠራ ነበር፤ ደግሞም ሁሉንም ያለ ምንም እንከን



አጠናቃቸዋለች። ኢቫ ጥንካሬን አዳብራለች፤ ወደ አዲስ በራስ የመተማመን እርከን አድጋለች። ቤተሰባዊ ጉዳዮቻችንን እንዴት መልክ ማስያዝ እንደምትችል እግዚአብሔር ጥበብን ሰጥቷት ነበር። ረዥምም ጊዜ በወሰደው የማገገሚያዬ ጊዜ ውስጥ፤ አቀርባቸው የነበሩትን ብሶት የተሞላባቸው ጥያቄዎቼንና ማጉረምረሜን ሁሉ ታግሳ መቻልን ተምራለች።

ቤተክርስቲያን ወርሃዊ ቀለቤን መክፈሏን አላቋረጠችም፤ ይሁን እንጂ ማቋረጥ እንዳለባቸው ተገንዝበናል፣ የማልሠራ በመሆኔ ሊከፍሉኝ እንደማይገባም አውቀናል። ስለ ገንዘብ ጉዳይ ተነጋግረን እናውቅም፤ ነገር ግን በገንዘብ ምክንያት እጅና እግራችን ሊታሠር እንደሚችል አላጠነውም።

የቴክሳስ መንግስት በአደጋው ክስተት የእኔም ሃላፊነት እንዳለበት በመረዳታቸው፤ ህጉ ሊከፈለኝ የሚገባውን ክፍያ ወደ 250,000 ዶላር ዝቅ አደረገው፤ ይህም ገንዘብ በሙሉ ለሆስፒታል ወጪአችን መሸፈኛ ዋለ፤ እናም የአንድ ሚሊዮን ዶላር ሲሶ የሆነ ገንዘብ ብዙም ሊያንቀሳቅስ የሚችል አልነበረም።

የቴክሳስ መንግስት አቃቤ ሕግ የቱገላቢጦሽ በሆነ መልኩ፤ የእኔን መኪና የገጫትን ከባድ መኪና ሲያሽከረክር ለነበረ ተከሳሽ "ችግረኛ እስረኛ ነው" በሚል ሰበብ ጥብቅና ቆመለት። በዚህም ምክንያት ከታክስ የተገኘው ገንዘብ የቴክሳስን መንግስትና አደጋ ያደረሰብኝን ሰው ለመከላከል ዋለ። ሕይወት አንዳንድ ጊዜ ግራ የምታጋባ አይደለችምን?

በሆስፒታል በቆየሁባቸው 105 ቀናት፣ ኢቫ በባለ ውጥረት ውስጥ ነበረች:: በቤት ውስጥ የነበረውን ሃላፊነት ሁሉ ብቻዋን በመሸከሟ ምክንያት ብቻ አልነበረም፣ በየዕለቱ ከማለዳው 12:00 ትነሣለች፣ በቤት ውስጥ ማከናወን ያለባትን ሥራ ሁሉ ከጨራረሰች በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ትበራለች:: የትምህርቱ ጊዜ ካለቀ በኋላ ደግሞ ከአጠገቤ ለመሆን በጥድፊያ ትመጣለች:: ከዚያም እስከ ምሽቱ 4:30 ድረስ አብራኝ ትቆያለች:: ከቀን ወደ ቀን ውጥረት የሞላበት የማይለዋወጥ ሂደት::

እጅግ ፈታኝ ከሆኑት ገጠመኞቿ አንዱ - በራሷ የተፈጠረው ነበር:: ያም ሁኔታ በአደጋው ምክንያት ከጥቅም ውጭ በሆነችው መኪናዬ ምትክ፣ እኔን ለማመላለስ የሚያመች የአምቡላንስ ዓይነት መኪና ለመግዛት ያደረገችው ሙከራ ነው:: በዚያ ጊዜ እኔ ወደ ቤት የተመለስኩ ስሆን የኤልዛሮብ ፍሬሙ በእግሬ ላይ እንዳለ መራመድ ችዬ ነበር:: ይህም ማለት ወደ የትኛውም ስፍራ መሄድ የምፈልግ ቢሆን፣ ያንን አምቡላንስ መሰል መኪና መጠቀም ይኖርብኛል ማለት ነው:: በመደበኛ የመኪና ወንበር ላይ በአግባቡ ለመቀመጥ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድብኝ የምናውቀው ነገር አልነበረም::

ኢቫ በሕይወት ዘመኗ የመኪና ግዥ አከናውና አታውቅም፣ ይሁን እንጂ አልተነጫነጨችም:: ወደ መኪና ሻጩ ዘንድ ሄዳ አንዱን አምቡላንስ መሰል መኪና መረጠች፣ ከዚያም እያሽከረከረች ፈተነችው፣ ወደ ቤትም ይዛው መጣችና፣ “እነሆ መኪናችን አለች”::

በእውነት ኩራሁባት - ታላቅ ክብርም ተሰማኝ::

በዚያች መኪናዋ መሾፈርን እንደገና ተማርኩ:: አንድ ቀን ቤተሰቡ መኪናዋን ያጥቧት ነበር፣ ኤልዛሮቩ በእግሬ ላይ እንዳለ ወደ



ውጭ ወጣሁ:: ወደ መኪናዋ በዝግታ ስጠጋ፣ በሾፌሩ በኩል ያለው በር ክፍት እንደሆነ ተገነዘብኩ:: ወደ ውስጥ ስመለከት፣ የእኔንና በላዬ ላይ የተሸከምኩትን ስላሣ ፓወንድ የብረታ ብረት ክብደት ይዤ ከመሪ በስተኋላ ለመቀመጥ የሚበቃውን ስፍራ ገመትኩ:: ቤተሰቤ ትኩረታቸው በእኔ ላይ አልነበረም፣ ራሴን እንደ ምንም ከመቀመጫው ላይ አኖርኩና ሞተሩን አስነሣሁት:: ቤተሰቦቼ ደነገጡ::

ኢቫ ወደ በሩ ዞራ መጣችና “ምን እያደረክ ነው?” ስትል ጠየቀችኝ::

ፈገግ አልኩና፣ “እያሽከረከርኩ ልወጣ ነው!” አልኳት:: የምታየውን አላመነችም፣ ሳታስበው፣ “ልታደርገው ግን አትችልም” አለች::

ይሁን እንጂ፣ ለአንድ ዓመት ያህል መኪና ባላሽከረክርም፣ የመጨረሻው የመኪና ሾፌርነት ተግባሬ በሞት ቢጠናቀቅም አሁን ማሽከርከር ካልጀመርኩ ዳግመኛ የመኪና መሪ ይዤ እንደማላሽከረክር አንድ ነገር በጆሮዬ ሹክ አለኝ::

መኪናዋን በዝግታ ወደ ኋላ ነድቼ አወጣሁና በህንጻው ዙሪያ አሽከረከርኩ:: በእርግጥ ረዥም ጉዞ አልተጓዝኩም፣ ይሁን እንጂ እያገገምኩ ለመሄዴ ምስክር የሆነ መታሰቢያ ነበር:: አሁንም ቢሆን በሰዓት ስማንያ ኪሎ ሜትር ለመብረር ወይም ረዥም ርዝመት ባለው ድልድይ ላይ ለማሽከርከር ደስተኛ አይደለሁም:: ይሁን እንጂ መሄድ እስከምፈልግበት ርቀት ድረስ እያሽከረከርኩ እጓዛለሁ::

በእርግጥ አንዳንድ ቀጠሮዎቼን መከታተልና በሳምንት ሁለት ቀናት በዶክተሮች ቢሮ ያለኝን የጤና ምርመራ የመከታተሉ ጉዳይ የወደቀው በኢቫ ላይ ነው:: መጨመር የምፈልገው ነገር ቢኖር እኔ ለእንክብካቤ የምመች ቀላል ሰው አለመሆኔን ጭምር ነው:: እስቸጋሪ ሰው እንደነበርኩ እውነት ነው:: ጤንነቴ እየተሻሻለ ሲሄድ፤ በሆነ ባልሆነው የምነጫነጭና በጥቃቅን ነገሮች ሁሉ የማጉረመርም ሆንኩ (ይህ ግን በጊዜው ለእኔ አይታወቀኝም ነበር)፤ ኢቫም እኔን ለማስደሰት ብዙ ተጨንቃለች፤ ያም ሆኖ ተሳክቶላታል::

የችግሩ ሁሉ ምክንያት ደስተኛ ስላልነበርኩ ነው:: ብዙዎቹ ችግሮቼ ይመነጩ የነበሩት ፍጹም ተስፋ የለኝም ከሚል ስሜቴ ነበር:: በጣም ለረዥም ጊዜ እንዲት ብርጭቆ ውሃ በገዛ እጄ አንስቼ አልጠጣም:: ምንም እንኳን በራሴ መቅዳት ብችልም፤ ሰው መጥቶ ካልረዳኝ በቀር በፍጹም አልጠጣም:: እያንዳንዷ ትንሽ ድርጊት እንኳን ዋጋ እንደሌለው ሰው እንዲሰማኝ ታደርገኛለች::

አብዛኛውን ጊዜ ኢቫ በሁኔታው ላይ ወዲያውኑ እኔን ሳታናገር እርምጃ ትወስዳለች:: ማድረግ የምትችለውን ያህል ታደርግ ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ኢቫ ነገሮችን በራሷ መንገድ በመስራት ላይ ሳለች፤ እኔ እንዴት እሠራው እንደነበር ለእርሷ ለመንገር እፈጥናለሁ:: ነገር ግን ወዲያውኑ ያንን በማድረግ ምን ያህል ስሜቷን እንደጎዳሁት እገነዘባለሁ:: ይሁን እንጂ ቃሉቼ አንድ ጊዜ አምልጠውኝ ወጥተዋል:: ስለአለሁበት ሁኔታና ስለእርሷም አስብና፤ በጣም አዝናለሁ:: “ማድረግ በምትችይው አቅም ሁሉ እያደረግሽ ነው” እላለሁ:: ራሴንም የማሳስበው ነገር ነበረኝ፤ ቁም ነገሩ ያንን ነገር እንዴት ማድረግ እችል እንደ ነበር ሳይሆን፤ አሁን ማድረግ አለመቻሌ ነው::



በነዚያ ጊዜያት እርሷ የምትናገረው ጥቂት ነገሮች ብቻ ቢሆንም በኋላ ላይ በዕለታዊ ውሎ እንቅስቃሴ ማስታወሻ ደብተሯ ላይ የጻፈችውን እንዳነብ አድርጋለች:: ከጻፈቻቸው አንዱ፤ “ዶን እኔ በማደርገው ነገር ሁሉ ላይ አቃቂር ያወጣል:: እየተሻለው በመሄዱ ምክንያት መሆን አለበት” የሚል ይገኝበታል::

ያ ለእኔ አሳዛኝም አስቂኝም ነው:: አንዳንድ ውሳኔዎችን እንደገና መስጠት በመጀመሬ እየተሻለኝ እንደሄደ አውቃለች:: ነገሮችን ለማድረግ የነበረኝ የነቃ ፍላጎት እየተሻለኝ ለመሄዱ የእርሷ መመዘኛ ነበር:: በሕይወት ዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ለመሣተፍና በዙሪያዬ እየሆነ ስላለው ነገር ለመጠየቅ የምፈልግ ይመስላል::

ጥሩ ባህሪ ያለው ታማሚ ሆኜ ነገሮችን ቀላል አድርጌላት ብሆን እመኝ ነበር::

እያገገምኩ በነበረበት ጊዜ አስቸጋሪ ሆኖብኝ የነበረው የቤተሰቦቼ ጉዳይ ሲሆን፤ ይኸውም የሦስቱ ልጆቻችን ከእኛ መለየታቸው ጉዳይ ነበር:: እናትና አባታቸውን ያጡ ልጆች አልነበሩም፤ ይሁን እንጂ ለሦስት ወራት ያህል ከሌሎች ሰዎች ጋር እየኖሩ ነው:: ሁለቱ መንታ ልጆቼ በሉሲኒያ ውስጥ ከሚኖሩት ከኢቫ ቤተሰቦች ጋር እንዲቆዩ ተደርጓል::

ከእኛ ያን ያህል መራቃቸውን የወደዱት እንዳልነበረ አውቃለሁ:: ርቀቱ ልጆቹ ከእኛ እንደራቁና እንደተለዩ እንዲሰማቸው አድርጓል፤ ይሁን እንጂ ሁሉንም ተቋቁመውታል:: ምናልባትም ገና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በመሆናቸውና በዚያም ዕድሜ ከለወጡት ሥፍራ

ጋር ቶሎ መላመድ አላስቸገራቸው ይሆናል። በዚያ ጊዜ ከመንትያዎቹ በአምስት አመት በላጭና አሥራ ሦስት ዓመት ዕድሜ የነበራት ኒኮል፣ ከሴት ጓደኛዋ ቤተሰቦች ጋር በመጠጋት በዚያው ቆይታ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርቷን መከታተል ችላለች። ከእኛ ተሰይታ መሄዷ ለእርሷ እጅግ አሳዛኝ ገጠመኝ ሳይሆን እንዳልቀረ አስባለሁ።

አደጋው የደረሰው በጥር ወር ውስጥ ሲሆን እስከ ሰኔ ወር ድረስ ልጆቹ ፈጽሞውኑ ወደ ቤት አልተመለሱም ነበር። ለልጆቻችን አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማቅረብ የማንችል በመሆናችን እጅግ ተሳቅቄና አዝኜ ነበር።

ሆስፒታል በነበርኩበት ጊዜ በሳምንቱ ማብቂያ ቀናት ልጆቹ ሲያዩኝ ይመጡ ነበር፣ ያ ደግሞ ለእነርሱ ከባዱ ጊዜ ነው። ወደ ሆስፒታሉ መጥተው መጀመሪያ ያዩኝ ጊዜ፣ የክፍሉ የሥነ አዕምሮ ሃኪም መልካም ነገር አደረገላቸው። ሦስቱንም ልጆች ወደ አንድ ክፍል ወሰደ፣ በሰው ቁመና ልክ የተሠራና ከመሣሪያ ጋር የተያያዘ የሰው ምስል አካል በማሳየት፣ በእኔ አካል ላይ የደረሰውን ጉዳት አሳያቸው። በዚህ መንገድ እኔ ወዳለሁበት ክፍል ሲገቡ የሚያዩትን ነገር አስቀድሞ ገለጸላቸው።

ይህንን በማድረጉ ደስተኛ ነኝ፣ እንደዚያ ዐይነት ቅድመ ዝግጅት ያላደረጉ ብዙ አዋቂ ሰዎች እንኳን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያዩን በሚታይ ሁኔታ ድንጋጤአቸው ተገልጿል። እነርሱ በሚያሳዮት ድርጊት እኔ የነበርኩበት ሁኔታ ምን ያህል አስከፊ እንደነበር አመዛዝናለሁ።

ልጆቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ክፍሌ በመጡ ጊዜ ሦስቱም ሊጨብጡኝ መቅረብ የሚችሉትን ያህል ርቀት ተጠግተውኝ ነበር። በጣም ይወዱኝ ስለነበር ደህንነቴን በራሳቸው ማረጋገጥ ይፈልጉ ነበር።



እርግጥ ነው በዚያ ጊዜ በሞትና በሕይወት መካከል ነው የነበርኩት፣ ይሁን እንጂ እነርሱን በማየቴ ብቻ መልካም ሆኖልኝ ነበር። ሀኪሞቹ ብዙ እንዲቆዩ አልፈቀዱላቸውም። ምንም እንኳን አካሌ በአሰቃቂ ሁኔታ መጎዳቱ የሚታይ ቢሆንም፣ በቅርቡ ደህና እንደምሆን በነገርኳቸው ጊዜ ልጆቹ አምነውኝ ነበር።

እነርሱ ከሄዱ በኋላ፣ ኢቫ ተመልሳ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍሉ መጣች። እኔ ይህንን አላስታውስም፣ በዚያ ጊዜ ስለሆኑት ነገሮች ብዙ የማስታውሰው ነገር የለም። እርሷ እንደነገረችኝ፣ በአክስጂኑ ጭንብል ውስጥ እያየኋት፣ “በዓለም ላይ ምርጥ የሆኑ ልጆች አሉን” ብያለሁ።

ልጆቼ ምንም ነገር እንደጎደላቸው ይሰማቸዋል የሚል ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም፣ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ከልምድ ማጣት የተነሣ ስለአባታቸው የተሳሳተ አመለካከት ኖሯቸው ይታሰሱ ይሆናል የሚል ስጋት ነበረኝ።

በመጨረሻው ከሆስፒታል ከወጣሁና መራመድም በቻልኩ ጊዜ፣ ከልጆቹ ጋር የጎልፍ ጨዋታ ለመጫወት መሞከሬን አስታውሳለሁ፣ ከአንድና ከሁለት እርከኖች በላይ ማለፍ እንደማልችል አውቅ ነበር። ከልጆቹ መካከል አንዱ ኳሷን ከእኔ በኋላ አሻግሮ ከመታት ተከትያት መሄድ አልችልም። በዚህ ነገር በጣም ያዝኑና ይቸገሩ ነበር።

በጨዋታው ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ ካለመቻሌ የተነሣ፣ በጨዋታው ሙሉ በሙሉ ከመደሰት ተቆጥበው ነበር፣ በመሆኑም ፈጥነን አቆምነው። አፍ አውጥተው አይናገሩ እንጂ ለመሮጥ ሙከራ ሳደርግ ወይም ለመውደቅ አደጋ ተጋልጬ ስማየት አለመፈለጋቸውን አውቄአለሁ።

በተጨማሪም ከአደጋው በፊት ሁለቱም ወንዶች ልጆች በባህር ዳርቻው ውሃ ላይ የመንሳፈፍ ልማድ ነበራቸው፤ እኔም አብሬአቸው እንሳፈፍ ነበር:: አሁን መራመድና መኪና ማሽከርከር ከቻልኩ በኋላ፤ በብዙ አጋጣሚዎች የመጫወቻ መሳሪያዎቻቸውንና እነርሱን በመኪናዋ ጭኜ ወደ ጎልፍ መጫወቻ ሥፍራው እወስዳቸዋለሁ፤ ይሁን እንጂ ከእነርሱ ጋር እንዳች ነገር ማድረግ አልችልም:: ይህንን እነርሱ ሊረዱልኝ የቻሉ ይመስላሉ፤ ለእኔ ግን በዚያን ጊዜ ከባድ ነበር::

ልጆቹ ማድረግ የሚፈልጓቸው ሌሎች ነገሮች እንደሚኖሯቸው አልጠራጠርም፤ ነገር ግን ጠይቀውኝ አያውቁም:: ምክንያቱም እኔ ወደ ሁኔታዎች ውስጥ እንዳልገባና ጉዳት እንዳይደርስብኝ በመፍራት ነበር:: በዚህ ምክንያት ልጆቼ በማደጊያ ዕድሜያቸው ላይ ሳሉ እንደልብ ተጫውተው እንዳያድጉ ከአንዳንድ ሁኔታዎች እንዲገደቡ ተጽእኖ እንደተደረገባቸው ይሰማኛል::

ኒኮል ትልቋ ልጃችን የአባቷን ነገር በአግባቡ የምትረዳ ነበረች:: ስሜቷን የምትገልጸው ከጆይ ይልቅ በጣም በተለየ መንገድ ነው:: እርሱ በጣም ስሜታዊ ነው:: ክሪስ ደግሞ ምንም እንኳን ጠለቅ ባለ ሁኔታ ንቁ ቢሆንም ረጋ ያለ ልጅ ነው፡፤ በመሆኑም እንደ መንትያው ስሜቱን በቀላሉ መግለጽ አይሆንለትም::

ይህ መጽሐፍ በሚጻፍበት ጊዜ፤ ልጆቼን ሰብስቤ አደጋው እንዴት አድርጎ በእነርሱና በቤተሰባችን ላይ ተጽእኖ እንዳሳደረና ስለ እኔ የነበራቸውን አመለካከት እንዴት እንደለወጠው ጠይቄአቸው ነበር:: አደጋው በ1989 በተከሰተ ጊዜ ኒኮል የአስራ ሦስት ዓመት ልጅ ነበረች:: እርሷ እንዲህ ስትል መልስ ሰጠች::



"አደጋው በሕይወቴ ላይ ያሳደረው ትልቁ ተጽእኖ ለበርካታ ወራት ከቤተሰቦቼ ርቄ እንድኖር ማድረጉ ነው:: በዚያ ጊዜ እኖር የነበረው የእኛ ቤተክርስቲያን አባላት ከሆኑት ከጓደኛዬ ካማውልዲን ቤተሰቦች ጋር ነበር፡፤ አደጋው የራሴን ቤተሰቦች እንዳደንቃቸው አስተምሮኛል:: እኔ ለእነርሱ ሁሉ በጣም ቅርብ ነኝ፤ ምክንያቱም የዚህ አስደሳች ቤተሰብ አካል በመሆኔ ምን ያህል እድለኛ እንደሆንኩ ተረድቻለሁ:: በተጨማሪም ደግሞ ሰዎች ችግር በደረሰባቸው ጊዜ መረዳት እንደሚገባኝ ይሰማኛል፤ ምክንያቱም በዚህ በወጣትነት ዕድሜዬ በአስቸጋሪ ሁኔታ ወቅት ጸሎትንና ባልንጀሮችን እንዴት መጠቀም እንዳለብኝ ተምሬአለሁ:: በአጠቃላይ ሕይወትን በተለየ አቅጣጫ እንድመለከት አድርጎኛል:: በዚህ የወጣትነት እድሜዬ ሕይወት ምን ያህል ውድ እንደሆነችና እያንዳንዷን ቅጽበት በአግባቡ ልንጠቀምበት እንደሚገባ ልገነዘብ ችያለሁ::

በአደጋው ምክንያት ቤተሰቦቼ በጣም መቀራረብ እንዳቻሉ ይሰማኛል:: እንዳችን ለሌላችን እውነተኛ የሆነ ጥንቃቄ እናደርግ እንደነበረም ይሰማኛል፤ ለቤተሰባችን አባል ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል:: ወንዶቹ ልጆችና እኔ ብዙውን ጊዜ በወንድምና በእህቶች መካከል ከሚታየው መቀራረብ ይልቅ የቀረበና የጠበቀ ግንኙነት አደብረናል:: በአባቴ ላይ የደረሰው አደጋና ከዚያ በኋላ የሆነው ማገገሙ እርስ በእርሳችን እንድንተሳሰብ አስተምሮናል:: እማማ በጣም ጠንካራና በራሷ የምትተማመን ሆናለች፤ ምክንያቱም አባባ ሁልጊዜም ያደርጋቸው የነበሩትን ነገሮች ሊያደርጋቸው አይችልም ነበር:: ቤተሰቡ ሁሉ እንደገና እንዲሰበሰብ አባቴ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምነው ባለለፈ እያልኩ ብቻ እመኝ ነበር::

አባቴ ከሩኛ ከተጎዳ በኋላ፤ እርሱ እንደማንኛውም ሰው አደጋ ሊደርስበት ወይም ችግር ሊያጋጥመው የሚችል ሰው መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከትኩ:: ከአደጋው በፊት፤ በምንም ዐይነት ሁኔታ ጉዳት ሊደርስበት የሚችል አይመስልም ነበር::

ከእነዚያ ዓመታት በኋላ፤ አደጋው ይበልጡን ጠንካራ ሰው እንዳደረገው ተመልክቻለሁ:: እርግጥ ነው ምናልባት አካሉ ተጎድቶ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን በመንፈሳዊና ስሜታዊ ሁኔታዎች ጠንካሮች እንደሆኑ ከማውቃቸው ሰዎች ይልቅ ጠንክሯል:: በዚያ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ካለፈ በኋላ፤ አሁንም ፍቅር የተሞላና ፍጹም የተሰጠ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑ ለእኔ አስደናቂ ነገር ነው::

ለረዥም ጊዜ ስለ አደጋው ባሰብኩ ቁጥር እናደድ ነበር፤ ነገር ግን ባደግኩ ጊዜ እርሱ በሕይወት ተርፎ ከእኛ ጋ በመሆኑና አደጋውም እጅግ እንድንቀራረብ በማድረጉ እድለኞች እንደሆንን ልገነዘብ ችያለሁ:: በአደጋው ወቅት ሞቶ ቢሆን ኖሮ፤ በሕይወቴ ባጋጠሙኝ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት ማለፍ እችል እንደነበር አላውቅም:: በመንግስተ ሰማይ ከነበረ፤ ቁጥር ስፍር ከሌላቸው ቀዶ ጥገናዎች በኋላም በሕይወት መኖር ከቻለና ስለዚህም ለመናገር በመኖር ላይ ካለ ሰው በሚሰጠው ምክር ውስጥ በጣም የተለየ ነገር አለ:: አሁን እርሱ የሚናገረውን ነገር በጥሞና ማድመጥ ጀምሬአለሁ::"



ጆይ ደግሞ በአደጋው ወቅት የስምንት ዓመት ልጅ ነበር፤ እርሱ ደግሞ መልስ የሰጠው እንዲህ ሲል ነበር፤

"የመጀመሪያው ትውስታዬ የእናቴ ጓደኛ በሆነች አስተማሪ አማካይነት ከት/ቤት መወሰዴ ነው:: እናቴ ስታለቅስ ባየኋት ጊዜ አንድ ጠንከር ያለ ችግር እንደተፈጠረ አውቄ ነበር::

አባቴን ለማየት ወደ ሆስፒታል መሄዴንም አስታውሳለሁ::

የአባባን አደጋ ሁኔታ እንድናውቅ በአሸንጉሊት ሠርተው አሳዩን፤ እናም ወደ ውስጥ የገባነው ተዘጋጅተን ነበር:: አባባን በዚያ ሁኔታ ውስጥ ማየት የሚከብድ ነገር ነበር:: በዚያ ብዙ አልቆየንም፤ እንዲዚያ ማድረጋቸው ለእኔ ጥሩ ነበር፤ ምክንያቱም እንደዚያ ሆኖ ላየው አልፈለግኩም:: እኔና ክሪስ በሉሲያና ወደሚኖሩት አያቶቻችን ተወስደን በዚያ ተቀመጥን:: በመጀመሪያ ላይ አካባቢው በጣም እንደሚቀዘቅዝ ተሰምቶኝ ነበር፤ በኋላ ግን ቤተሰቦቼ ይናፍቁኝ ጀመር:: መንትያ ወንድሜ ከእኔ ጋር በመሆኑ በጣም ደስተኛ ነበርኩ:: በየሣምንቱ መጨረሻ ላይ ከቦሲር ከተማ ወደ ሀውስቶን በመኪና እንወሰዳለን:: ነገሩ ሁሉ በፍጥነት እንግዳ ሆኖብኝ ነበር::

የአደጋው እጅግ አስከፊ ጎን የነበረው፤ ሌሎች ልጆች ከአባቶቻቸው ጋር ለሽርሽርና ዓሣ ለማጥመድ ሲወጡ እነዚያን ነገሮች ለማድረግ ፈጽሞ አለመቻሌ ነበር:: እስከዛሬም ድረስ ስለዚያ ሁኔታ አብዝቼ አስባለሁ:: አንዳንድ ጊዜ የብስጭት ሁኔታና ድብርት ውስጥ የመግባት ነገር ይሰማኝ ነበር:: ነገር ግን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ከአባባ ጋር ሽርሽር ለመውጣትና ዓሣ ለማጥመድ ችያለሁ:: እነዚህ ነገሮች ምን ያህል እንደሚያስደስቱኝ ይገነዘበው እንደሆን አላውቅም:: እርሱ በአደጋ ውስጥ ባለፈበት ሁኔታ ምን ያህል ሰዎች እንደሚወዱንና ለእኛም

ቤተሰብ ግድ እንዳላቸው ለመገንዘብ ችያለሁ:: እግዚአብሔር በሕይወታችን ባይኖርልን ኖሮ፤ በዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ እንዴት እናልፍ እንደነበር አላውቅም::"

የክሪስ ምላሽ ደግሞ ይህንን ይመስላል::

"የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለህ አባትህ ምን ጊዜ ለአንተ ትልቁ ጀግና ሰው ነው:: በምንም ነገር ሊበገር የሚችል አይመስልህም:: በአባቴ ላይ አደጋ እንደደረሰበት በመጀመሪያ ስሰማ፤ የደረሰበት ጉዳት ያንን ያህል ትልቅ ይሆናል ብዬ አላሰብኩኝም:: እማማ ስለአደጋው በነገረችኝ ጊዜ እጅግ ተስፋ ቆርጣ ነበር፤ እናም የሚፈስውን እንባዋን መደበቅ አልቻለችም:: አባባ ግን ጠንካራ ነበር፤ እርሱ ሲያለቅስ በጭራሽ አይቼ አላውቅም::

በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ በብዙ የህክምና ባለሙያዎች ተከቦ፣ በኦክስጂን እየተነፈሰና መናገር እንኳን ተስኖት እያየሁ፤ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ተሽሎት ወደ ቤት እንደሚመለስ ሙሉ ለሙሉ ጠብቄ ነበር::

አብዛኞቹ ዋነኛ የቀዶ ጥገና ህክምናዎቹ በተደረጉለት ጊዜ እኔ በዚያ አልነበርኩም:: ከአደጋው በኋላ በነበሩት ጥቂት ቀናት ውስጥ ከአያቶቼ ጋር ለመኖር ሄድኩ:: አባባን ለማየት የነበረኝ ዕድል በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት ላይ ብቻ ነበር:: እርሱን ማየት በቻልኩባቸው በእነኛ አጫጭር ጊዜዎች ምን ያህል ክፉኛ እንደተጎዳ መገንዘብ ጀመርኩ - በመንፈሱም በአካሉም:: በእጁና በእግሩ ላይ የነበሩ እነኛ ብረታ ብረቶች ትኩረቴን ስበው ያስደንቁኝ ነበር፤ ይሁን እንጂ ክፉኛ የህመም ስቃይ እያደረሱበት እንዳሉ ተረድቻለሁ:: እጅግ ተዳክሞ ስለነበር ሁኔታው ልክ



ገና ከእንቅልፉ እንደነቃ ወይም ፈጽሞ ተኝቶ እንዳላደረ ሰው ነበር የሚመስለው:: አንዳንድ ጊዜ እኔ እገምታለሁ:: ምንም እንኳን ስለ ድብርት የማውቀው በጥቂቱ ቢሆንም፤ በዚያ እንደተጠቃ አውቄ ነበር::

ልጠይቀው በሄድኩ ጊዜ አደርግ የነበረው የመጀመሪያ ነገር በዝግታ ወደ እርሱ መቅረብና እጄን በእርሱ አንገት ዙሪያ አድርጌ ማቀፍ ነበር:: በቀስታ እጨብጠዋለሁ:: በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ አቅም የሌለው ተሰባሪ ነገር ሆኖ ተሰማኝ:: ከሆስፒታል ወደ ቤት ከተመለሰ በኋላ እንኳን፤ ያንኑ ነገር ነበር ደጋግሜ የማደርገው - ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ተመልሼ አባቴን መጨበጥ:: ይህ ሁኔታዬ ለእኔ በእርሱ የመተማመንን ለእርሱ ደግሞ ምቾትን ይሰጠዋል:: በሁለቱም መንገዶች እንደ ሠራ ተስፋ አደርጋለሁ::

ወንድሜ ጆይና እኔ እያደግን በሄድን መጠንና አባቴም እየተሻለው ሲመጣ፤ በእስፖርትና ከቤት ውጭ በሚዘወተሩ ጨዋታዎች ይበልጥ እየተሳብን ሄድን:: አባባ ከእኛ ጋር ለመቀላቀል የተቻለውን ጥረት ያደርግ ነበር:: አንድ ጊዜ ኳሷን አሻግሬ ስወረውራት ክፉኛ እንደወደቀ አስታውሳለሁ:: በጨዋታው ላይ ሚዛኑን አጥቶ ይንገዳገዳል፤ አንዳንድ ጊዜም ይወድቃል:: በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ስለዚህ ነገር እንባዬ እያመለጠኝ አልቅሻለሁ:: እርሱም እንደ እኔ እንዳለቀሰ እርግጠኛ ነኝ:: ስሜታዊ በሆኑት ሁኔታዎች ግን አባቴ ሁልጊዜም ከእኔ ጋር ነበር:: ልጆቹ በሚሠሩት ነገር ላይ ከፍተኛ ትኩረትና ፍላጎት ነበረው:: ከሁሉም በላይ ደግሞ፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከገነት የመመለሱን ነገር ከፍተኛ ግምት የሰጠነው ይመስለኛል::

በአባቴ ላይ በደረሰው አደጋ ምክንያት ቤተሰባችን በጣም ተቀራረበ:: ሁላችንም ሥራዎችን ከመከፋፈልም አልፈን የተለያዩ

ሚናዎችን እንጫወት ነበር:: አባባ እያገገመ በነበረበት ወቅት እማማ ውሳኔ የምትሰጥና እኛንም ሥነ ሥርዓት የምታስይዝ ሆነች:: እኔ ደግሞ የቤቱ አባወራ እንደሚያደርገው ለማድረግ የተቻለኝን ጥረት አደረግኩ:: አንዳንድ ጊዜ እንደዚያ እንዳደርግ ራሴን አስጨንቅ ነበር፤ ነገር ግን በዚያው ነገር ውስጥ እየበሰልኩ ሄድኩ:: ኒኮል በምትችለው አቅም ሁሉ ለእኔና ሰጆይ እንደ እናት ሆነችልን::

ከአደጋው በኋላ አባባ ለዓመታት ያህል በድብርት ውስጥ ገባ፤ አሁንም እንኳን በጥቂቱ ምልክቶቹ ይታዩበታል:: ምናልባትም ከአደጋውም በፊት እንኳን ሲታገለው ሳይቆይ አይቀርም:: እንደዚያ እያደረገ ከቆየም እኔ ግን በጭራሽ አልተገነዘብኩትም:: አባቴ እጅጉን በራሱ የሚተማመንና ውስጠኛውን ማንነቱን አልፎ አልፎ ብቻ ለቤተሰቡ ግልጽ የሚያደርግ ሰው ነው:: እኔም እንደርሱ እንደሆንኩ አስባለሁ::"

ከአደጋው ጋር በተያየዘ ኢቫ ስለ እኔ የነበራት አመለካከት መለወጡን ስትገልጽ እንዲህ ብላለች::

"ከአደጋው በኋላ በነበሩ የመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ውስጥ ዶን አንዳንድ ውሳኔዎችን ለመወሰን ሲቸገር በማየቴ በጣም ተደንቄ ነበር:: እርሱ ምን ጊዜም የሕይወትን ውጣ ውረድ የሚጋፈጥና እራሱንና ሌሎችን ጭምር ብዙ እንዲሠሩ የሚያደፋፍር ሰው ነበር:: ለመናገር መሞከሩን ባቆመ ጊዜ ልክ የማላውቀው ዓይነት ሰው ሆኖ ይሰማኝ ጀመር:: በድብርት ውስጥ መግባቱም አንድ አዲስ ጉዳይ ነበር:: "ክፉው ጊዜ" እየቀረበ እንደመጣ ምልክቶቹን ማስተዋል ጀምሬ ነበር:: የህመም ስቃዩ እየከፋ ሲሄድ ድብርቱ ይጨምራል፤ መተኛት አይችልም እናም ችግሩ እየከፋ ይሄዳል::



በዓመታት መካከል አንድ ነገር እየተገነዘብኩ መጣሁ፤ ዶንን በራሱ ነገሮችን እንዲያደርግ የምታወው ከሆነ በመጨረሻው እየተጠናከረ ይሄዳል ብዬ አስብ ነበር:: መስማት የሚያስፈልገውን አንድ ነገር ልነግረው ስፈልግና እርሱ ግን ማወቅ ሳይፈልግ ሲቀር እንደበቴን እሰበስባለሁ፤ በጥቂት ሁኔታዎች ውስጥ ግን አልተሳካልኝም ነበር::

ምንም እንኳን ጉዳተኛ እንደሆነና ወደፊትም በዚሁ እንደሚቀጥል ባውቅም፤ ዛሬ ዛሬ ጉዳት እንደደረሰበት ሰው እንኳን አድርጌ አላስብም:: ዶን ሰላም ያሰው ሰው ስለሆነ የነበረበትን ስቃይ እንኳን ልረሳውና ጉድለቶቹንም ላላስባቸው ችያለሁ:: የእኔ ባሰቤት በርግጥ የተለየ ሰው ነው::

ምናልባትም ከእኔ ይልቅ ልጆቼ ነበሩ ከጉዳቴ እንደማገግም እርግጠኞች የሆኑት:: ህክምና ሲደረግልኝ፤ በስቃይ ሳቃስት ወይም ለሞት በተቃረብኩበት ሁኔታ ውስጥ ስገባ በጭራሽ አይተው አያውቁም፤ ምክንያቱም ያንን እንዲያዩ ባስመፈለጌ ነበር:: በተቻለው መጠን ነገሮችን እንሸፋፍንባቸዋለን:: ኢቫ እጅግ አስከፊ በሆነው ሁኔታዬ ውስጥ አይታናለች፤ ልጆቹን ግን በተቻለ መጠን ሁኔታዬን እንዳያዩ ታሸሻቸው ነበር::

ምንም እንኳን እነርሱ ባይቀበሉትም በተለይ መንትያዎቹ ልጆች ከእኔ ጋር የነበራቸው ቅርርብ ተቋርጦ ነበር:: ምክንያቱ ደግሞ እድሜያቸው ስምንት ዓመት መሙላቱ ነው:: ይህ ዕድሜ የቡድን እስፖርቶችንና ሽርሽርን የመሳሰሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች

ለመለማመድ አስፈላጊ የሆነ የዕድገት ጊዜ በመሆኑ የእኔ በቅርብ ሆኖ ሁኔታዎችን የመከታተልና የማለማመድ ሚና አጥተውታል።

አሁን ወደ ኋላ ሳስብ፤ አደጋው ከማንም ይልቅ ወላጆቼን በዘላቂነት ጎድቷቸው እንደሄደ አስባለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ እድጉን ለብሯቸዋል፤ ከሦስቱ ወንዶች ልጆቻቸው የመጀመሪያው እኔ ነኝ፤ ሁላችንም ደግሞ ጤነኞች ነበርን። ከዚያ ዕድሜዬ ሰላሳ ስምንት ዓመት ሲሞላ በድንገት ልባቸውን የሚሰብር ነገር ተከሰተ፤ ለእኔ ምንም ሊያደርጉልኝ እንደማይችሉ እስከሚያስቡ ድረስ ተስፋ ቆረጡ። ለረዥም ጊዜ ምናልባት አንድ ቀን ይሞታል ብለው ያስቡ ነበር።

አባቴ በዘመኑ ሁሉ በውትድርና ነው ያገለገለው፤ እናታችን ደግሞ ሌሎችን የቤት ጣጣዎች ቀጥ አድርጋ ይዛ ነበር። ይሁን እንጂ ሆስፒታል በገባሁባቸው የመጀመሪያ ሳምንታት ሊያዩኝ በመጡ ጊዜ እናቴ ራሷን ሳተች። አባቴ ከንዷን እፈፍ አድርጎ በመያዝ ክፍሉን ለቃ እንድትወጣ ረዳት። በእንደዚያ ያለ የተበላሸ የአካል ቅርጽ ሆኜ ልታየኝ አልተዘጋጀችም። ማንም ሰው እንደሷ ሊሆን ማየቴን እርግጠኛ አይደለሁም።

እስከ አሁንም ቢሆን ከእናቴ አዕምሮ ውስጥ የአደጋው ነገር መጥፋቱን እርግጠኛ አይደለሁም። ቤተሰቦቼ ለእኔ የነበራቸውን ፍቅር የሚገልጹ ሁለት ውብ ትውስታዎቼ የሚቀጥሉት ናቸው።

የመጀመሪያው፤ ከአደጋው ቀጥሎ በነበረው የበጋ ወራት የሆነው ነው። በዚያ ጊዜ ኢቫ ለራሷ እንዳች ነገር ለማድረግ ግድ አልነበራትም፤ እናም የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን ወጣቶችን ወደ በጋው ሽርሽር ስፍራ ልትወስድ ወሰነች። በአካል ጤነኛ በነበርኩበት ጊዜ ያንን ማድረግ



የእኔ ሥራ ነበር። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ እርሷን ተክቶ ከእኔ ጋር የሚሆን የግድ አንድ ሰው መተካት ነበረበት።

እናቴ በደስታ ነገሩን ተቀበለችው። ወጣቶቹ ወደ ሽርሽሩ የሚሄዱበት ሳምንት ተቃረበ፤ እናም ኢቫ እኔን ለእናቴ ትታ ሄደች። በእያንዳንዱ ቀን እማማ ምግብ ታዘጋጅልኛለች፤ በእርሷ እዚያ መገኘ ትም በጣም ተደስቼ ነበር። ነገር ግን በአንድ ዕለታዊ ተግባር እጅግ ተሳቅቄ ነበር እናቴ የሽንትና የአይነምድር መቀበያ ዕቃዎችን ማጸዳዳት ነበረባት። አዎ በህፃንነቴ የሽንት ጨርቆቼን ትለውጥልኝ እንደነበረ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ በአሁኑ ማንነቴና በህፃንነቴ ጊዜያት መካከል በርካታ ዓመታት አልፈዋል።

አስታውሳለሁ፤ በመጀመሪያው ቀን እኔን በመንከባከብ ላይ ሳለች የአይነ ምድር መቀበያውን እንድታቀርብልኝ ጠየቅኋት። ያ ድብቅ ያልሆነ የተለመደ ተፈጥሯዊ ግዳጅ እንደሆነ እንዳውቀው ለማድረግ ሞከረች። ከጨረስኩ በኋላ ለእርሷ ለመንገር ከፍተኛ የሆነ የውስጥ ጭንቀት ተሰማኝ።

እርሷ እንደጨረስኩ በመጠየቋ ምክንያት ከጭንቀቴ ገላገለችኝ። በአምንታ ራሴን አነቃነቅኩ። መቀበያውን አንስታ ወደ መታጠቢያ ቤቱ ይዛው ሄደች፤ ከዚያ በኋላ በሕይወት ዘመኔ ከሰማኋቸው ድምጾች ሁሉ ፈጽሜ የማልረሳውን ድምጽ ሰማሁ። ወደ መታጠቢያ ቤቱ አይነምድሩን ከደፋች በኋላ እማማ ስትዘምር እሰማት ነበር። የሰው ልጅ ለሌላው ሰው ማድረግ የሚችለውን የመጨረሻውን ዝቅተኛ ነገር እያደረገች ቢሆንም ዕቃውን እያጠበች ትዘምራለች። ነገሩ ሁሉ በልጅነቴ ታደርግልኝ የነበረው የእናትነት ተግባሯ እንደገና የተመለሰ ይመስላል። አንድ ጊዜ ታደርገው እንደነበረ ልጇ ሊያደርግ የማይችለውን ነገር

እያደረገችለት ነበረ፤ እናም ደስተኛና ሥራዋም የተሣካላት ነበረች። ያንን ትዝታ ከአዕምሮዬ አላወጣውም፤ ምክንያቱም አንድ እናት ለልጇ ያላት ብቸኛ ፍቅር የተገለጸበት ድርጊት ስለነበረ ነው።

የማስታውሰው ሁለተኛው ነገር፤ ከአባቴ ጋር የነበረኝን የአጭር ጊዜ የግል ቆይታ ነው። ይህም ከእናቴ ጋር እንደነበረኝ ቆይታ ሁሉ ልብ የሚነካና ተውኔታዊ የሚመስል ነበር። አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ቤተሰቦቼ 250 ማይሎች ርቀት ተጉዘው ሊጠይቁኝ ወደ ቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል ከመጡ በኋላ ተመልሰው ወደ ቦሲር ከተማ ለመሄድ እየተዘጋጁ ነበር።

በማላስታውሰው የሆነ ምክንያት እናቴ ከክፍሉ ቀድማ ወጥታ ነበር። እኔና አባቴ ብቻችንን በሆንን ጊዜ ወደ አልጋዬ መጥቶ ደህነኛ የነበረውን የቀኝ እጄን ጠንካራ በሆነው የእጅ መዳፍ ጨብጦ ያዘ። ወደ እኔ እጅግ ተጠግቶ ከፍተኛ በሆነ ስሜትና ፍጹም ሐቀኝነት በተሞላበት ሁኔታ፤ "ያለኝን ነገር ሁሉ በመስጠት ከጎንህ እቆማለሁ፤ የአንተን ነገር በእኔ ጣለው" ሲል ተናገረ።

አዎን አባቴ ነው፤ ከዚያም በላይ ከሌሎች ጊዜዎች ሁሉ ይልቅ ምን ያህል እንደሚወደኝ ተገነዘብኩ።

ዶክተሩ በተደጋጋሚ "ለአንተ የምናደርገው ማንኛውም ነገር ማድረግ የምንችለውን የመጨረሻ ነገር ነው። እረዥም እድሜና ስኬታማ የሆነ ሕይወት ሊኖርህ እንደሚችል አትቁጠር። ቁርጥማትና በርካታ የሆኑ ውስብስብ ችግሮች ይከሰታሉ፤ በዚህም ታላቅ ጦርነት ከፊትህ ይጠብቅሃል" ሲል ነግሮኛል።



የሚናገረውን ነገር ያውቅ ነበር። አሁን አደጋው ከደረሰብኝ አሥራ አምስት ዓመታት አልፈዋል። የቁርጥማቱ ስሜት ይሰማኝ ጀምሯል። ትንሿም ለውጥ ብትሆን ትጎዳኛለች፤ ፈጥኜም እደክማለሁ። አንዳንዶቹ ጉዳዮች ከእድሜ ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን እግሮቼንና ጉልበቶችን እግዚአብሔር አስቀድሞ ሲፈጥራቸው እንድጠቀምባቸው ካቀደው ውጭ እየተገለገልኩባቸው የመሆኑ ውጤት እንደሆነ አስባለሁ።

አሁን እንኳን የግራው ጉልበቴ ከመጠን በላይ የተሰጠጠ ነው፤ በመሆኑም አንድ ሰው ከኋላዬ መጥቶ በድንገት ጀርባዬን መታ ቢያደርገኝ ፈጥኜ ራሴን ማቆም አለብኝ፤ ካልሆነ ግን ዝም ብዬ ወደፊት መገስገሴን እቀጥላለሁ። ወደ ከፍታ ስፍራ ወደፊት በምሄድበት ጊዜ ሚዛኔን ለመጠበቅ እንዲያስችለኝ ጉልበቴን መቆጣጠር አልችልም።

ነገሮችን ቀለል ለማድረግ እንዲህ እያልኩ እቀልዳለሁ፤ "በቴክሳስ ውስጥ በሚገኙ በአንዳንድ ምርጥ ስፍራዎች ላይ ወድቄአለሁ" ወይም፤ "ዶን ፒፐር እዚህ ወደቀ" የሚል ማስታወቂያ ኮሚሽን እከፍላለሁ" እላለሁ።

አንድ ጊዜ በቴክሳስ ተራራማ ሀገር፣ ከቤት ውጭ የሚደረግ ኮንፍራንስ አሳተፍ ነበር። ስፍራው ሜዳማ ስላልነበረ በምራመድበት ጊዜ ድንገት ወደቅኩ ጉዳት አልደረሰብኝም፤ ይሁን እንጂ ገና በመጀመሪያው ቀን ሦስት ጊዜ ነበር የወደቅኩት።

ምንም እንኳን የሚቻላቸውን ሁሉ ቢያደርጉልኝም፤ አንደኛው እግሬ ከሌላኛው ይልቅ በአንድ ኢንች ከግማሽ ያህል ያጠረ ነው። ይህ በራሱ የጀርባ አጥንቴን እንዲጎብጥ አድርጎታል። በጭኔ መገጣጠሚያ

ላይ እንደሆነው ሁሉ የጀርባ አጥንቴም መጎዳትና መለያየት ጀምሯል:: የቀኝ እጄ ክርን እጅጉን ስፍራውን በመልቀቁ ቀጥ አድርጌ ልዘረጋው አልችልም:: ዶክተሮቹ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ አድርገውልኛል፤ ይህም ብዙ ጊዜ ቀዶ ጥገና ማድረግን ይጨምራል:: ክርኔ የተሰነጠቀው ከውስጥ ነው፤ በመሆኑም ወደኋላ ካጠፍኩት በኋላ መልሼ ለመዘርጋት በጣም ያስቸግረኛል:: ዶክተሩ የሚጠቀምበትን ቋንቋ ልጠቀምና፤ "ፍጹም ሽባ" የሆነ መታጠፊያ ነው::

እንዲህ ያለ ጉዳት በቀላሉ ይቅርታ የሚያደርግ አይደለም፤" ሲል ተናግሮ ነበር:: አንድ ጊዜ ስፍራውን ከለቀቀ እንደገና ለማስተካከል ይከብዳል::

እንግዲህ ይህ አንዱ ልቀበለው የተገባ የአዲስ ሕይወቴ ገጽታ ነው::

አንድ ጊዜ በዶክተር ቶም ግሪደር ቢሮ ታክሜ ስጨርስ፤ ወደ ግል ቢሮው እንድገባ ጠየቀኝ:: ምንም እንኳን በርካታ የሥራ ጫና ቢኖርበትም፤ ከልቡ በእኔ ጉዳይ ላይ ትኩረት የሰጠ በመሆኑ ስለ ብዙ ነገሮች ተነጋገርን::

ድንገት እንዲህ ስል ጠየቅኩት:: "ቶም፤ በአደጋው ምሽት ወደዚህ ሥፍራ ሲያመጡኝ ምን ያህል ክፉኛ ተጎድቼ ነበር?"

ምንም ሳያንገራግር፤ "ከዚያ የከፋም ተመልክቻለሁ" ለአጭር ጊዜ ዝም አለና በደረቱ ወደ ጠረጴዛው ተጠግቶ፤ "ነገር ግን አንዳቸውም በሕይወት አልኖሩም" አለ::



አንዳንድ ነገሮችን ለማድረግ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ነበረብኝ:: አዎ በሕይወት አለሁ፤ በሕይወት እስካለሁ ድረስም ኢየሱስ ክርስቶስን የማገልገል እቅድ አለኝ:: ይሁን እንጂ ከፊቴ የሚጠብቀኝን አስቀድሜ አውቄዋለሁ::

በየትኛውም ጊዜ ይህችን ዓለም ለቅቄ ለመሄድ ተዘጋጅቻለሁ::

# 15

# ነፍሳትን መድረስ

"የርህራሄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ:: እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፤ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት፤ በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን" 2ቆሮ 1፥3-4

አንዳንድ ጊዜ አሁንም እንኳን በመንግስተ ሰማይ እንድቆይ ያልተፈቀደልኝ ለምን እንደሆነ እግዚአብሔርን እጠይቃለሁ:: ለዚህ ጥያቄዬ መልስ አልተሰጠኝም:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እኔን ወይም መልዕክቴን የሚፈልጉ ሰዎችን ወደ እኔ በመላክ ወደ ሕይወታቸው መድረስ እንድችል ዕድል እንደሰጠኝ ተምሬአለሁ::

በአደጋው ምክንያት ሰዎችን እንዳገለግል ለመጀመሪያ ጊዜ በሩ የተከፈተልኝ በአንድ ትልቅ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተጋባዥ ሰባኪ ሆኜ በነበረበት ጊዜ ነው:: የጋበዙኝ በተለይ ወደ መንግስተ ሰማይ ስላደረኩት ጉዞ እንድናገር ነበር:: በአዳራሹ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ረድፎች ላይ ከእኔ በስተቀኝ በኩል የነበረች አንዲት ሴት ገና መናገር ከመጀመሬ አለቀሰች:: የእንባ ዛላዎች ጉንጮቿን እያቋረጡ ሲወርዱ ማየት ችዬ ነበር:: ልክ ስብሰባውን እንደጨረስን እየሮጠች መጣችና እጄን ጨበጠችኝ::

"እናቴ የሞተችው ባለፈው ሳምንት ነበር"::

"እናትሽን ስላጣሽ በጣም አዝናለሁ ..."



"አይደለም ... አይደለም ነገሩ አልገባህም:: በዚህ ምሽት ወደዚህ የላከህ እግዚአብሔር ነው:: እንዲህ አይነቱ ማረጋገጫ ያስፈልገኝ ነበር:: ያላመንኩ ሴት ስለሆንኩ አይደለም፤ አምናለሁ፤ ይሁን እንጂ እናቴን በማጣቴ ልቤ በጣም አዝኖ ነበር:: አሁን በጣም መረጋጋት ይሰማኛል:: አሁን ያለችው በተሻለ ስፍራ ነው:: አ! መጋቢ ፒፐር፤ የተናገርከው ቃል በዚህ ምሽት ያስፈልገኝ ነበር::"

አንዳች ቃል ጨምሬ ከመናገሬ በፊት እጄን አጥብቃ በመጨበጥ እንዲህ አለች፤ "እንደገናም ደግሞ በዚህ ምሽት እግዚአብሔር ወደዚህ የላከኝ፤ ይህ ማረጋገጫ የሚያስፈልገኝ በመሆኑ ምክንያት ነው:: ስለማላምን ወይም የማላውቀው ጉዳይ ስለሆነ አይደለም፤ ምክንያቱም እኔም ሆንኩ እናቴ አማኞች ነን፤ ነገር ግን እነኛን ቃላት ዛሬ ምሽት መስማት ያስፈልገኝ ነበር:: ስለመንግስተ ሰማይ በዚያ ከነበረ ከአንድ ሰው ማወቅ ያስፈልገኝ ነበር::"

እኔ እስከማስታውሰው ድረስ፤ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያናገረችኝ የመጀመሪያዋ ሰው ናት፤ በእርግጠኝነት የመጨረሻዋ ግን አልነበረችም:: እንደዚህ ያሉ ምላሾችን ከመቶዎች ጊዜ በላይ ሰምቻለሁ:: በዚያ የነበረኝን ቆይታዬን በመናገር ብቻ ለብዙዎች ባርኮት የመሆኑ ጉዳይ ያስደንቀኛል::

ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ምስክርነቴ ማረጋገጫ ነው፤ ለሚጠራጠሩና ለማያምኑ ስለ እግዚአብሔር ትኩረት ሰጥተው እንዲያስቡ መንገድ የሚከፍት ነው::

ከአደጋው በኋላ ሁለት ዓመት ቆይቶ፤ ገና የእግር መደገፊያ ብረቶችንና ክራንቾችን እየተጠቀምኩ ሳለ፤ በቤተክርስቲያናችን ያሉት ወጣቶች ወደ ሃውስተን የመጀመሪያ መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ስብሰባ እየወሰድኳቸው ነበር። ዳውሰን ማክሊስተር የወጣቶች ታዋቂ አስተማሪ የዕለቱ ተናጋሪ ነበር።

ከወጣቶች ጋር ስትሠሩ ሊያጋጥም እንደሚችለው፤ ያለንበትን የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን በቶሎ ለቀን አልወጣንም ነበር። ምንም ነገር አልተናገርኩም፤ ይሁን እንጂ በመዘግየታችን በጣም ነበር ያዘንኩት። ቶሎ መድረስ የፈለኩበት ምክንያት፤ ቢያንስ ቢያንስ ስብሰባው ከመጀመሩ ከአንድ ሰዓት በፊት እስቀድመን ካልተገኘን ለእይታ ጥሩ የሆኑ መቀመጫዎች ሁሉ ቀድመው እንደሚያዙ ስለማውቅ ነበር።

ማዘኔ እንዲታወቅብኝ ለማድረግ ሞከርኩ፤ ነገር ግን ከጉባኤው ከሚካሄድበት የመጀመሪያው የመጥምቃውያን የሃውስተን ቤተክርስቲያን በደረስንም ጊዜ ተስፋ እንደቆረጥኩ ነበር። ወደ ትልቁ የመሰብሰቢያ ህንጻ በገባንበት ጊዜ እንደ ፈራሁት በምድር ወለሉ ላይ የነበሩ መቀመጫዎች ሁሉ በሰዎች ተሞልተዋል። ደረጃዎችን በመውጣት ወደ ፎቁ ማምራት ነበረብን።

ተጨማሪ እርምጃዎችን በደረጃዎቹ ላይ የመራመዱን ነገር ሳስበው ማጉረምረም ጀመርኩ። መንቀሳቀስ የምችል ብሆንም እንኳን፤ እነዚያ የእግር መደገፊያ ብረቶችና በብብቶቼ ስር ይገፔ እራመድባቸው የነበሩ ክራንቾች በጣም አድክመውኝ ነበር። ነገሩን እጅግ አስከፊ ያደረገው ደግሞ አሣንሰሩ አለመስራቱ ነበር። ያ ሰው ዘግይቶ ባይመጣ ኖሮ፤ እነዚያን ደረጃዎች ሁሉ ለመውጣት እያስፈልገኝም ነበር እያልኩኝ ማሰቤን ቀጠልኩ።



ችግሩ ደረጃዎቹን መውጣት ብቻ አልነበረም፤ አዳራሹ ጥቅጥቅ ብሎ ሞልቶ ስለነበር የቀረው የመጨረሻ መቀመጫ መጨረሻ ላይ ያሉት ረድፎች ብቻ ነበሩ። ወጣቶቹ አንድ መቀመጫ እንደሚይዙልኝ ቃል ገቡ። እዚያ እስክደርስ 150 ደረጃዎችን ቆጠርኩ፤ በብዙ ጭንቅ ወደፍጻሜው ደረስኩ።

ጫፉ ላይ በደረስኩበት ጊዜ ፈጽሞ ተዳክሜ ነበር። ከመቀመጫዎቹ የመጨረሻ ወደሆነው ልጆቹ ወደያዙልኝ ስፍራ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረኝ መራመድ ተስኖኝ ነበር። ከመቀመጤ በፊት ‑ ያም በራሱ ብዙ ጥረት የሚጠይቅ ነበር። የግንቡን ግድግዳ በመደገፍ ትንፋሼን ሰበሰብኩ። ትንፋሼን እንደገና ለመመለስ እየሞከርኩ ራሴን እንዲህ ስል ጠየቅኩት፤ እዚህ ምን እያደረኩ ነው?

ወጣቶቹን ወደ ስፍራው የሚወስድ አዋቂ ሰው ማግኘት እችል ነበር፤ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር መሆን እፈልግ ነበር።፤ እንደገና ጠቃሚ ሰው እንደሆንኩ ማሰብ እፈልግ ነበር። በተጨማሪም ለወጣቶቹ ይህ አስደሳቹ ጊዜ እንደሆነም አውቅ ነበር፤ እናም የዚህ ደስታቸው ተካፋይ ለመሆን እፈልግ ነበር። የሚያስተጋባ ሳቅና ጩኸት አዳራሹን ሞልቶታል። ወጣቶቹ ለመባረክና ለመመከርም ዝግጁዎች ነበሩ፤ ነገር ግን በዚያ ጊዜ ውስጥ ስለወጣቶቹ እያሰብኩ አልነበረም ወይም ከስብሰባው ምን ያህል ተጠቃሚዎች እንደሚሆኑም እያሰላሰልኩ አልነበረም። አስብ የነበረው ፈጽሞ ከጥቅም ውጭ እንደሆንኩ ነበር።

በዚያ ቅጽበት ለራሴ ማዘን ጀመርኩ። ግድግዳውን ተደግፌ እንደቆምኩ በዓይኖቼ ጉባኤውን ቃኘሁት። ከነበርኩበት ስፍራ ሁለት እርከኖች እልፍ ብሎ አንድ ወጣት ተሽከርካሪ ጎማ ባለው ብስክሌት ላይ ሆኖ አየሁት። የተቀመጠው በእጆቹ ራሱን ይዞ ሲሆን የሚታየኝ

ጀርባው ነበር:: ወደእርሱ ተጠግቼ ማነጋገር እንደሚገባኝ አወቅኩ:: ለድርጊቴ ምክንያት መስጠት አላስፈለገኝም ነበር፤ መድከሜንም ሁሉ በድንገት ረሣሁ::

ክራንቹን በግድግዳው ላይ አስደገፍኩና በዝግታ፤ ህመም እየተሰማኝ እርሱ ወደነበረበት ሥፍራ ደረጃዎቹን እየወረድኩ ሄድኩ:: አካሉ ግዙፍና መልክ መልካም ወጣት ነው፤ ዕድሜው ምናልባት 16 ይሆናል:: እየቀረብኩት ስሄድ እርሱን ማነጋገር የፈለኩበትን ምክንያት ተረዳሁ:: ከርቀት ሆኜ ያላየሁትን ነገር ስቀርበው አየሁ፤ ልጁ የኤልዛሮቭ ፍሬም በእግሩ ላይ ተደርጎለታል:: ድካሜ ሁሉ ጠፋ፤ ንዴቴና ለራሴ የነበረኝ የሃዘን ስሜት ተወገደ:: ነገሩ ሁሉ እኔ ራሴ በዚያ ተሽከርካሪ ብስክሌት ላይ ተቀምጬ በነዚያ ጊዜያት ያየኋቸውን ስቃዮች ሁሉ እንደገና የማልፍባቸው ነው የሚመስለው::

እጁን በትከሻው ላይ ጣል ሳደርግ ፊቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዙሮ ነበር:: ራሱን ዘወር አደረገና አትኩሮ ተመለከተኝ

"ይህ ነገር በጣም ያማል፤ አይደለም" ስል ጠየኩት::

ትኩር ብሎ ማየቱን ቀጠለ፤ በውስጡ "እንዴት ያለ ሞኝ ሰው ነው?" የሚል ይመስላል:: ነገር ግን፤ "አዎ፤ በጣም ነው የሚያሳምመው" አለኝ::

"አውቃለሁ" አልኩና ትከሻውን መታመታ አደረግኩ፤ "እመነኝ ስቃዩን አውቀዋለሁ ዓይኖቹ በአግራሞት ፈጠጡ፤ "በዚህ ሁኔታ አልፈህበታል?"

"አዎን አልፌበታለሁ፤ እንዳንተው አንዴ ተደርጎልኝ ነበር"



"እጅግ አስጨናቂ ነው"::

"አውቃለሁ:: በጣም አስጨናቂ ነው:: በግራ እግሬ ላይ አንድ ተደርጎልኝ ነበር፤ ለአሥራ አንድ ወራት ያህል::"

"ማንም ሰው ሊረዳልህ አይችልም" አለ ሃዘን በሞላበት ድምጽ::

"ሊረዱልህ አይችሉም:: ይህ ችግር ለሰዎች ነግረሃቸው ሊረዱልህ የሚችሉት ዓይነት ችግር አይደለም::"

ለመጀመሪያ ጊዜ በዓይኖቹ ውስጥ አንድ ነገር ተመለከትኩ:: ምናልባትም ተስፋ ወይም ሰላም ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም በመጨረሻው እያለፈበት ያለውን ስቃይ የሚረዳለትን አንድ ሰው አግኝቷል:: አንድ የሚያደርገን ነገር ነበር፤ አጠገቡ ልቆም በመቻሌ ራሴን እንደ እድለኛ ቆጠርኩት::

"ስሜ ዶን ይባላል" አልኩት፤ አሁን የተገናኘኸው እያለፍክበት ያለውን ስቃይህንና ሃዘንህን ሁሉ ከሚረዳልህ ሰው ጋር ነው::

ትኩር ብሎ ሲያየኝ ቆየና አይኖቹ በእንባ ረጠቡ፤ "ከዚህ ሁኔታ ውስጥ በሰላም መውጣቴን እንኳን አላውቀም"::

"ትወጣዋለህ፤ እመነኝ ትወጣዋለህ" ::

"ምናልባት አለ"::

"ምን ሆነህ ነበር?" ወዲያውኑ አንድ ነገር ተገነዘብኩ፤ በፍቃደኝነቱ የተደረገለት የቀዶ ጥገና ህክምና አይደለም::

"በበረዶ መንሸራተት ጨዋታ ላይ ሳለሁ አደጋ ደርሶብኝ ነበር"::

እንደገናም ደግሞ የስፖርት ጃኬት እንደለበስ ተመለከትኩና

“የእግር ኳስ ተጫዋች ነህ” አልኩት።

“አዎን”

በእኔ ላይ ስለደረሰው አደጋ በአጭሩ ነገርኩት፤ እርሱም ያጋጠመውን ችግር በዝርዝር አጫወተኝ ... “አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ” አልኩት፤ “አንድ ቀን እንደገና ትራመዳለህ”።

ፊቱ ላይ ጥርጣሬ ሲያጠላበት አስተዋልኩ።

“ምናልባት እንደገና እግር ኳስ ልትጫወት ትችላለህ፤ ነገር ግን ትራመዳለህ”። ማንነቴን የሚገልጸውን ካርዴን ሰጠሁት፤ የስልክ ቁጥሬን በካርዱ ላይ ታገኛለህ፤ እናም በፈለክበት ሰዓት በቀን ይሁን በሌሊት፣ ባመችህ በቀኑ የትኛውም ጊዜ ልትደውልልኝ ትችላለህ።

ካርዱን ተቀበለና ትኩር ብሎ ይመለከተው ጀመር።

“ይገርቸው ወደመጣሁት ልጆች መመለስ አለብኝ” አልኩና የተቀመጡበትን ስፍራ አመለከትኩት። “ስራመድ በደንብ እንድትመለከተኝ እፈልጋለሁ። እየተመለከትከኝ ሳለ አንተም አንድ ቀን እንደምትራመድ እንድታውቅ እፈልጋለሁ” አልኩትና ሳቅሁ።

“እውነቱን እነግርሃለሁ አንተ ደግሞ ከእኔ በተሻለ ሁኔታ ትራመዳለህ”።

ቀና ብሎ እጄን ጨበጠና እየወዘወዘ ሰላምታ ሰጠኝ። ለረዥም ጊዜ እጄን አጥብቆ ይዞ ነበር። ከእንባው ጋር እየተናነቀ የሚያሰማውን



የስቀይ ድምጽ ስሜት መረዳት ችያለሁ። በመጨረሻው እጄን ለቀቀና ምስጋናውን አዥጎደጎደው።

“ችግርህን የሚረዳልህን አንድ ሰው አግኝተሃል” አልኩት፤ “እባክህን ደውልልኝ”

ያ ልጅ የሚረዳለትን አንድ ሰው ይፈልግ ነበር። ምን ያህል ላግዘው እንደምችል አላወቅኩም፤ ነገር ግን ያለፍኩበት ልምምድ አለኝ፤ ስለ ህመም ስቃይ ልነግረውም እችላለሁ። እርሱ ባለፈበት ሁኔታ ውስጥ ያላለፍኩ ቢሆን ኖሮ፤ “እንደሚሻልህ ተስፋ አደርጋለሁ። ይሻልሃል ብቻ ብዬው አልፍ ነበር - ብዙ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው የመልካም ምኞት መግለጫዎች - ነገር ግን ሁኔታውን በጥልቅ ያላገናዘቡ ቃላት ናቸው።

ወደስፍራዬ በደረስኩ ጊዜ ካደረኩት የመውጣትና መውረድ እንቅስቃሴዬ የተነሳ ሰውነቴ በላብ ተጠምቋል፤ ነገር ግን ግድ አልነበረኝም። ዘወር ብዬ ተመለከትኩ፤ አሁንም አትኩሮ ይመለከተኛል። ፈገግ አልኩና እጄን አወዛወዝኩለት፤ እርሱም አጸፋውን መለሰልኝ። ሃዘኑና የተስፋ መቁረጥ ስሜቱ ከላዩ ላይ ተወግዷል።

በቀጣዮቹ ስድስት ወራት፤ ሦስት ጊዜ ያህል የስልክ መልዕክቶቹን ተቀብያለሁ። ሁለቱ ጊዜያቶች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የተነጋገርንባቸው ሲሆኑ፤ ሦስተኛው ደግሞ ከአንድ እጅግ ተስፋ በቆረጠበት ሌሊት ያደረግነው የስልክ ንግግር ነበር። እነዚያ የስልክ ጥሪዎች ሁልጊዜም የምደስትባቸው ናቸው፤ ከአንዱ ወደሌላው ለማለፍ የሚደረግ የትግል ጉዞ ስለሆነ።

አንድ ጊዜ የሃውስተን ቴሌቪዥን ጣቢያ በቀጥታ ስሚተላለፍ ቃለ ምልልስ ግብዣ አደረገልኝ:: ገና በእንግዳ ማረፊያው ክፍል እያለሁ፤ የፕሮግራሙ አዘጋጅ ወደ እኔ መጥቶ ፕሮግራሙ እንዴት እንደሚሠራና ልጠየቃቸው ስለሚችሉ አንዳንድ ጥያቄዎች ገለጻ አደረገልኝ::

"በጣም ጥሩ ነው" አልኩ፤ በተጨማሪ "ተጋባዥ እንግዳ ሆኖ የሚቀርበውስ ማን ነው?"

"አንተ ብቻ ነህ"::

"ምን ማለትህ ነው? የአንድ ሰዓት ፕሮግራም እየሠራችሁ፤ እኔ ብቻ ነኝ እንግዳችሁ?"

"አዎ፤ እንደዚያ ነው"::

ለአንድ ሰዓት ያህል ምን እንደምናገር ይገርመኝ ጀመር:: ገና ማገገም የጀመርኩበት ጊዜ ነበር፤ እናም በዚያ ወቅት የእኔን ታሪክ ለመስማት ሰዎች ምን ያህል ጉጉት እንዳላቸው አላውቅም:: ለቃለ ምልልሱ በቀረብኩት ጊዜ ዶክተሩ የኤልዛሮቭ ፍሬሙን ከእግሬ ላይ አንስቶልኝ፤ በአጥንት መደገፊያ ብረቶችና በክራንች እየተጠቀምኩ ነበር የምራመደው:: በሆስፒታል ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በአደጋው የደረሱብኝን ጉዳቶች የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ይገኙ ነበር፤ በዚያ ቀን በተላለፈው ፕሮግራም ምስሎቹ ተላልፈዋል፤ ራሱን የኤልዛሮቭ ፍሬም መሳሪያውንም ጭምር ይዤ ቀርቤ ነበር::

የቴሌቪዥን ቃለ ምልልሱ በተጀመረ ጊዜ፤ ታሪኬን በዝርዝር ተናገርኩ፤ ከዚያ ጋባዡ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀመረ:: ሰዓቱ በፍጥነት አለቀ:: ገና በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭቱ ላይ እንዳለን አንድ ሴት ወደ



ቴሌቭዥን ጣቢያው ስልክ ደውላ፤ ከመጋቢ ፒፐር ጋር አሁኑኑ መነጋገር እፈልጋለሁ ስትል ጥያቄዋን አቀረበች::

ፕሮግራሙን አቋርጠው ጣልቃ እንድትገባ አልፈለጉም፤ ነገር ግን ፕሮግራሙ ከተፈጸመ በኋላ አንድ ሰው የሴትዮዋ አድራሻ የተጻፈበትን ወረቀት ሰጠኝ:: እናም ደወልኩላት::

"ወንድሜን ልታነጋግረው ይገባል" አለች::

"የወንድምሽ ችግር ምንድን ነው?"

"በአንድ መጠጥ ቤት በተደረገ ረብሻ ውስጥ ተካፍሎ ነበር፤ አንድ ሰው ሽጉጡን መዞ እግሩን በመምታት እንዲቆረጥ አደረገው:: በአንተ እግር ላይ እንደነበረው ነገር እይነት በእግሩ ላይ ተደርጎለታል::"

"በእርግጥ አነጋግረዋለሁ" አልኳት፤ አሁን የት ነው ያለው?

"በቤት ውስጥ አልጋ ላይ ነው"::

"አድራሻውን ስጭኝና ሄጄ ..."

"ኧረ በጭራሽ፤ እንደሱማ አይሆንም:: በታላቅ ቁጣ ውስጥ ነው ያለው:: ደግሞም አደጋ ሊያደርስ የሚችል እመጸኛ ነው:: እርሱን ለማየት የሚመጣውን ማንኛውንም ሰው አያናግርም አለችና የስልክ አድራሻውን ሰጠችን:: "እባክህን ደውልለት፤ አሁን በጥሩ ሁኔታ ውስጥ አይደለም ያለው፤ መልካም ንግግር እንደማይጠብቅህ" አረጋግጥልሃለሁ አለች:: በመጨረሻው ማስጠንቀቂያ ነገረችኝ፤ "ስልኩን ሊዘጋብህ ይችላል፤ ይሁን እንጂ እባክህ ሞክረው::"

ገና ወደ ቤቴ እንደደረስኩ፣ ወደ ወንድሟ ደወልኩና ራሴን አስተዋወቅኩት:: ሦስት ተጨማሪ ዐረፍተ ነገሮች ከመናገሬ በፊት፣ ልክ እህቱ የገመተችውን ነገር አደረገ:: በቁጣ ጮኸብኝ:: ድምጹን ከፍ አድርጎ ስሞቻቸውን የማላውቃቸውን የርግማን ቃላት ሁሉ አወረደብኝ:: ርግማኑንም ብዙ ጊዜ ደጋገመው::

ስድቡን ትንሽ ጋብ ባደረገበት ቅጽበት ተረጋግቼ፣ "አንተ ያደረግከውን ነገር እኔም በእግሬ ላይ አድርጌ ነበር ያንን የእግር አጥንት ማስተካከያ መሣሪያ" አልኩት::

ስሚቀጥሉት ጥቂት ሰከንዶች ምንም አልተናገረም፣ እናም "ያንን የኤልዛሮቭ ፍሬም በግራ እግሬ ላይ አድርጌው ነበር እያለፍክበት ያለውን ስቃይ አውቀዋለሁ"::

"አ! ሰውየው ... ስቃዮ ሊገድለኝ እኮ ነው:: ያለ እንዳች ፋታ ነው የሚያሰቃየኝ::" የተናገርኩትን እንዳልሰማ ያህል እንደገና ቁጣው ገነፈለ፣ ልቅ በሆነ ቋንቋና ባልተገራ አነጋገር ብስጭቱን መግለጽ ጀመረ::

እንደገና ከንግግሩ ትንሽ ጋብ ሲል "ያደረግከው የህክምና መሣሪያ የተደረገላቸው ሰዎች የሚሰማቸውን ስቃይ እረዳዋለሁ" አልኩት::

"አሁን በአንተ እግር ላይ የለም፣ አይደል?"

"የለም፣ በመጨረሻው አወጡልኝ፣ ማድረግ የሚገባህን ነገር የምታደርግ ከሆነ፣ ከአንተም ላይ አንድ ቀን ይወልቅልሃል":: ያ ንግግር ያን ያህል ዋጋ ያለው አልነበረም፣ ነገር ግን መናገር እችላለሁ ብዬ ያሰብኩት ብቸኛው ነገር ነበር::



"ከተደረጉልኝ ብረቶች አንዳንዶቹን አሁኑኑ ባወጣቸውስ?"

"የምታወጣቸው ከሆነ፣ እግርህን እንደቆረጥከው የሚቆጠር ነው፣ ምክንያቱም እነዚያ ብረቶች ናቸው የእግርህን አጥንቶች አገጣጥመው የያዙልህ::"

"ያንን አውቃለሁ፣ ነገር ግን እየገደለኝ እኮ ነው መተኛት አልችልም ... እና"፣ እንደገና በቁጣ ገነፈለ፣ በምን ያህል ስቃይ ውስጥ እንደሆነና ሁሉንም ነገር ምን ያህል እንደጠላ ነገረኝ::

ከዚያ በኋላ አንድ ነገር በእኔ ውስጥ ሲሆን ተሰማኝ፣ አቋረጥኩትና፣ "እግርህ ምንድን ነው የሚመስለው? ብረቶቹ በገቡበት አካባቢ በጣም ቀልቷል? በቆዳህ ላይ ከላይና ከታች ተመሳሳይ ቀለሞች አሉ? ከሌሎቹ ይልቅ ሃይለኛ ህመም እንዲሰማህ የሚያደርጉ የተለዩ ቀዳዳዎች አሉ?" ስል ጠየኩት::

"አዎ፣ ትክክል ነህ፣ በተለይ አንደኛው - ሰውየው - ከፉኛ የጎዳኝ እርሱ ነው::"

እህትህ አሁን በአካባቢህ አለች?" እንዳለች በነገረኝ ጊዜ፣ "ከእርሷ ጋር አገናኘኝ" ስል አዘዝኩት::

አልተከራከረም ነበር፣ እርሷም ቴሌፎኑን ያዘችና፣ "አመሰግንሃለሁ ... በጣም ነው የማደንቅህ ..." አለች::

"አሁን እኔን አድምጭኝ" አልኳት ንግግሯን አቋርጬ፣ "አሁኑኑ አምቡላንስ እንድትጠሪ እፈልጋለሁ፣ በተቻለ ፍጥነት ወንድምሽን ወደ ሆስፒታል እንድትወስጂው ይሁን:: በፍጥነት መድረስ ካልቻለ እግሩን ሊያጣ ይችላል::"

"እንደዚያ ይሆናል ብለህ ታስባለህ?"

"የምነግርሽን ስሚ:: ምልክቶቹ ሁሉ እየታዩበት ነው:: ምናልባትም ትኩሳት ጭምር ሊኖረው ይችላል:: ትኩሳቱን አይተሻል?"

"አዎን፤ ትክክል ነው:: ትኩሳትም አለው::"

"አሁኑኑ ወደ ሆስፒታል ውሰጂው:: ከዚያ በኋላ ደውይልኝ::"

በሚቀጥለው ቀን ደወለችልኝ:: "ኦ ትክክል ነበርክ! ሰውነቱ ተመርዞ ነበር፤ የሚያስፈራ የአካል ቅርጽም ነበረው:: ጸረ ተህዋስያን የሆኑ መድሃኒቶችን ሁሉ ሰጡት በጊዜው ወደ ሆስፒታል እንደመጣም ነገሩኝ፤ እናም ዛሬ ትንሽ ሻል ብሎታል::"

"አሁንም ሰዎች ሲገቡበት ባልተፈቀደ ክፍል ውስጥ ተለይቶ እንደተኛ እገምታለሁ" አልኳት:: ትክክል እንደሆነ ስትነግረኝ፤ "መጥፎ እየዋለሁ" ስል ጨምሬ ነገርኳት::

አገልጋይ ስለሆንኩ ገብቼ ላየው እችል ነበር:: እናም ወደ ሆስፒታሉ ሄድኩ፤ ተጫዋወትን አብረንም ጸለይን:: በመጨረሻው ያ ወጣት ወደ ጌታ መጣ::

በዚያ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ባልቀርብ ኖሮና እህቱም ያንን ፕሮግራም ባትከታታል፤ ሰውየው እግሩን ማጣቱ ብቻ አይደለም ሕይወቱንም የማጣት ዕድሉ ሰፊ ነበር:: እግዚአብሔር የተጠቀመብኝ የወጣቱን አካላዊ ሕይወት ለማትረፍ ብቻ ሳይሆን ለደህንነቱም እንደ መሣሪያ ሆኛለሁ:: ይህ ደግሞ እግዚአብሔር አሁንም በምድር ላይ እንድሠራው ያዘጋጀው ነገር እንዳለ ካየሁባቸው ድርጊቶች ውስጥ አንደኛው ነበር::



ችግሩን ፈጥቼ ነበር የተገነዘብኩት፤ ምክንያቱም በሆስፒታል ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በእኔ ላይ የደረሰ ችግር ነበር:: ሰውነቴ ተመርዞ ከፉኛ የተጎዳሁበት ጊዜ ነበር:: ያን ጊዜ እንደ ሌሎቹ የስቃዩ ክፍሎች እንደ አንዱ ቆጥሬ በዚያ ውስጥ ማለፍ እንደሚገባኝ አስቤ ነበር:: ከዚያ በኋላ ግን ነርሷ ብረቱ ካለፈባቸው በእግሬ ላይ ካሉ ቀዳዳዎች አንደኛው መመረዙን ደረሰችበት::

ከዚያ በኋላ፤ ከአንድ ቀን በፊት ከነርሶቹ አንዷ በጥንቃቄ ጉድለት ለመመረዜ ምክንያት እንደሆነች በግልጽ አስታወስኩ:: ርህራሄ የማይታይባት ዐይነትና እንደሌሎቹ ፍቅርን የማታሳየኝ ሴት ነበረች:: ወደ ክፍሌ ትገባና ሥራዋን ትሠራለች፤ ይሁን እንጂ እኔን በምታክምበት ጊዜ ምሬት እንደሚሰማት ዐይነት ትሆናለች::

ኪው ቲፕስ የተባለ ቀዳዳዎቹን የማጽጃ ዕቃ እንዲጠቀሙና ለእያንዳንዱ ቀዳዳ አዳዲስ ኪው ቲፕስ እንዲጠቀሙ ትእዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር:: ነርሷ ታክመኝ በነበረ ጊዜ ለእያንዳንዱ ቀዳዳ አዳዲስ ኪው ቲፕስ እንዳልተጠቀመች አስታውሳለሁ:: እንዲህ ያደረገችበት ምክንያት ምናልባትም አዲስ ኪው ቲፕስ ለማምጣት ጊዜ የሚወስድባት በመሆኑ ይሆናል:: ቀዳዳው ከመመረዙ በፊት እንዲህ ዐይነት ችግር ይከሰታል ብዬ አላሰብኩም ነበር:: በእርሷ ስንፍና ምክንያት ለተጨማሪ ስቃይ ተዳረግኩ:: የሰውነቴን መመረዝና የትኩሳቴ መጠን መጨመሩን ካወቁ በኋላ፤ ማንም ወደማይደርስበት ወደተለየ ክፍል ፈጥነው ወሰዱኝ፤ በዚያም ለሁለት ሳምንታት ቆይቻለሁ:: እዚያ በነበርኩበት ጊዜ ማንም ሰው እንዲጎበኘኝ አይፈቀድም ነበር::

ኢቫ አቤቱታ አቀረበች፤ የሆነውንም ለዶክተሮቹ ነገረቻቸው:: ከዚያ በኋላ ያችን ነርስ አላየኋትም፤ ከሥራ ያሰናብቷት ወይም ወደ ሌላ ክፍል ያዘዋውሯት አላውቅም::

ታሪኬን በአደባባይ መናገር ያስደስተኛል፤ በጥቂት አጋጣሚዎች ግን ከመጠን በላይ ሃሴት ለማድረግ ችያለሁ:: ከእነዚህ አንዱ በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ያደረግኩት ንግግር ነበር:: በዚያ ጉባኤ እኔና ባለቤቴ የተገኘን ሲሆን፤ ኮሌጁ ከሦስቱ ልጆቻችን ሁለቱ የሚማሩበትም ስፍራ ነበር::

በተደጋጋሚ ካገለገልኩባቸው በኮሌጅ ውስጥ ካሉ ድርጅቶች አንዱ የባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት (ቢ.ሲ. ኤም) ነው:: ኒኮል በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበረችበትና በአንድ ቡድን ውስጥም መሪ ሆና ታገለግል በነበረበት ጊዜ፤ የባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ንግግር እንዳደረግ ጋበዘኝ:: ኒኮል ከጉባኤው ተሳታፊዎች አንዷ መሆኗን ማወቁ፤ ጊዜውን እጅግ የደስታ አደረገልኝ::

የባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ከሚያዘጋጃቸው በርካታ የኮሌጅ እንቅስቃሴዎች መካከል የማክሰኞ ምሽት የምስጋናና የአምልኮ አገልግሎት ይገኝበታል:: ኮሚቴው የጋበዘኝ ስለደረሰብኝ አደጋ ንግግር እንዳደርግ ነው::

ተማሪዎቹ በግቢያቸው ውስጥ፤ "የሞተው ሰው ሲናገር" በሚል ርዕስ ስለማደርገው ንግግር ማስታወቂያ አሰራጩ:: የተገኙት ሰዎች ቁጥር ብዛት ስለነበረው ስብሰባው በሁለት ጊዜያት ተከፍሎ እንዲደረግ ነበር የታቀደው:: እየተናገርኩ አድማጮቹ በሞተውና ወደ ሕይወት



በተመለሰው ሰው ታሪክ በፍጹም የተማረኩ ይመስል ነበር:: ስለመንግሥተ ሰማይ ተናገርኩ፣ ስለተመለሰ ጸሎትና ስለተአምራቶቹም ጨመርኩ:: "በክርስቶስ ያለን ባልንጀርነት እንዴት ያለ ነው" የሚለውን ዝማሬ ከዲክ ዋንሪከር ጋር በመኪናው ውስጥ እንደዘመርነው ተናገርኩ::

እያንዳንዱ አገልግሎት በተፈጸመ ጊዜ የምስጋናው ዝማሬ ቡድን ከታሪኬ ጋር የተያያዘ ዝማሬ በማቅረብ ይመሩን ነበር:: እንደዚያ እንደሚያደርጉ አላወቅኩም' ነበር:: እንዲያደርጉ የተመሩት በመንፈስ እንደሆነ ግን ምንም ጥርጥር የለኝም:: "በክርስቶስ ያለን ባልንጀርነት እንዴት ያለ ነው" የሚለው ዝማሬ ለእኔ ለመስማትም ይሁን ለመዘመር አስቸጋሪ የሆነ ዝማሬ ነበር::

በመጨረሻው ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ተሰልፈው ነበር:: ከእነርሱም መካከል ዋልተር ፎስተር የተባለ አፍሪካ - አሜሪካዊ ተማሪ ይገኝበታል:: እርሱ ራሱ በርካታ ጥያቄዎችን ከጠየቀ በኋላ በዚያ ቆይቶ ሌሎች ተማሪዎች የሚጠይቋቸውን ጥያቄዎችም ያደምጥ ነበር:: መድረኩን ለቅቄ ስወርድ ዋልተር ከኋላዬ ተከተለኝ:: እኔ እጅግም ትኩረት ባልሰጠውም እርሱ ፍጹም ቁርጠኛ በሆነ ውሳኔ ይከተለኝ እንደነበር ተሰማኝ:: ነገሩ ሁሉ ስለመንግስተ ሰማይ ዝርዝር ጉዳዮች በበቂ ሁኔታ መረጃ ያላገኘ ወይም ስላለፍኩበት ሁኔታ በበቂ ስምቶ ያልጠገበ ይመስላል::

ከጥቂት ወራቶች በኋላ፤ ኒኮል ደወለችልኝ:: "ዋልተር ፎስተርን ታስታውሰዋለህ?" ስትል ጠየቀችኝ:: በድምጿ ውስጥ ሃዘን ነበር፤

ቀጥላም ማልቀስ ጀመረች:: ልክ ማስታወሴን ስነግራት፤ "ሞተኮ ... ሞተ፤ በልብ ድካም ህመም ሞተ! በቃ በዚያ ምክንያት ... ሄደ"

ዋልተር ከባድ በሆነ የልብ ድካም ህመምተኝነቱ በግልጽ የሚታወቅና በህክምና ክትትል ሥር የነበረ ተማሪ ነው:: በዚህ ምክንያት ሁሉም ሰው ጤንነቱ በደህና ሁኔታ እንደሚገኝ ይገምት ነበር:: የእርሱ ሞት የሚያውቁትን ተማሪዎች ሁሉ እጅግ ማስደንገጡ በግልጽ ታየ::

"የሃያ ዓመት ዕድሜ ያለው ተማሪ ይሞታል ተብሎ አይገመትም" ሲል ከጓደኞቹ መካከል አንደኛው ተናገረ::

ስልኩን ከዘጋሁ በኋላ እኔና ዋልተር ስለተገናኘንበት ቀን ወደ ኋላ ሄጄ ማሰብ ጀመርኩ:: ስለ ሞቱ ቀደም ያለ ስጋት ይኖረው ይሆን ስል እገረም ጀመር:: በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ውስጥ ባገለገልኩበት ጊዜ፤ ያን ያህል ጊዜ ይከተለኝ የነበረውና ስለ መንግስተ ሰማይ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ጥያቄዎች የጠየቀበት ምክንያት ያስገርመኝ ጀመር::

ጥያቄዎቹ በቀላሉ ከተገረመ ሰው ከሚወጡት ጥያቄዎች በላይ ትኩረት የነበራቸው ነበሩ:: ምናልባት በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ወደ ዘላለም ቤቱ ለሚያደርገው ጉዞ እያዘጋጀው ነበር ስል አሰብኩ:: ድንገተኛ የሆነው ሞቱ ጓደኞቹን ይልቁን ደግሞ በባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ውስጥ ይሳተፉ የነበሩትን ተማሪዎች ክፉኛ ስሜታቸውን ጎዳ:: አብሮ አደጋቸው በመሆኑ ምክንያት ተወዳጅ በነበረው ጓደኛቸው ሞት መሪር ሀዘን አዘኑ:: በሞቱ ማግስት ዋልተር በጣም ይወደው በነበረው በባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ህንጻ ውስጥ ተሰበሰቡ::



በዚያ ምሽት በነበረው ስሜት በፈነቀለው ስብሰባ፤ በርካታ ጓደኞቹ እየተነሱ ስለ መንግስተ ሰማይ ስላደረግኩት ንግግር ዋልተር እጅግ ክብደት ሰጥቶት የነበረ ንግግር እንደሆነ በሰፊው ተናገሩ:: ብዙዎችም ዋልተር በሰማው ነገር እጅግ መደሰቱን ገልጾላቸው እንደነበረ አስታውሰው ተናገሩ:: ከስብሰባው በኋላ በነበሩት ቀናት ስለዚያ ስብሰባ ደጋግሞ ይናገር ነበር::

"መጋቢ ፒፐር እዚህ ከመጡ በኋላ በቀን ውስጥ እጅግ ብዙ ጊዜ" አለ ከተማሪዎቹ መካከል አንዱ፤ "ዋልተር አንድ ቀን እኔ ራሴ ወደ መንግስተ ሰማይ እሄዳለሁ!" ሲል ነግሮኛል አለ::

በርካታ የቤተክርስቲያን ጉዳዮች ወጥረው ይዘውኝ ስለነበር፤ በባቶን ሮጅ በሚገኘው የመጀመሪያው የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ለዋልተር ሞት በተዘጋጀው የመታሰቢያ አገልግሎት ላይ ለመገኘት አልቻልኩም:: ኒኮል ቤተሰባችንን ወክላ የተገኘች ከመሆኑም በላይ በዚያ ምሽት ስለዋልተር ሕይወት በተደረገው የመታሰቢያ ስብሰባ ላይ የተከናወኑትን ነገሮች ሪፖርት አድርጋልናለች:: ከጓደኞቹ ቀርበው ከነበሩት ሁለት የተለዩ ጥያቄዎች አንደኛው ለባኪው የወንጌል መልዕክት እንዲያቀርብና አንድ ሰው አንድ የተለየ ዝማሬ እንዲዘምር ነበር:: እርግጥ ነው ዝማሬው፤ "በክርስቶስ ያለን ባልንጀርነት እንዴት ያለ ነው" የሚለው ዝማሬ ነበር:: በዚያ የነበሩ የስብሰባው ተካፋዮች ያ ዝማሬ በዋልተር ዘንድ ከፍተኛ ስፍራ የነበረው ዝማሬ እንደነበር ተነገራቸው::

በሉሲኒያ ግዛት ዩኒቨርስቲ ሙዚቃ የምታጠናውና የተዋጣላት ሶሎ ዘማሪ የሆነችው ኒኮል መዝሙሩን ለሃዘኑ ለተሰበሰቡ ሰዎች ዘመረችላቸው:: ዝማሬውን የተቀበሉት በታላቅ ሃዘንና በታላቅ ተስፋ

ነበር:: እንባዎች ይዘንቡ ነበር፤ የብዙዎችም ፊት ሰላም የተሞላ ፈገግታ አጥልቶበታል::

ስብሰባው ካበቃ በኋላ፤ ስለመንግስተ ሰማይ የነበረው የማይናወጥ እምነት ምን ያህል እንዳጽናናቸውና እንዳበረታታቸው ለመወያየት ወደ ኋላ ቀርተው ነበር::

ከእኔ ምስክርነትና ይህንንም ተከትሎ ከመጣው የዋልተር ሞት የወጣው ሌላው አስደሳች ነገር፤ በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ውስጥ በሚገኘው የባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ክልል ጸሎት የሚደረግበት የመናፈሻ ሥፍራ እንዲገነባ መደረጉ ነው:: እኔ ይህ ትክክለኛ ነገር ይመስለኛል፤ ምክንያቱም ታሪኬን ባካፈልኩባቸው ጊዜያቶች ሁሉ የጸሎትን ወሳኝ የሆነ አስፈላጊነት አበክሬ ገልጫለሁ:: ከሁሉም በላይ እኔም እኮ አሁን በሕይወት ያለሁት በተመለሰ ጸሎት አማካይነት ነው::

ከደረሰብኝ አደጋና ከመንግስተ ሰማይም ከተመለስኩ በኋላ መለኮታዊ በሆነ ጣልቃ ገብነት ሕይወታቸው ከእኔ ጋር እንደ ተያያዘ እጅግ ብዙ ሰዎች ሁሉ፤ እግዚአብሔር ለሁለተኛ ግዜ ወደ ቤቱ እስኪጠራኝ ድረስ ዋልተር እኔን የሚጠብቁትን ሁሉ የሚወክል ነው::

ሱ ፋይሌ የተባለች የመጀመሪያ ባሏ የሞተው በካንሰር በሽታ ነበር:: ለረዥም ጊዜያት ካለፈበት ከዚህ አስከፊ በሽታው የተነሳ እርሷ በብዙ ተጎድታ ነበር:: ቀሪ ሕይወቷንም መበለት ሆና እንደምትጨርሰው ገምታ ነበር:: ይሁን እንጂ ጎረቤቷና ያለ ትዳር የነበረው ቻርልስ ይህን ግምቷን ቀየረው:: ጎረቤታሞች ብቻ አልነበሩም፤ ይልቁንም ሁለቱም



የትዳር ጓደኞቻቸውን ያጡ በመሆናቸው ምክንያት ጥሩ ጓደኞችም እየሆኑ መጡ::

ጊዜው እያለፈ ሲሄድ፤ አንድ ጊዜ ሰዎችን ወደው የሚወዷቸውን እነዚያን ሰዎች ያጡ ብቻ ሊገነዘቡት በሚችሉበት ሁኔታ እንዳቸው የእንዳቸውን ፍላጎት ማሟላት መቻላቸውን ተገነዘቡ:: ጓደኝነታቸው ወደ ፍቅር በማምራቱ በአደገኛ ሁኔታ የጋብቻን ጉዳይ ማሰብ ጀመሩ::

ሱ ቻርልስን የማግባቱን ነገር ገደብ አበጅታለታለች፤ ምክንያቱም ቻርልስ አስቸጋሪና የማይመቹ የሥራተኛ መደብ አባላት ብላ ከምትጠራቸው ጎረቤቶቿ አንዱ ነው:: ሃይለኛ ጠጭ እንደነበር የሚነገር ታሪክ አለው፤ እናም እርሷ፤ "ከዚህ አይነት አመል ጋር አብሮ መኖር አልችልም" ትላለች::

ይሁን እንጂ ፍቅራቸው እየጨመረ ሲሄድ፤ ሱ ጋብቻውን ለመቀበል አንድ ቀላል ቅድመ ሁኔታ ብቻ አቀረበች፤ "ጠጪ የሆነ ሰው አላገባም::"

ቻርልስ ስካራምነቱን ብቻ አይደለም፤ መጠጡንም ቁርጥ አድርጎ ተወ:: አሁን ስለጋብቻ ለመነጋገር ዝግጅዎች ሆኑ::

አንድ ቀን ስለትዳር ጓደኞቻቸው ሞት መነጋገር ጀመሩ ሁለቱም የሞቱት በካንሰር በሽታ ነበር:: "እኔ ካንሰር እንዳለብኝ በህክምና ቢረጋገጥ" አለ፤ "ራሴን አጠፋለሁ::" ቻርልስ አንድ ነገር ያውቃል፤ በበሽታው የሚሰቃየው ታማሚው ብቻ ሳይሆን፤ ፍቅረኞቻቸውም ጥልቅ በሆነ ችግር ውስጥ ማለፋቸው ግድ ነው:: "እኔ ማንንም ቢሆን በዚያ አይነት ችግር ውስጥ አብሮኝ እንዲሰቃይ አልፈልግም::"

ተጋቡ፤ ጥሩ ትዳር ሆነላቸው፤ ቻርልስም ዳግመኛ መጠጥ አልጠጣም። ሱ ቀድሞውንም በቤተክርስቲያናችን ትጉህ ተሳታፊ ነች። ከጋብቻቸው በኋላ ግን ቻርልስም ንቁ ተሳታፊ ሆነ።

ይሁን እንጂ አንድ ቀን ካደረጋቸው የህክምና ምርመራዎች በአንዱ ከሁሉም በላይ የሚፈራው ነገር ተከሰተ፤ ቻርልስ ካንሰር አለበት። አሁን ወደ ውስጥ ጠልቆ ከገባ ፍርሃት ጋር መፋጠጥ ግድ ሆነበት። ሱ ካለፈው ባለቤቷ ጋር ያሳለፈችውን ስቃይ እንደገና ደግማ ልታልፍበት ነው በሚል ፍርሃት ተዋጠ።

የህክምና ምርመራውን ካደረገ በኋላ ሌላም ፍርሃት ከፊቱ ተጋርጦ ነበር፤ ይህ ክፉ ዜና ሞራሉንም ተገዳድሮታል፤ በመሆኑም ሞቴ እጅግ አስፈርቶኛል ሲል ተናገረ። ምንም እንኳን ቻርልስ የቤተክርስቲያን አባል የሆነና እንደሚያምን የሚናገር ቢሆንም፤ ደህንነታቸውን ከሚጠራጠሩ ሰዎች አንዱ ነው። ቻርልስ ከዚህ በሽታ ነፃ ወጥቶ እስከታየው ድረስ ሱ የታቻላትን ሁሉ እንደምታደርግ አረጋገጠችለት። ያሳሰባት ሌላው ነገር ግን ስለድነቱ እርግጠኝነት የማጣቱ ጉዳይ ነው። በተለያዩ ጊዜያቶች ስለመንግስተ ሰማይ የሰጠኋቸውን ምስክርነቶች አዳምጣለች፤ እንዲያውም የእኔን ታሪክ ለሌሎች ሰዎችም ደግማ ተናግራዋለች።

"ቻርልስን ልታነጋግረው ትችላለህ?" ስትል ጠየቀችኝ "አንድ ቀን ምስክርነትህን ከራስህ መስማት ይፈልጋል።"

በዚያ ጊዜ አሁን ባለሁበት ስፍራ ማለትም በፓሳድና የምትገኘው የመጀመሪያዋ የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን የእዋቂዎች ብቸኛው



መጋቢ ሆኜ ነበር። እኔና ሱ በተለያዩ አጋጣሚዎች በተወሰኑ ፕሮጀክቶች ላይ አብረን ሠርተናል።

"እባክህ ድነትን በሚመለከት አነጋግረው፤ ይሁን እንጂ ጨምረህ ከምድራዊው ሕይወት ፍጻሜ በኋላ ሕይወት ምን እንደሚመስል አስረዳው" አለችኝ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ቻርልስን አውቀዋለሁ፤ ካለፈ ሕይወቱ አስከፊነት የተነሣ ለእግዚአብሔር ጥሩ ሰው እንዳልሆነለት ያስብ እንደነበር እጠረጥራለሁ።

እኔና ቻርልስ ወዲያውኑ ቀጠሮ ያዝን። በጣም ጥሩ ሰውና ፈጥኖ ለመግባባትም ቀላል የሆነ ነው። መደበኛ በሆኑ ቀላል ጉዳዮች ከእርሱ ጋር መነጋገር እንደምፈልግ አመካኘቼ ነበር ቀጠሮ የምይዘው። ወደ ቤታቸው በምሄድበት ጊዜ ሁሉ ሱ ይቅርታ ጠይቃ ከክፍሉ ትወጣና ለመሄድ እስከምዘጋጅ ድረስ በዚያው ትቆያለች።

ምንም እንኳን የቻርልስ ጤንነት እያሽቆለቆለ ቢሄድም፤ እንዳችም አይነት የንዴት ወይም የድብርት ምልክት አላሳየም። በጣም ግላዊ የሆኑ ነገሮችን ለምሳሌም በአልጋ ላይ ሆኖ በመቀበያው እቃ ላይ ለመጸዳዳት፣ ሽንትን ለመሽናትና ለመታጠብም ቢሆን በሌሎች ላይ ለመተማመን በጣም አስቸጋሪ መሆኑንም እንኳን ተነጋግረናል።

በአራተኛው ጉብኝቴ ወቅት፤ ቻርልስ በመጨረሻው በግልጽ መናገር ጀመረ፤ "እኔ ፈርቻለሁ። ወደ መንግስተ ሰማይ መሄድ እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን ማረጋገጫ እሻለሁ በሞትኩ ጊዜ በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ እንደምሄድ ማረጋገጫ እፈልጋለሁ ..." አለ።

እርሱ ስለሕይወቱ እንደሚናገረው ከሆነ፤ ከእግዚአብሔር ጋር አሁን ያለው ግንኙነት በግልጽ እውነተኝነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እንደሚያጋጥመው ሱን ከማግባቱ አስቀድሞ ለብዙ ዓመታት፤ የክርስቶስ ታማኝ የሆነ ተከታይ አልነበረም፡፡ እየደጋገምኩ መንግስተ ሰማይ የሁሉም አማኞች የመጨረሻ ቤት መሆኗን የሚገልፁትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንዲያስታውስ አደረግኩ፡፡

"አውቃለሁ፤ አውቃለሁ" አለ፡፡ "ድነትን ከማግኘቴ በፊት ወደ መንግስተ ሰማይ እንደማልሄድ አውቅ ነበር፡፡ ወደ ሲኦል እየሄድኩ ነበር፡፡ አሁን ስለ መንግስተ ሰማይ እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ፡፡"

ስለ መንግስተ ሰማይ የሰጠሁት ስዕላዊ መግለጫ አጽናናው፡፡ "አዎ ... አዎ፤ የምፈልገው ይህንን ነው" አለ፡፡

በሌላው ጉብኝቴ ጊዜ፤ በጭውውታችን መካከል፤ "አሁን ተዘጋጅቻለሁ፡፡ አሁን ሰላም ይሰማኛል፡፡ በመጨረሻው ወደ መንግስተ ሰማይ እንደምሄድ አወቅኩ" አለ በፈገግታ፡፡

ለመጨረሻ ጊዜ ባደረኳቸው ሁለት ጉብኝቶች፤ ቻርልስ እንዲህ አለ፤ "እንደገና ንገረኝ፤ መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል አንድ ጊዜ ደግመህ ንገረኝ፡፡"

ምንም እንኳን የምነግረውን ነገር ሁሉ ሰምቶ የጨረሰው ቢሆንም እንደገና ደግሜ ነገርኩት፡፡ ስለ መንግስተ ሰማይ በነገርኩት ቁጥር እርግጠኝነቱ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ይመስል ነበር፡፡



ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ፤ ሱ ወደ ሃውስተን የክህምና ማዕከል ሆስፒታል ወስዳው ነበር፤ ያ ስፍራ እኔ ለረዥም ጊዜ ከተኛ ሁበት ክፍል ጥቂት በሮች ብቻ ነበር የሚርቀው፡፡

በምድር ላይ በኖረባት የመጨረሻዋ ቀን፤ ቻርልስ ለሱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "ሁሉም ነገር ጥሩ ይሆናል፤ አንድ ቀን እንደገና አብረን እንሆናለን፡፡ "

ሱ ስልክ ደውላ ስትነግረኝ፤ "ሲሞት ፈጽሞ ፍርሃት አይታይበትም ነበር" ስትል ሁኔታውን ገልጻልኛለች፡፡

የቻርልስ የተረጋጋ እርግጠኝነትና ነገሮችን አምኖ መቀበል፤ ከሃዘኗና እርሱን በማጣቷ ከደረሰባት ጉዳት ፈጥና እንድትወጣ ለሳምን ሰጣት፡፡ እርሷ እንደነገረችኝ፤ ከመሞቱ አንድ ሳምንት ብቻ ቀደም ብሎ፣ የእኔን ታሪክ ማድመጡና በሕይወቱ ያየው አምንታዊ የሆነ ብሩህ ገጽታ ልዮነቱን እንደፈጠረ ነግሯታል፡፡ አሁን ሁሉም ነገር ተረጋግቷል አለ፡፡ ወደ ተሻለ ስፍራ እንደምሄድ አውቃለሁ፡፡"

ሱ ስለቻርልስ የነበራትን ትውስታ ስታጫውተኝ፤ እየሳቀች እንዲህ አለች፤ "እኔ በጣም እድለኛ ሴት አይደለሁምን? በላይ እኮ ሁለት ሰዎች ይጠባበቁኛል፡፡ አንድ ቀን የእኔ ጊዜ ሲመጣ፤ እያንዳንዳቸው አንዳንድ እጆቼን ይይዛሉ፤ የቀድሞው ባለቤቴም በጌታ ወንድም ነበር፡፡ እናም በወርቁ ጎዳና ላይ ቁልቁለቱን እያዘገሙ ይሸኙኛል፡፡ "

ከልጆቻችን አንዱ የሆነው ጆይ ዕድሜው ወደ ወጣትነት በደረሰ ጊዜ፤ አንድ የሠራች መኪና ልንገዛለት ፈለግን፡፡ እርሱ የፈለገው የዕቃ

መጫኛ ያላት መኪና በመሆኑ፤ የፈለጋትን አይነት እስክናገኝ ድረስ አፈላለግን፤ በመጨረሻውም የ1993 ፎርድ ሬንጀር አገኘንስት::

የመኪና ነጋዴው ስም ጋሪ ኢሞንስ ይባላል፤ በእኛ አካባቢ በዚህ ሥራው ለረዥም ጊዜ የታወቀ ነው:: ጆይ የፈለጋትን መኪና ለመግዛት ከወሰንን በኋላ፤ ዋጋውን ለመነጋገር ወደ ውስጥ ገባን:: ሚስተር ኢሞንስ ጥሩ ዋጋ ሰጡን፤ በመሆኑም ጆይ መኪናዋን ገዛት::

በዚህ አጋጣሚ ምክንያት በሚስተር ኢሞንስና በእኔ ቤተሰብ መካከል ጥሩ ግንኙነት ተመሠረተ:: ከዚያ በኋላ ከእርሳቸው ላይ ተጨማሪ ሦስት ወይም አራት መኪናዎች ገዝተናል::

ጋሪ በእኔ ላይ ስለደረሰው ነገር በጥቂቱ ያውቃሉ፤ ይሁን እንጂ ዝርዝር ነገሮችን አያውቁም:: እኝህ ሰው ከመኪና ነጋዴነታቸው በተጨማሪ የመኪና ተወዳዳሪም ናቸው:: በእኔ ታሪክ በጣም የተማረኩም ይመስላሉ:: ሙሉውን ታሪክ ለመስማት እንደሚፈልጉ ነግረውኛል፤ ይሁን እንጂ እርሳቸው በሥራ ብዛት ይጠመዳሉ ወይም እኔ በአጣዳፊ ሥራ እሯሯጣለሁ::

አንድ ቀን ጆይ ገንዘብ ለመክፈል ወደ መኪና መሸጫው ድርጅት ይሄዳል:: ጋሪ እጃቸውን እየወዘወዙ ሰላምታ ከሰጡት በኋላ፤ "ይህን ብነግርህ ጭራሽ አታምንም" አሉ በፈገግታ:: "ትላንትና አስደናቂ ነገር ተከሰተ::"

"ምን"

"ገና ገዝተን ያስገባናትን መኪና እየፈተሽኩ ነበር:: ሁልጊዜም የማደርገውን ነገር ለማድረግ ወደ መኪናዋ ውስጥ ገባሁ:: ሁሉም ነገሮች በአግባቡ መሥራታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ቁልፎችን



መነካካቴን ቀጠልኩ የመኪናው ሞተር ችግር ያለው መሆኑን ለማየት የሞተሩን ድምጽ አዳመጥኩ፤ የአየር ማቀዝቀዣውን ተመለከትኩ፤ በመጨረሻም ሬዲዮው መሥራቱን ሞከርኩ:: ድንገት በቴፕ ሪከርደሩ ውስጥ ካሴት መኖሩን አየሁ:: የማፈናጠሪያ ቁልፍን ተጭኜ ካሴቱን አወጣሁት::"

ንግግራቸውን ቆም አድርገው ፈገግ ሉ፤ "በቴፑ ውስጥ ይናገር የነበረው ሰው ማን እንደሆነ እስኪ ገምት"

"ይህን መገመት አልችልም" አለ ጆይ::

"የአባትህ ታሪክ ነበር:: መኪናዋን የገዛናት በይፋ ጨረታ ነበር፤ በመሆኑም የቴፕ ክሩን መልሰን ለመስጠት ባለቤት አልነበረውም:: ቴፑን ወስጄ አዳመጥኩት ታሪኩን አዳምጥ በነበረበት ጊዜ ሁሉ እሰላሰል የነበረው አንድ ቃል ነበር የሚደንቅ ነው! የሚል"

ዘወር ብዬ ሁኔታውን ሳስበው፤ የሚደንቅ ነው:: ጋሪ ታሪኬን ለመስማት ይፈልጉ ነበር፤ ይሁን እንጂ ተገናኝተን መነጋገር አልቻልንም::

"በሽህ ከሚቆጠሩ ለጨረታ ከቀረቡ መኪናዎች ውስጥ ይህችን መኪና መግዛቴ እንግዳ ነገር አይደለምን?" ሲሉ ጋሪ ጆይን ጠየቁት፤ ከዚያ በኋላ በመኪናው ውስጥ እንደተቀመጥኩ፤ የማጫወቻውን ቁልፍ ተጭኜ አባትህ የሚናገረውን ሁሉ ሰማሁ::

ከዚያ በኋላ ባሉት ቀናት፤ ጋሪ ላገኟቸው ሰዎች ሁሉ በእኔ ላይ ስለደረሰው አደጋ ሳይናገሩ እንዳልቀሩ እስባለሁ::

እርግጥ ነው በዚያ ምስክርነት ተደስቻለሁ:: ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር የእኔን ታሪክ ስለተጠቀመባቸው መንገዶች ሌሎች ታሪኮችን ሰምቻለሁ::

በቤተክርስቲያኔ ውስጥ በምሰብክበት ጊዜ በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታም በመተረክ በቴፕ ቀድቼ እንዲባዛ አድርጌው ነበር:: በሺህ የሚቆጠሩ ቅጅዎችን ሳላሰራጭ አልቀረሁም:: በተጨማሪም ሰዎች እነዚያን የቴፕ ክሮች እያባዙ ለቤተሰቦቻቸው እንደሚሰጡ አውቃለሁ:: በአንድ ወር ጊዜ ውስጥም እስከ ሃያ ቅጅዎች ያዘዙ ሰዎችንም አውቃለሁ::

ያ የምስክርነቴን ታሪክ የያዘ ቴፕ እስከ አሁንም ድረስ እየተባዛ በመከፋፈል ላይ ይገኛል:: እጅግ ብዙ ሰዎች ታሪኬን ካደመጡ በኋላ ክሩን በማባዛት አካል ጉዳት ለደረሰባቸውና በስቃይ ላይ ላሉ ሰዎች እንዲሁም በሚወዷቸው ሰዎች ምክንያት በብርቱ ሃዘን ላይ ላሉ ሰዎች ይሰጧቸዋል::

እግዚአብሔር ጋሪ ኢሞንስ ያንን ቴፕ እንዲያደምጥ የፈለገበት ምክንያት አለው ብዬ ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ በርግጥ ምክንያት እንዳለው እርግጠኛ ነኝ::

አንድ ቀን ፓሳድና የመጀመሪያው የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን የመተላለፊያ ኮሪደር ላይ በመጓዝ ላይ ሳለሁ፣ አንዲት ሴት አስቆመችኝ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ያ ደግሞ የተለመደ አልነበረም:: ባለቤቴ እያንዳንዱ ሰው ወንድ ይሁን ሴት እኔን የሚጠይቀው ወይም ለእኔ የሚነግረው አንዳች ነገር የማያጣ በመሆኑ "ስድስት ሜትር



ለመጓዝ ሰላሳ ደቂቃ ይፈጅብሃል" እያለች ትቀልዳለች:: እኛ ያሉን አስር ሺህ ያህል አባላት ናቸው፣ እያንዳንዱን ሰው ለማነጋገር ብዛቱ አስቸጋሪ ነው::

"ኦ! መጋቢ ፒፐር፣ ወደዚህ የመጣሁት አንተን ለማግኘት ነው:: አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ:: አንተ መስማት ያለብህ ነገር እንደሆነ አስባለሁ::"

አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ነገሩን ከጀመረ፣ "ለራስህ ጥቅም ነው" የሚል ቃል አብሮ ይጨምርበታል:: ብዙ ጊዜ እንዳስተዋልኩት ያ ነገር እኔ ልሰማው የሚያስፈልገኝ ነገር አይሆንም:: ብዙ ሰዎች ከእኔ ጋር ስለነበሩ ምን ብዬ እንደምመልስ አላወቅኩም ነበር:: ይሁን እንጂ ትኩር ብዬ ስመለከታት በፊቷ ላይ የሆነ አጣዳፊ ነገርና ውጥረት እንዳለ ስሜቷን ማንበብ ቻልኩ:: ወደ ሌሎቹ ሰዎች ዞወር አልኩና፣ አንድ ጊዜ ትፈቅዱልኛላችሁ? ስል ጠየቅኳቸው::

በርግጥም ፈቃደኞች ነበሩ::

"እኔ ፈቃድ ያለኝ ነርስ ነኝ፣ ምን እንደተፈጠረ ብነግርህ ልታምን አትችልም"

"በእኔ ሕይወት ብዙ የማይታመኑ ነገሮች ደርሰዋል:: ንገሪኝና ማመን አለማመኔን ሞክሪ:: "

"ይህ የሆነው በሆስፒታል ውስጥ ነው:: በጠና ታማ ሆስፒታል የገባች አንዲት ሴት የአንተን ቴፕ ለማዳመጥ ችላ ነበር፣ እናም ሕይወቷን ለወጠው::"

"እንዲህ ያሉ ነገሮችን አስቀድሜ ስምቻለሁ፤ አዳዲስ ታሪኮችን ለመስማት ግን ፈቃደኛ በመሆኔ፤ ሰፋ አድርገሽ ንገሪኝ አልኳት::"

"ሴትዮዋ አማኝ አልነበረችም፤ ይሁን እንጂ አንድ ሰው አምጥቶ የአንተን ቴፕ ክር እንድታዳምጠው ሰጣት:: ጓደኞቿ ስለ እግዚአብሔር ሊያነጋግሯት ሞክረው ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ፤ ብዙ ዓይነት መጻሕፍትና ትራክቶችን ጭምር ሰጥተዋታል፤ ነገር ግን አንዳቸውም አልበገሯትም:: ስለ እግዚአብሔር ጉዳይ፣ ስለሃይማኖትም ይሁን ስለ ድነት ነገር መነጋገር አልፈልግም ትላለች:: እስከ ሞት ድረስ ቀርባ የታመመች ቢሆንም፤ የዘላለም ሕይወትን በሚመለከት ለየትኛውም ዐይነት መልዕክት ውስጧ ክፍት አልነበረም::"

ከመቀጠሏ በፊት በዓይኖቿ ላይ የሚወርደውን እንባ ለማበስ ንግግሯን አቋረጠች:: "አንድ ሰው የቴፕ ክሩን አመጣላት፤ ያንን ስለ መንግስተ ሰማይ የሚናገረውን የቴፕ ክር ማለቴ ነው ማድመጥ ትፈልግ እንደሆነም ጠየቃት:: ያ ጓደኛዋ ምንም አይነት ተጽእኖ አላደረገባትም፤ በቃ ቀለል አድርጎ ምናልባት ጠቃሚ የሆነ ነገር በዚህ ውስጥ ታገኚ ይሆናል:: ታሪኩ የሚያወሰው ሞቶ ስለነበረ፣ ወደ መንግስተ ሰማይ ስለሄደና እንደገና ወደ ሕይወት ስለተመለሰ ሰው ነው" አላት::

ሴትየዋ በነገሩ ላይ አሰባበት ልታደምጠው እንደምትችል መግለጿን ነርሷ ነገረችኝ:: ጓደኛዋም ተሰናብቷት ሄደ:: የቴፕ ክሩ ሳይደመጥ ከአልጋዋ አጠገብ በነበረ መሰስተኛ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ቆየ:: ወዲያውኑ የጤንነቷ ጉዳይ ክፉኛ እያሽቆለቆለ ይሄድ ጀመር::



ዶክተሮቿ የሴትየዋን ልጅ ጠርተው እናቷ ከዚያ በኋላ በሕይወት ብትኖር ለአንድ ግፋ ቢልም ለሁለት ሳምንት እንደሆነ ነገሯት::

አማኝ የሆነችው ልጇ የእኔን ክር እናቷ እንድታዳምጠው አጥብቃ ትፈልግ ነበር:: የቴፕ ክሩ የያዘው ሁለት መልዕክቶችን ነው:: የመጀመሪያው ክፍል እኔ በሕይወት እኖር ዘንድ ስለአስቻለኝ ተአምርና ስለተመለሰው ጸሎት የሚያወሳ ሲሆን ይህንኑ ታሪክ በዚሁ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ላይ ጠቅሼዋለሁ:: ሁለተኛው ክፍል ደግሞ መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል ይተርካል:: እኔ፤ "የልብ ህመም ፈውስ" ስል ርዕስ ለጥቼዋለሁ:: ልጅቱ እናቷ እንድትሰማው የፈለገችውም ክፍል ይሄኛው ነበር::

ሴትዮዋ ግን መስማት ባለመፈለጓ ተቃወመች:: በዚህ የቴፕ ክር ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ መስማት አልፈልግም ስትል ተቃውሞዋን ገለጸች::

ቀናቶች እያለፉ ሄዱ፤ የአሮጊቷም ሁኔታ ወደ አስከፊ ሁኔታ ተሸጋገረ:: ከእኔ ጋር የምትነጋገረውና ክርስቲያን የሆነችው ነርስ፤ በዚያ እየሆነ ያለውን ነገር ተገነዘበች:: ከልጅቱ ጋር ከተነጋገረች በኋላ፤ ነርሷ በሽተኛዋን ስለ ሕይወቷ ጉዳይ ራሷ ልታነጋግራት ወሰነች:: ከዚህ ቀደም እንዲህ አድርጋ አታውቅም::

እንደ ምክንያት አድርጋ የወሰደችው፤ አንዳንድ ጊዜ ከቤተሰብ አባላት ይልቅ አሉታዊ የሆነ ምስክርነት ለመስጠት እንግዳ ለሆነ ወይም በመጠኑ ብቻ ለሚያውቁት ሰው ይቀላል የሚል ግምት ነው::

የሥራ ጊዜዋን ከጨረሰች በኋላ፤ ነርሷ ወደ ሴትየዋ ክፍል ሄዳ፤ "አጠገብሽ ተቀምጬ ጥቂት ጊዜ ላጫውትሽ እችላለሁ?" ስትል ጠየቀቻት::

በመሞት ላይ ያለችው ሴት ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች:: በፍጹም ትህትናና በታላቅ ጥንቃቄ ስለ እምነትና ስለ እግዚአብሔር ሰላም እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ በእራሷ ሕይወት ስላመጣው ታላቅ ለውጥ ተረከችላት::

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ሴትየዋ አንዳች ቃል አልተነፈሰችም:: ነርሷ፤ "ይህንን የቴፕ ክር አድምጬዋለሁ፤ አንቺም ልታውቂው የሚገባ ነገር በውስጡ እንዳለ አስባለሁ፤ የቴፕ ክሩን ማድመጥ ትፈልጊያለሽን?" ስትል ጠየቀቻት::

አሮጊቷ ሴት ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች፤ ስለዚህም ነርሷ ቴፑን ከፈታችላትና ሄደች::

በሚቀጥለው ቀን በሞት መንገድ ላይ ያለችው ሴት ለልጇና ለነርሷ ቴፑን እንዳደመጠችው ከነገረቻቸው በኋላ፤ "በጣም አስደሳች ሆኖ አግኝቼዋለሁ አሁን ክርስቲያን ስለመሆን ጉዳይ አጥብቄ አስቤበታለሁ" አለች::

ምንም እንኳን ልጅቷና ነርሷ በዚህ ነገር እጅግ ቢደሰቱም ከዚያ በላይ ሄደው ምንም ነገር አልጠየቋትም:: ከሁለት ቀን በኋላ ሴትየዋ፤ "እኔ አሁን አማኝ ሆኛለሁ" ስትል ተናገረች:: ይህንን በመጀመሪያ የተናገረችው ለልጇ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ ለነርሷ ነበር:: ከዚያ በኋላ ማንም ሊጠይቃት ወደ ክፍሏ ይምጣ፤ "እኔ ክርስቲያን ሆኛለሁ:: ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኜ አድርጌ ተቀብያለሁ፤ እናም ወደ መንግስተ ሰማይ እሄዳለሁ እያለች" ትነግረዋለች::



ሴትዬዋ በግልጽ ለሌሎች መለወጧን ከተናገረች ከጥቂት ሰዓታት በኋላ የጤንነቷ ጉዳይ ከፊቱ ይልቅ እያሽቆለቆለ ሄደ:: ቀይቶም ህሊናዋን ሳተች:: በሚቀጥለው ቀን ነርሷ ወደ ሥራ ገበታዋ ስትገባ፤ አሮጊቷ ሴት ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት መሞቷን ሰማች::

ነርሷ ይህንን ሁሉ ከነገረችኝ በኋላ፤ "ሴትዬዋ እየሞተች በነበረችበት ጊዜ የሆነውን ነገር ማመን አትችልም" አለች::

ጥያቄ ከመጠየቁ በፊት ነርሷ እንዲህ አለች፤ "ቴፕ ሪከርደሩ በአልጋው ላይ አጠገቧ ተቀምጦ ነበር:: ልጇ አንተ መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል የገለጽከበትን ሁለተኛውን የቴፑን ክፍል ከፈተችላት:: ሕይወቷ እየተወሰደ በነበረበት ጊዜ መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል የተረከውን ገለጻ እያዳመጠች ነበር:: ከዚህ ምድር ከመሰናበቷና በመንግስተ ሰማይ እግዚአብሔርን ከማግኘቷ በፊት የሰማችው የመጨረሻ ነገር መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል ነው::"

ስሜቴን ለመቆጣጠር ብታገልም፤ እንባ ከዓይኔ ጠርዞች ላይ መፍለቅ ጀመረ::

"ይህንን ማወቅ እንዳለብህ ስላሰብኩ ነው::"

"አዎ" አልኳት:: "ስለነገርሽኝ አመሰግናለሁ:: ያ ለእኔ ትልቅ መጽናናት ነው::"

ነርሷ ከእኔ ጋር ለነበሩት ሰዎች ታሪኩን ደግማ ስትናገር ወደ ምድር መልሶ ስላመጣኝ እግዚአብሔርን አመሰገንኩ:: "አ! እግዚአብሔር ሆይ እዚህ ያለሁበትን ዐላማ አንዳንድ ምክንያቶች አውቄአለሁ:: ይህንን ታሪክ እሰማ ዘንድ ስለፈቀድክልኝ አመሰግንሃለሁ::"

አንድ ጊዜ በሃውስተን በምትገኘው በቾክላት ባዮ መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ሰብኬ ነበር:: የጋበዙኝም የሞቴንና በመንግስተ ሰማይ የመገኘቴን ተሞክሮ እንዳካፍላቸው ነበር::

ከመድረኩ በታች ሆኜ ሃሳቤን ሰብስብ አድርጌ በመጠባበቅ ላይ ነበርኩ:: በተለይ የመጥምቃውያን አብያተክርስቲያናት፤ ተጋባዥ እንግዳ ወደ መድረኩ ከመውጣቱ በፊት በነጠላ የሚዘምር ዘማሪ ወይም የተለየ ሙዚቃ የማቅረብ ልምድ አላቸው:: አገልግሎቱ ሲጀመር ያልነበረች በምን እርዕስ ላይ ቃል እንደማቀርብም የማታውቅ አንዲት ሴት በስተጉን ባለ በር በኩል አልፋ ለመዘመር ወደ መድረኩ ወጣች::

እጅግ ማራኪ የሆነ ድምጽ ነው ያላት፤ የዘመረችው የኢየሱስን እግር በእንባዋ ያጠበችው ሴት ስለሰበረችው የአልባስጥሮስ ሽቱ ብልቃት ሲሆን፤ የዝማሬው መጠሪያ "ተሰብሮ መፍሰስ" የሚል ነበር::

አገልግሎቷን ጨርሳ እንደተቀመጠች፤ እኔ ደግሞ ተነስቼ ስለደረሰብኝ አደጋ መናገር ጀመርኩ:: በእርሷ ዝማሬና በእኔ መልዕክት መካከል አንዳችም ግንኙነት እንዲኖር አላደረግኩም፤ ይሁን እንጂ በርካታ ሰዎች ጥሩ ባልሆነ ስሜት ወደርሷ ሲመለከቱ አስተዋልኩ::



አገልግሎቱ ካበቃ በኋላ፤ አንድ ሰው ዘማሪዋን፤ "ዶን ንግግር ከማድረጉ በፊት፤ 'ተሰብሮ መፍሰስ' የሚለውን ዝማሬ መዘመርሽ አስደሳች ነው" ብሎ ሲናገራት ሰማሁ:: አስደሳች የሚለውን ቃል ሲናገር የነበረው ስሜት ባዶ ነበር::

"አ!" አለች ዘማሪዋ በፊቷ ላይ ካየሁት ድንጋጤ ልናገርበት የነበረውን ሃሳብ አስቀድማ እንደማታውቅ ተገነዘብኩ:: እውነቱን ለመናገር፤ እርሷም ብትሆን ዝማሬዋና የእኔ ምስክርነት ግንኙነት እንዲኖረው አላደረገችም:: ዓይኖቻችን ተገጣጠሙ፤ እናም ማልቀስ ጀመረች፤ "በጣም አዝናለሁ ... አዝናለሁ::"

ጥሩ እኮ ነው" አልኳት:: "በእውነት በጣም ጥሩ ነበር" አልኳትና ወደ እርሷ መራመዴን ቀጠልኩ፤፤

"ተሰብሮ መፍሰስ" አለ አንድ ሰው:: "ይሄ እኮ የሆነው በአንተ ላይ ነው፤ አይደለም እንዴ?" ቢያንስ ቢያንስ ደርዘን የሚሞሉ ሰዎች ተመሳሳይ አስተያየት ሰንዝረዋል:: አንዳንዶች ደግሞ እኛ በተለይ ይህንን መዝሙር እንድትዘምር ሆን ብለን ያደረግነው እንደሆነ ገምተዋል::

ቆም አልኩና ወደ ኋላዬ ተመለከትኩ:: ዘማሪዋ ከፒያኖው አጠገብ ቆማ ታለቅሳለች:: ራሴን ይቅርታ ጠይቄ ወደ እርሷ ተመልሼ ሄድኩ:: "በመጽሐፍ ቅዱስ ከተከናወኑት አስደናቂ ታሪኮች አንዱን የሚዘክር አስደናቂ ዝማሬ ነው የዘመርሽው እኔ ልናገርበት የነበረውን ጉዳይ አንቺ አላወቅሽም ነበር፤ ነገር ግን ጥሩ ዝማሬ ነበር፤ ምክንያቱም ከዚህ የተሻለ ዝማሬ እንደሚኖር አላስብም::"

ይቅርታን ለመጠየቅ በደስታ ተሞልታ ፈገግ አለች::

"በጣም ጥሩ ዝማሬ ነው፤ ጥሩ ነበር" ስል አረጋገጥኩላት።

አልፌአት እየሄድኩ ሳለ፤ ምናልባትም እኔ ተሰብሬ የፈሰስኩ ነኝ ስል አሰብኩ። ነገር ግን ወዲያው ደግሞ በሌላ ሃሳብ ፈገግ አልኩ፤ እንደገና ከስብራቴ ተጠግኜ ወደ ስፍራዬ ተመልሻለሁ።



# 16

# ዓላማን ማወቅ

"ይህንን ተረድቼ በእናንተ ዘንድ እንደገና ስለመሆኔ በእኔ መመካታችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ይበዛ ዘንድ በእምነት ታድጉና ደስ ይላችሁ ዘንድ እንድኖር ከሁላችሁም ጋር እንድቆይ አውቃለሁ"

ፊል 1፥25-27

በሃውስተን የፓሳድና ክፍለ ከተማ ፖሊስ የሆነው ብራድ ቱርፒን በአደጋ ምክንያት እግሩን ሊያጣ ምንም ያህል አልቀረውም ነበር። የሚያሽከረክራት ሞተር ብስክሌት ከአንድ የጭነት መኪና የጀርባ ክፍል ጋር ተጋጨች። የህክምና ባለሙያዎች ፈጥነው በመድረስ ደሙ እንዳይፈስ ባያደርጉ ኖሮ በዚያው ስፍራ ደሙ ፈሶ ያልቅ ነበር።

ሶኒ ስቲድ የተባሉት በቤተክርስቲያናችን የቀድሞ የትምህርት አገልግሎት ሠራተኛ ደግሞ ብራድን በግል ያውቁት ስለነበር ሄጄ እንዳየው ጠየቁኝ። "በርግጥ ሄጄ አየዋለሁ" አልኩ፤ በተለይ ደግሞ ያ የእግር አጥንት ማፅኛ መሣሪያ እንደተደረገለት ከሰማሁ በኋላ መሄዴ አይቀሬ ሆነ። ደወልኩና ሊያነጋግረኝ እንደሚችል ፈቃድ ጠየኩት። ለምን እንደሆን ባላውቅም ከመሄዴ በፊት በእኔ ላይ የደረሰውን አደጋና ከዚያ በኋላም የሆነውን ማገገሜን የሚያሳዩ ፎቶግራፎቼን ይዤ ሄድኩ።

ሶኒ በመኪናቸው ወደ ፖሊሱ ቤት ወሰዱኝ። ወደ ውስጥ ከገባን በኋላ ያየሁት ነገር ልክ የእኔ ቤት ለወራቶች ያህል የነበረበትን ሁኔታ

ዓይነት ነው:: ብራድ የመደገፊያ የብረት ዘንግ በተዘረጋበት የሆስፒታል አልጋ ላይ ተኝቷል:: በእግሩ ላይ የተደረገለት መሣሪያ ለእኔ ተደርጎ ከነበረው ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ይሁን እንጂ ልክ የእኔ ዐይነት አልነበረም፤ ምክንያቱም ከእኔ አደጋ በኋላ በነበሩት ደርዘን በሚሞሉ ዓመታት ውስጥ ቴክኖሎጂው መሣሪያውን አሻሽሎታል::

ሌሎች ሰዎች በክፍሉ ውስጥ በመኖራቸው ተቀመጥኩና በሌሎች ጉዳዮች ላይ አብሬአቸው ጨዋታ ጀመርኩ:: በደህና ሁኔታ ላይ ነው ያለው፤ ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች ይጎበኙት ስለነበር በጠያቂዎች ምክንያት እንደሚሰላች አውቄአለሁ:: ልክ የመጨረሻው ሰው ክፍሉን ለቆ እንደወጣ፤ "ከሰዎች ጋር መነጋገር አሰልችቶሃል፤ አይደለም?" ስል ጠየኩት::

ብራድ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ::

"አውቃለሁ:: በዚህ ለፍራ ተኝተህ ልክ እንደ ኢግዚቢሸን እንደሆንክ እንደሚሰማህ አውቃለሁ:: ስልኩ መጮሁን አያቆምም:: እያንዳንዱ ሰው አንተን መጥቶ ማየት ይፈልጋል::"

እንደገና ራሱን ነቀነቀ፤ "በመምጣታቸው ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ጥቂት ሰላምና እፎይታ እፈልጋለሁ::"

"መጥቼ ከእረፍትህ ስላናጠብኩህ ይቅርታ እጠይቃለሁ፤ ነገር ግን ወደዚህ አንተን እንዳይ ያመጣኝ ሶኒ ነው፤ ምክንያቱም ምን ማድረግ እንደሚጠበቅብህ ከአንተ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ:: በእግሩ ላይ ወደ ታሰረው ኤልዛሮቭ ፍሬም በጣቴ እየጠቆምኩ፡ እንደዚህ በእግርህ ላይ እንዳለው መሣሪያ ዐይነት እኔም አድርጌ ነበር" አልኩት::



"ኦ! አንተም አድርገህ ነበር?"

በእጄ የያዝኳቸውን ፎቶግራፎች አውጥቼ መሣሪያውን ካደረጉልኝ ቀን ጀምሮ የተነሱትን ፎቶዎች በቅደም ተከተል አሳየሁት:: እያንዳንዱን ፎቶ በትኩረት ይመለከት ጀመር ከዚያም እኔ ከእርሱ በባሰ ሁኔታ እንደነበርኩ አየ::

"እና ተሻለህ፤ አይደለም?"

"አዎ ተሽሎኛል፤ አንተም ደግሞ ይሻልሃል::"

"አንተ የተሻለህ በመሆኑ በጣም ጥሩ ነው፤ ነገር ግን እኔ እንዳንተ የሚሻለኝ አይመስለኝም:: ይሄ እግሬ እንደማይቆረጥ አንዳችም ዋስትና ሊሰጡኝ አልቻሉም:: ዶክተሮቹ በእኔ ነገር ጨለምተኞች ናቸው፤ እናም ይሄ ነው ነገሩን ያከበደብኝ::"

"ጥሩ ነው፤ እነርሱ እኮ እንዲሁ ናቸው" አልኩት በእነዚያ አስቸጋሪ ጊዜዎች የነበረኝን ስሜት ወደ ኋላ ሄጄ አጥብቄ እያስታወስኩ "በዚህ ረገድ ወግ አጥባቂ የመሆንን ስህተት ነው የሚፈጽሙት፤ ተስፋህ ፈጽሞ እንዳይንሰራራ ነው የሚያደርጉት:: ከዚህ በኋላ በወራት ውስጥ ይሄ በእግርህ ላይ ያለ መሣሪያና ሁሉም ነገር ጥሩ እንደሚሆን ያውቃሉ ነገር ግን የሚነግሩህ እግርህ ሊመረዝ የሚችልና ሊቆረጥም እንደሚችል አድርገው ነው::"

"እኔም ያልኩህ ይህንኑ ነው:: በዚህ ሁሉ ስቃይ ውስጥ ማለፊ ዋጋ እንዳለው ነገር አልቆጥረውም::"

"መልካም ዜና እያገገምክ ስትሄድ የህመም ስቃዩ እየቀነሰ መሄዱ ነው::"

ይህንን እየተጫዋወትን ሳለ ሚስቱ ወደ ክፍሉ እየገባች ስለ ነበር ንግግራችንን አዳምጣለች::

"ምንም ዐይነት መሻሻል ባለመኖሩ' በጣም አስልችቶኛል፤ ደግሞም ማንም ሰው ስለዚህ ነገርም ምንም አይነግረንም" አለች:: "እንዲያውም ዶክተሮችን ለመለወጥ በዝግጅት ላይ ነን::"

"የተሻለ ዶክተር ልታገኙ ትችላላችሁ" አልኳት፤ "ነገር ግን ጥቂት ቆዩ ትዕግስትም ይኑራችሁ:: እርግጠኛ ነኝ ዶክተራችሁ የሚቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው::"

ከዚያ በኋላም ፍጹም ተስፋ ቆርጬና ትዕግስቴ አልቆ ስለነበረበት ጊዜ አጫወትኳቸው::

"ዶክተሬ ሊጎበኘኝ በመጣ ጊዜ ንዴቴ ግሎ ነበር"

"ተቀመጥ" ስል ጭንቀት በሞላው ድምጽ ጮኹበት::

"ተቀመጠ፤ ከዚያ በኋላ ላሉት ቢያንስ አምስት ደቂቃዎች የተቸገርኩበትንና ተስፋ ያስቆረጠኝን ነገር አዘረዘረለት ጀመር:: ፊቱን ትክ ብዬ ስመለከት ስሜቱን እንደጎዳሁት ተገነዘብኩ:: በርግጥ ለራሱ እያሰብኩ አልነበረም:: ተጎድቼ ነበር፣ ስቃዩ ማቆሚያ አልነበረውም፣ መተኛት አልችልም፤ ለዚህ ሁሉ ደግሞ መልስ እፈልግ ነበር:: ነገሮችን ማወቅ ባለመቻሌ ስልችቶኛል:: አሁንም ምን ያህል ጊዜ ይህ ብረት በእግሬ ላይ እንደሚቆይ ጠይቄሃለሁ፤ ምናልባትም አንድ ወር ወይም ሁለትና ሦስት ወራት ነበር ያልከኝ ያልካቸው ወራቶች ካለፉ በኋላም እንኳን ያገኘሁት ለውጥ የለም:: ቀጣዩን ዙር አቤቱታዬን ለማቅረብ



እንደገና ንዴቴ እየገነፈለ ነበር:: ነገሬን ያጠቃለልኩት፤ ቀጥተኛ የሆነ መልስ ለምን አትሰጠኝም በማለት ነበር::"

"ራሱን ቁልቁል ጣል አደረገና፤ ማድረግ የምችለውን ሁሉ እያደረግኩ ነው:: እኔም መልሱን አላውቀውም:: የማልነግርህም ለዚህ ነው" አለኝ::

"እኔ አሁን የምፈልገው ..."

"የምትፈልገውን አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ ይህ እርግጠኛ የሆነ ሳይንስ አይደለም፡ መሣሪያውን እንደ ገና ነው የፈለሰፍነው:: በዚህ አቅጣጫ ብዙም ልምድ የለንም፤ ከዚህም በላይ ይህ ለእኛ አዲስ ቴክኖሎጂ ነው:: ማድረግ የምንችለውን ሁሉ እያደረግን ነው::"

ለዚያ አደጋ ለብራድና ለሚስቱ በነገርኳቸው ጊዜ፤ "እባካችሁ ለዶክተራችሁ ትዕግስት ይኑራችሁ:: የሌለውን መልስ ሊሰጣችሁ አይችልም:: ማድረግ የሚገባችሁን ነገር እንድታደርጉ ይነግራችኋል፤ የመድሃኒት ትዕዛዝ ወረቀት ያሸክማችኋል:: በበርካታ የህክምና ሂደቶች ውስጥ እንድታልፉ ያደርጋል፤ በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ውስጥ እንዴት ማለፍ እንደምትችሉ መማር አለባችሁ በሁሉም ውስጥ::"

"አዎ፤ አውቃለሁ" አለ:: ይሁን እንጂ ከዚህ በኋላ ስሜቴን ለመቆጣጠር አልችልም:: እኔ ፖሊስ ነኝ:: ብዙ ችግሮችን አይቻለሁ፤ በጣም መጥፎና አስቸጋሪ ሁኔታዎችን:: ውስጤ ስብርብር ብሎ ነው ያገኘሁት ማለቴ ስሜቴ ወድቋል:: የምለውን ታውቃለህ?"

"በትክክል:: ዝም ብለህ በመለባበርህ ቀጥል:: ነገሮቹ ሁሉ እንደገና ይስተካከላሉ::"

"ከቁጥጥር ውጭ እንደሆንኩ ይሰማኛል"

"አሁንም ከቁጥጥር ውጭ ነህ!"

ብራድ ትኩር ብሎ ተመለከተኝ::

"ነገሩን እስኪ አስበው፣ ልትቆጣጠረው የቻልከው ነገር ምንድነው? ምንም የለም::"

"ራሴን ማጽዳት እንኳን አልችልም"

"ትክክል ነው:: ሙሉ ለሙሉ ተስፋ ቢስ ነህ:: ልታደርገው ወይም ልትቆጣጠረው የምትችለው አንዳች ነገር የለም::"

"እንዲህ ከመሆኔ በፊት ክብደት አነሣና የሰውነት ማዳበሪያ እንቅስቃሴ አደርግ ነበር" አለ:: "ማመን ከሚያቅትህ በላይ ክብደትና ቅርጽ ነበረኝ"

"ስለዚያ ምንም ጥርጥር የለኝም::" አንድ ጊዜ ጥሩ ቅርጽና ጡንቻ እንደነበረው ማየት ችያለሁ:: አሁን ግን እነዚህ ነገሮች የሉህም:: አንድ ቀን ግን እንደ ቀድሞኑ ግዙፍ ሰውነት ይኖርሃል፤ ነገር ግን ተነስተህ ቀድሞ የምታደርጋቸውን ነገሮች ለማድረግ አለመቻልህ እንድትለወጥ ያደርግሃል:: ለመለወጥ ተዘጋጅ:: ክብደትህን ትቀንሳለህ፤ ጡንቻዎችህም ይላላሉ:: ቀድሞ ታደርገው እንደነበረው ሰውነትህን መቆጣጠር አትችልም::"

ሚስቱ በአዕምሮው ላይ የደረሰውን ዝለት ሁሉ በግልጽ በስሜቷ የተረዳች በመሆኑ ለማልቀስ እየተዘጋጀች ነበር:: "መጥፎ ስሜት ነው የሚሰማው፤ በራሱ በህክምናው እንኳን ደስተኛ አይደለም:: ምን ማድረግ እንደምችል አላውቅም::"

"ጥቂት ነገሮች ልጠቁምሽ እችላለሁ:: ከሁሉም በፊት፤ ለጎብኚዎችና ለምትቀበሏቸው የስልክ መልዕክቶች ቁጥር ወሰን አብጁ:: ማንም ሰው በፈለገ ጊዜ ሁሉ እንዲገባ አትፍቀዱ" አልኩ:: "ጠበቅ በሉ:: ሁሉም ሰው እንዲገባ የምትፈቅዱ ከሆነ እየተሰላቻችሁ ትመጣላችሁ፤ ከፊታችሁ ላይ መልካም ስሜት መነበቡን ያቆማል:: ጓደኞቻችሁም ይህንን ይረዱታል::"

እንደገናም ወደ ብራድ ዞወር አልኩና፤ "ሁሉንም ህክምናዎች ለማድረግ ራስህን አዘጋጅ:: ምክንያቱም አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ታደርጋቸው ዘንድ ከፊትህ ይጠብቁሃል:: እንድትራመድ የሚረዱህ እስከሆኑ ድረስ አድርጋቸው ትዕግስት ይኑርህ፤ ምክንያቱም ህክምናው የሚወስደው ረዥም ጊዜ ነው:: ምናልባትም ልነግርህ የምችለው እጅግ የተሻለው ነገር ብቸኛ እንደ ሆንክ እንዳታስብ ነው::" ለአጭር ጊዜ ንግግሬን አቋርጩ ፈገግ አልኩ፤ ምክንያቱም እኔ ራሴ እንዴት እንደነበርኩ አስታውሼ ነው:: "የት ስፍራ እንደተጎዳህ ለዎች እንዲያውቁ ፍቀድ፤ እንዴትስ ሊረዱህ እንደሚችሉ መንገድ ክፈት፤ በተለይም ለምታምናቸው ሰዎች አንዳንድ ነገሮችን ሊያደርጉልህ እንዲችሉ ችግሮችህን እንዲያውቁ አድርግ:: እንዲጸልዩልህ አድርግ:: ወደዚህ የሚመጡ እጅግ በርካታ መልካም ወገኖች ልታገኝ ትችላለህ፤ እነርሱም ኬክ፣ ኮካ ወይም ምግብ ሊያመጡልህ ወይም አንድ ነገር ሊያደርጉልህ ይፈልጋሉ:: ባልንጀርነታቸውንና ፍቅራቸውን እንዲገልጹልህ አድርግ::"

ለጥቂት ጊዜያት ካነጋገርኳቸው በኋላ፣ ለመሄድ ተነሳሁ:: የስልክ ቁጥሬን ጻፍኩና፣ "ደውልልኝ፣ ገና ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ እንቅልፍ እንቅልፍ ካለህ ወይም ከተበሳጨህ ደውልልኝ:: እደምጥሃለሁ:: ችግርህን እረዳልሃለሁ፣ ምክንያቱም መረዳት እንድችል ሆኛለሁ:: አንድ የሚያደርገን ትንሽ ወዳጅነት በመካከላችን ተፈጥሯል፣ እያንዳንዳችን እጅ ለእጅ ልንያያዝ የቻልነው በምርጫችን ብቻ አይደለም" አልኩት::

ከመሄዴ በፊት፣ ብራድ እንዲህ አለ፣ "ወደዚህ በመምጣትህ ምን ያህል እንደተደሰትኩ ልነግርህ አልችልም:: እኔ እያየሁ ያለሁትን ስቃይ በሚያውቅ ሰው መጎብኘቴ በጣም ረድቶኛል:: በቀን ውስጥ ለሃያ አራት ሰዓት በማያቋርጥ ስቃይ ውስጥ ማለፍ ምን ማለት እንደሆነ ከሚያውቅ ሰው ጋር ስገናኝ አንተ የመጀመሪያ ነህ ..."

"እኔ በነበርኩበት ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ሰዎች መጎብኘት፣ እኔ ራሴ በገዛ ፍቃዴ አስቤ የማደርገው ነገር አይደለም" አልኩት፣ "ይሁን እንጂ አደርገው ዘንድ ፈቃደኛ ነኝ:: መረዳት እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን አንተ ወደ እኔ በመደወል የመጀመሪያውን ጥረት ማሣየት አለብህ:: አስታውስ ብቻህን የምትዘልቀው ነገር አድርገህ እንዳትገምት::"

የብራድ ሚስት መኪናችን ድረስ እየሸኘችን እንዲህ አለች፣ "የሚያስፈልገው ይህ ነበር:: ለሰዎች ሲታይ ልክ የኃይል ሁሉ ምንጭ እርሱ እንደሆነ ይመስላል፣ እሉታዊ የሆኑ ነገሮችንም ይናገራል:: በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት ውስጥ በፍርሃት ይዋጣል፣ ስሜቱ ይቀዘቅዛል፣ እናም በቀላሉ ውስጡ ተሰባብሮ ይወድቃል:: ስለ እርሱ በጣም መጨነቅ ጀምሬአለሁ:: አብረን በኖርንባቸው ዓመታት ሁሉ እንደዚህ ሲሆን አይቼው አላውቅም::"



"ሚስቴ ቀኑን ሙሉ በትምህርት ቤት ስትለፋ ቆይታ ምሽቱን ከእኔ ጋር ለማሳለፍ ስትመጣ የነበረችበትን ሁኔታ አስታውሳለሁ" አልኳት:: "ዝም ብለሽ ከእርሱ ጋር ቆይ:: እየተሻለው ይሄዳል::"

አንድ ጊዜ እጅግ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ፣ ኢቫ እኔን ልታጽናናኝ ፈልጋ፣ "ጊዜ ስጠው:: ደህና ትሆናለህ" እንዳለችኝ አጫወትኳት::

በጭንቀትና በቁጣ ፈነዳሁና፣ "እኔ ደህና እንደምሆን ምን አስበሽ ነው የምትናገሪው? እነዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ነገሮች እንዴት ነው ደህና የሚሆኑት? ማንም እንዲህ ብሎ ሊነግረኝ አይችልም:: ማንም ሰው ይህንን ቃል ሊገባልኝ አይችልም::"

ምስጋና ይግባትና ኢቫ አልተከራከረችኝም:: እጆቿን ዘርግታ አቀፈችኝ:: አለቀስኩ:: በእርሷ ፊት ያንን አድርጌው አላውቅም::

ለብራድ ሚስት ይህንን ታሪክ ከነገርኳት በኋላ፣ እንዲህ አልኩ፣ "በእርሱና በአንቺም ሕይወት ሊመጣ ስላለው ለወጥ ተዘጋጂ:: እርሱ ስሜቱን መቆጣጠር አይችልም፣ ይሁን እንጂ በሚጮህብሽና በሚቆጣ ጊዜ በግል በአንቺ ላይ የተነሳ አድርገሽ አትውሰጂው:: በአንቺ ላይ ሳይሆን ከስቃዩና ከስጋቱ የተነሣ ነው":: እጇን ጨብጬም እንዲህ አልኳት "ነገሮች መልካም እንዲሆኑ ከፈለግሽ በምትፈልጊኝ ጊዜ ደውይልኝ:: ብራድም እንዲደውልልኝ ገፋፊው::"

ከዚያ በኋላ ብራድን ሦስት ወይም አራት ጊዜ ያህል ጎብኝቼዋለሁ:: በመራመጃው እየተረዳ መራመድ ከቻለ ከሳምንታት በኋላ በአንድ ምግብ ቤት ውስጥ አይቼዋለሁ:: እርሱ ወደነበረበት ጠረጴዛ ሄጄ ተቀመጥኩ:: "እሺ ሁሉ ነገር እንዴት ነው?" ስል ጠየቅኩት::

"አሁን ደህና ሆኛለሁ፤ በርግጥ ደህና ነኝ"፡፡ እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በነበረበት ጊዜ መጥቼ ስለጎበኘሁት አመሰገነኝ፡፡ በዚያን ጊዜም የሰውነት አቋሙ ሙሉ ስሙሉ አልተመለሰለትም፤ ይሁን እንጂ እንደገና ጤነኛ ሰው ሆኗል፡፡ እጄን ጨብጦ ለረዥም ጊዜ እንደያዘ ቆየ፤ በቃላት ሊገልጽ ያልቻለውን አድናቆቱን የሚገልጽበት መንገድ መሆኑን አላጣሁትም፡፡

የሕይወቱ ጨለማ እጅግ በጠቆረበት ወቅት ብራድን ለመርዳት በመቻሌ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረብሁ፡፡

አደጋው ከደረሰብኝ ከሁለት ዓመታት በኋላ፤ ቻድ ቮውል ከባድ የሆነ የመኪና አደጋ እንደደረሰበት ሰማሁ፡፡ በሳውዝ ፓርክ የሚገኘው የወጣቶች አገልግሎት አባል የነበረ ሲሆን ቤተሰቦቹም በቤተክርስቲያን ከነበሩ ከፍተኛ እገዛ ከሚያደርጉልኝ ወገኖች መካከል ናቸው፡፡ እናቱ ካሮል ሆስፒታል በነበርኩበት ጊዜ ስለ ወጣቶች የእረፍት መዝናኛ ጉዳይ ለመወያየት ወደ እኔ ዘንድ ይመጡ ከነበሩት የኮሚቴ አባላት መካከል አንዷ ናት፡፡ በዚያን ጊዜ ወደ እኔ ዘንድ የሚመጡት እኔ ያን ያህል እገዛ ላደርግላቸው የምችል ሆኜ ሳይሆን እነርሱ እኔ ጠቃሚ ሰው እንደሆንኩ እንዲሰማኝ የተጠቀሙበት መንገድ ነበር፡፡

ቻድ በጣም የተዋጣለት የሶከር ተጫዋችና በቤተክርስቲያናችን የወጣቶች ህብረት ውስጥ ወደ ኮሌጅ እስከገባበት ጊዜ ድረስ ይሳተፍ ነበር፡፡

ለእናትዬው በደወልኩላት ጊዜ፤ በጋልቭስቶን ወደሚገኘው የስኦሴይ ሆስፒታል በሂሊኮፕተር እንደወሰዱት ነገረችኝ፡፡ ጉዳቱ



የደረሰበት በታችኛው እግሩ ላይ እንደሆነ ሪፖርት ደርሷል፤ የአጥንት ማጽኛ ብረትም ተደርጎለታል ብላ እስክትነግረኝ ድረስ ምን ያህል ከባድ አደጋ እንዳጋጠመው አላወቅኩም ነበር፡፡ የአጥንት ማጽኛ የሚለውን ቃል ስሰማ የግድ ሄጄ ማየት እንዳለብኝ ተሰማኝ ደግሞም የወጣቶች ህብረት አባላችን በመሆኑ መሄዴም አይቀርም፡፡ ይሁን እንጂ የአጥንት ማጽኛ የሚለው ቃል ለሁኔታው አጣዳፊነት ትኩረት እንድሰጥ አደረገኝ፡፡

ወደ ተኛበት ክፍል በገባሁበት ጊዜ፤ ቻድ ተደብሮ ተጋድሟል፤ ማንንም ሰው ማናገር እንደማይፈልግ በግልጽ ይታያል፡፡ ይህ ቀድሞ የማውቀው ቻድ አይደለም፡፡ ከዚያ ቀደም ባሉት ጊዜያት፤ እኔን ለማየት ሁል ጊዜም የሚፈልግ ነበር፤ ፊቱም እኔን በማክበር ይፈካል፡፡ በዚህ ጊዜ የእኔን በዚያ መገኘት አውቋል፤ ይሁን እንጂ ከእኔ ጋር ውይይት ለመጀመር ምንም አይነት ፍላጎት አልታየበትም፡፡

"ደህና ነህ ወይ? ትንሽ የመሻል ስሜት ይሰማሃል? " ስል ጠየኩትና ወደ እግሩ ተመለከትኩ፤ "የአጥንት ማጽኛውን እንዳደረጉልህ ደግሞ አያለሁ፡፡"

"አዎ አድርገውልኛል" አለ፡፡

"ቻድ፤ እኔ አደጋ የደረሰብኝ ጊዜ ታስታውሳለህ? ያንኑ በእኔ ላይ ያደረጉትን መሣሪያ ነው ለአንተም ያደረጉልህ፡፡"

"በእውነት?" ሲል ጠየቀኝ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በእኔ ላይ ፍላጎት እንዳሳደረ በሚገልጽ ሁኔታ ተመለከተኝ፡፡ እኔ መሣሪያውን በእግሬ ላይ አጥልቄ በጭራሽ አላየኝ ይሁን ወይም ሁኔታውን ዘንግቶት እንደሆነ አላውቅም፡፡ ወደ እርሱ ቀረብ አልኩና፤ "እስኪ ይህንን አስታውስ፤

እንዲህ ያሰውን መሣሪያ ያጠሰቀ ሰው ምን እንደሚሰማው አውቃለሁ” አልኩት።

ጉዳቱ የደረሰበት በታችኛው የእግሩ ክፍል ላይ ነበር። በታችኛው እግራችን ላይ ሁለት አጥንቶች በመኖራቸው ምክንያት ስመፈወስ ቀለል ይላል። ከዚያ ከመውጣቴ በፊት እንደተረዳሁት የመዳን እድሉ ሰፊ እንደሆነ በሀክምናው ምርመራ ተረጋግጧል።

ከዚያ ልጅ ጋር ስመነጋገር፤ እጁን ስመያዝና አብሬው ስመጸለይ ችዬ ነበር፤ በዚህም መንገድ ባጋጠመው ችግር ውስጥ እኔም አልፌበት እንደነበር እንዲገነዘበው አድርጌአለሁ። ስመጀመሪያ ጊዜ፤ ወደፊት ማየት ያለበት ዋነኛው ነገር የሚደረግለትን የሀክምና ክትትል መሆኑን የመገንዘብ ስሜት አደረበት። ከዚያ በፊት እኔ አደጋው ካጋጠመኝ በኋላ በእኔ ላይ እንደደረሰው ሰቻድ ዝርዝር የሆነ መረጃ የሰጠው ማንም ሰው አልነበረም። ልክ እንደእኔው ሁሉ ሰብስጭትና ሰድብርት ተሰጥቶ ነበር።

“የሀመም ስቃዩ ረዥም ጊዜ ይፈጃል። የማገገም ሂደቱም ዘላለም የሚቆይ ነው የሚመስለው፤ ነገር ግን ከሀመሙ ትድናለህ። ይህን አንድ ነገር አስታውስ፤ ትድናለህ። ”

እናም ዳነ።

ጆይስ ፔንትኮስት ዕድሜዋ ሰላሣ ዘጠኝ ዓመት ሲሞላ አንድ ሳምንት ሲቀረው ካንሰር እንዳለባት ታወቀ። በጣም ነበር የምወዳት። ያገባችው የኢቫን ወንድም ሲሆን ባሰቀያይ ጠጉር የሆኑ ጀርዳንና ኮልቶን የተባሉ ሁለት ልጆችን ትታ አልፋለች።



ጆይስ ከማውቃቸው እጅግ ተወዳጅ ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዷና ኃይለኛ ዘማሪ ብቻ አልነበረችም፤ ይልቁንም ገና ወደ አንድ ክፍል ውስጥ በመግባቷ ብቻ ክፍሉን በብርሃን የምታደምቅም ጭምር ናት። የምትዘምረው አልፎ አልፎ ብቻ ነበር።

ስሞቷ መታሰቢያ በአርካንሰስ በምትገኘው ፎርሬስት ከተማ በመጀመሪያዋ የባፕቲስት ቤተክርስቲያን በተዘጋጀው ሥነ ሥርዓት ላይ ንግግር እንዳደርግ በመጋበዜ ክብር ነበር የተሰማኝ። በጉባኤው አዳራሽ ውስጥ ከስድስት መቶ ሰዎች በላይ ነበሩ። ጆይስ በርካታ ክርስቲያናዊ ዝማሬዎችን በሲዲ አሳትማ ስለነበር በምድር ሰቀረነው ብዙ መንፈሳዊ ውርስ ትታልን ነው ያለፈችው። በዚያ ፀሃያማ ከሰዓት በኋላ የተባረኩ ዝማሬዎቿን ከራሷ እየሰማን ነበር።

ከሰማናቸው የተቀዱ ዝማሬዎቿ በኋላ አባቷ መጋቢ ቻርልስ ብራድሌይ ተስፋንና ድነትን አስመልክቶ ቃል አቀረቡ። በዚያ ሰተሰበሰብነውም፤ “ከዓመታት በፊት እኔና ጆይስ ቃል ኪዳን አድርገን ነበር። እኔ ቀድሜ የምሄድ ከሆነ በመቃብሬ ስፍራ እርሷ እንድትዘምር፤ እርሷ ቀድማ የምትሄድ ከሆነ ደግሞ በእርሷ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ እኔ እንድሰብክ ነበር። ዛሬ ሰትንሿ ልጄ የገባሁላትን ቃል ፈጸምኩ” ሲሉ ተናገሩ።

ያች ቅጽበት ዛሬም ድረስ ከውስጤ አልጠፋችም።

ሃዘን ያረገዙ ፈገግታዎች ብልጭ ብልጭ አሉ፤ እንባዎች ተከትሰዋቸው ወረዱ፤ ይሁን እንጂ ማንም በዚያ የተገኘ ንዴት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተሰማው አይመስለኝም።

የጆይስ አባት መልዕክታቸውን ከጨረሱ በኋላ ቀጣዩ ተናጋሪ እኔ ነበርኩ::

"ዛሬ ከመካከላችሁ አንዳንዶች ጆይስ እንዴት ልትሞት ቻለች? ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል" ስል ተናገርኩ:: "ነገር ግን ልትጠይቁ የሚገባችሁን የተሻለ ጥያቄ ልንገራችሁ፤ የኖረችው እንዴት ነበር? ጥሩ ኑሮ ኖራለች፤ የተወደደችም ነበረች:: የሕይወቷን ሩጫ በመልካም ጨርሳለች::"

ጆይስ ለቅጽበት ጊዜ በሕይወት መድረክ ላይ ውልብ ብላ እንዳለፈች ድራታም ኮከብ የምትመስል ነች፤ የኖረችው ለሰዎች ደስታ ለመስጠት በነበራት ፍቅር ነው፤ ልብ የሚጣልባት ባልንጀራ፤ የተለየች ውድ ልጅ፣ ተወዳጅ እህት አስደናቂ ሚስት ነበረች:: በዚህ ቤት ውስጥ ባላችሁት የብዙዎቻችሁን ልብ ለንጥቆ የገባውን 'ለምን?' የሚለውን ጥያቄያችሁን ለመመለስ እንደማልችል ግን በፍጹም ትህትና አገልጽላችኋለሁ" ስል በዚያ ለተሰበሰቡ ልባቸው ላዘነባቸው ህዝብ ተናገርኩ::

"መልስ ባልመጣ ጊዜ መጽናናት" አለ ስል ጨምሬ ተናገርኩ:: "ጆይስ ብሞት ወዲያውኑ ከእግዚብሔር ጋር እሆናለሁ የሚል ጽኑ እምነት ነበራት:: ደግሞም በሕይወት ብትኖር እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር እንደሚሆን ታምን ነበር:: ለመኖሯ ምክንያት የነበረው ነገር ይህ ነበር:: እኛም ሊኖረን የሚገባው ምክንያት ይሄው መሆን አለበት::"

ንግግሬን አንድ የግል ገጠመኜን በማካፈል ደመደምኩ:: ይህ ገጠመኜ ጆይስ ወደ ቤቷ ከመመለሷ በፊት በሆስፒታል ውስጥ ሳለች



ለመጨረሻ ጊዜ ያደረግነው የቃላት ምልልስ ሲሆን፤ ይህም ስለመንግስተ ሰማይ ነበር::

"ወደ መንግስተ ሰማይ ያደረኩትን ጉዞ ሳጫውታት በፍጹም ለምታ አትጠግብም ነበር:: በዚህም ለመጨረሻ ጊዜ አብረን መንግስተ ሰማይን በሃሣባችን ጎበኘናት:: ስለመላእክቱ አወራን፤ ስለ መንግስተ ሰማይ ደጆች ተጫወትን፣ እንወዳቸው ስለነበሩ በዚያ ስላሉ ሰዎች ተነጋገርን (የጆይስ እናትም የሞቱት በካንሰር ምክንያት ነበር):: ጆይስ ሁልጊዜም ስለዝማሬው እንድተርክላት ትፈልግ ነበር:: የነበረን የመጨረሻው የንግግር ልውውጥም ከዚህ የተለየ አልነበረም::"

"ከጥቂት ቀናት በፊት"፣ ንግግሬን ለጉባኤው ቀጠልኩ፤ "እግዚአብሔር በእነዚያ በመንግስተ ሰማያት ደጆች ላይ ተቀምጦ፣ መላእክቱን በዚህ አካባቢ አሁን የሚያስፈልገን ጥሩ ባለቀይ ጠጉር ዘማሪ ነው ሳይላቸው እንዳልቀረ እምናለሁ:: መላዕክቱ፣ ያች ዘማሪ ጆይስ ፔንትኮስት መሆን አለባት!" ብለው እንደ ተናገሩ እምናለሁ::

"እግዚአብሔር ወደ ጆይስ መልእክተኛ ላከ:: እርሷም ለጥሪው ምላሽ ሰጠች:: አሁን ከመላእክቱ ተቀባዮቿ ጋር በመዘመር ላይ ትገኛ ለች:: ጆይስ ፔንትኮስት አሁን በአካል የለችም፤ ይሁን እንጂ ከጌታ ጋር ናት::"

የሃሣቤ ማጠቃለያ ለሕዝቡ የቀረበ ጥያቄ ነበር::

"የት እንዳለች የምታውቋትን ሴት፣ እንዳጣችኋት ትቆጥራላችሁን?"

በመኪና አደጋ በሞትኩበት ጊዜ የለላሳ ዘጠኝ ዓመት ጎልማሣ ነበርኩ:: ጆይስም የካንሰር በሽታ እንዳለባት ሲነገራት በዚሁ ዕድሜ ላይ

ነበረች፡፡ እኔ ከደረሰብኝ ዘግናኝ ጉዳት እንደገና ማገገም ቻልኩ፡፡ ጆይስ ግን አልቻለችም፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር አውቃለሁ፤ እኔ መንግስተ ሰማይን ስላየሁ፤ እርሷንና ተወዳጆቿን ሁሉ ለዚያ ክብር ላዘጋጃቸው ችዬ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ እናንተን እያዘጋጀኋችሁ ነው፡፡

አደጋ ከደረሰብኝ በኋላ ብዙ ጊዜ በአደጋ ምክንያት በእግሩ ላይ የአጥንት ማጽኛ መሣሪያ ተገጥሞለት ለወራት ያህል ያሳለፈ ሰው ወደ ሆስፒታሉ መጥቶ እንዲጎበኘኝ እናፍቅ ነበር፡፡ እንደዚያ ቢሆን አብዛኛው ጭንቀቴ እንደሚቃለልልኝ አውቅ ነበር፡፡

አሁን ደግሞ በእግራቸው ላይ መሣሪያው ስለተደረገላቸው ሰዎች በሰማሁ ቁጥር፤ ልገናኛቸው እሞክራለሁ፡፡ ረዥም የሥቃይ ጊዜ በማሳለፍ ላይ ያሉ ሰዎችን ሳነጋግር ሙሉ ለሙሉ ግልጽ ልሆንላቸው እሞክራለሁ፡፡ ከዚያ የህክምና ሂደት በቀላሉ የሚወጣበት መንገድ የለም፤ ይሄንንም እንዲያውቁ ደግሞ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እኔ በዚያ ሂደት ውስጥ ስላለፍኩ ልነግራቸው እችላለሁ (እነርሱም ያደምጡኛል)፤ ምንም እንኳን የማገገም ሂደቱ ረዥም ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም በመጨረሻው ይሻላቸዋል፡፡ በተጨማሪም አጫጭር ለሆኑ ጊዜያት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን እነግራቸዋለሁ፡፡

ከቻድና ከብራድ እንዲሁም ከሌሎች ጋር የነበረኝ የጉብኝት ጊዜ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለመቆየቴ ዓላማ እንዳለው እንዳስታውስ አድርገውኛል፡፡ በነበረኝ በዚያ ረዥም የማገገም ጊዜ አንዳንድ ጊዜ መንግስተ ሰማይን እናፍቅ ነበር፡፡ ዛሬ ዘወር ብዬ ስመለከተው ግን፤ ዛሬ ለሌሎች ሰዎች ያካፈልኳቸው የመንግስተ ሰማይ ልምምዴ መንግስተ



ሰማይ ከነበርኩበት በዝግታ ወደ ምድር ያወረደኝ እንደሆነ እመለከታለሁ፡፡ "እግዚአብሔር ሊወስደኝ በተዘጋጀ ጊዜ" በመጨረሻው "እግዚአብሔር ይለቀኛል" ለማለት እችላለሁ፡፡ እስከዚያው ግን የተቻለኝን ያህል ለሌሎች የተመቻቸ አገልግሎት ለመስጠት እሞክራለሁ፡፡

እንደኔው ሁሉ፤ አደጋው የደረሰባቸው ሌሎች በመጀመሪያ ጊዜ የአጥንት ማጽኛ መሣሪያውን በእግራቸው ላይ ሲመለከቱ፤ በተለይም ደግሞ አስቃቂ የሆነውን የስቃይ ስሜቱንና ለመራመድ አለመቻላቸውን ሲያውቁ ድብርት በውስጣቸው ይለቀቃል፡፡ ቀጥሎ የሚሆነው ነገር ምን እንደሆነ አያውቁም፡፡ ምንም እንኳን ዶክተሮቹ እንደሚሻላቸው ሊያረጋግጡላቸው ቢሞክሩም፤ ከዶክተሮቹ ቃል መጽናናትን ለማግኘት ስለሚከብዳቸው በብዙ ይጎዳሉ፡፡

ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ፤ ህመምተኛው ባለማስተዋል፤ "ከዚህ ችግር በፍጥነት ወጥቻለሁ" ብዬ እንደተናገርኩ በማሰብ ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ሊደርስ ይችላል፡፡

"ካለህበት ችግር ልትወጣ ትችላለህ፤ ይሁን እንጂ ፈጥኖ የሚሆን ነገር አይደለም" ብዬ እነግረዋለሁ፡፡ "ይህ በረዥም ጊዜ ልትወጣው የምትችለው የህክምና ሂደት ነው፤ ሂደቱንም ለማፋጠን የሚያስችል አንዳችም አማራጭ መንገድ የለም፡፡ በዚህ አይነት የከፋ ደረጃ ጉዳት የሚያጋጥምህ ከሆነ፤ ፈጥኖ ለመውጣት ቀላል መንገድ የለም፡፡ ለጊዜው አብረኸው ልትኖር ግድ ነው፡፡"

ሌሎች ታሪኮችንም ላጫውታችሁ እችላለሁ፤ ይሁን እንጂ በሕይወቴ እጅግ በጨለሙ አንዳንድ ጊዜዎቼ ውስጥ እንዳልፍባቸው

ያስቻሉኝ ገጠመኞቼ እነዚህ ናቸው። በዚህ ምድር ለመኖሬ እንደገና ዓላማዬን አውቄአለሁ። አሁንም ወደ መንግስተ ሰማይ ለመመለስ እናፍቃለሁ፤ ይሁን እንጂ ለጊዜው ልሆን የተገባኝ ስፍራ ይህ ነው። በምድር የተሰጠኝን የሕይወት ግዳጅ እየተወጣሁ ነው።



# 17

# ወደ ቤቴ እናፍቃለሁ

"ስለ እናንተ ስንጸልይ፤ በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ የተነሳ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እምነታችሁ፤ ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተን፤ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እናመሰግናለን። ስለዚህም ተስፋ በወንጌል እውነት ቃል አስቀድማችሁ ሰማችሁ"

ቆላ 1፥5-6

ደጋግሜ ከምናገራቸው ተወዳጅ ታሪኮች አንዱ፤ ከቤቷ ወጥታ የት እንደሄደችና እንደደረሰች እናቷ ያላወቀቻት የትንሿ ልጃገረድ ታሪክ ነው። እናቷ የልጇን መጥፋት ካወቀች በኋላ በልጇ ላይ አንድ ነገር ሳይደርስ አይቀርም ስትል በጭንቀት ተዋጠች። በቤቷ መግቢያ በር ላይ ቆማ የልጇን ስም ደጋግማ ተጣራች።

ወዲያውኑ ልጅቷ አጠገባቸው ከነበረው ቤት ወጥታ እየሮጠች ወደ ቤቷ መጣች። እናቷ የልጅቱን እጅ ይዛ፤ እንደተጨነቀች ከነገረቻት በኋላ፤ "የት ነበርሽ?" ስትል ጠየቀቻት።

"አገጠባችን ካለው ቤት ከሚስተር ስሚዝ ጋር ነበርኩ።"

"ደግሞ እዚያ ምን ታደርጊያለሽ?"

"ሚስቱ በመሞቷ ምክንያት በጣም አዝኗል።"

"እ! ምጣም አዝናለሁ፤ ያንን አላውቅኩም ነበር አለች" እናቷ:: "ይሁንና አንቺ እዚያ ምን እያደረግሽ ነበር?"

"አይ በቃ ሲያለቅስ አላቅሰው ነበር::"

በነገራችን ላይ እኔም ይህንኑ እያደረግኩ ነው:: ልምምዴን ሳካፍላቸው በጭንቀት ያሉትን አብሬ እያላቀስኳቸው ነው::

ራሳቸው ወደ ሞት ለተቃረቡትና በሚወዷቸው ሰዎች ሞት ምክንያት እጅግ ላዘኑ ሰዎች መጽናናትን ማምጣት የቻልኩበትን አንድ ምክንያት ልገነዘብ ችያለሁ:: አጠገባቸው በመገኘት መንግስተ ሰማይ አቻ የሌለውና ሊገለጽ የማይችል ደስታ ያለበት ስፍራ መሆኑን ላረጋግጥላቸው መቻሌ ነው::

ያለ አንዳች ጥርጥር፤ መንግስተ ሰማይ እውን መሆኑን አውቄአለሁ:: በሕይወቴ ከተለማመድኳቸው ልምምዶቼ ሁሉ የበለጠ እውን ነው:: አንዳንድ ጊዜ፤ "በእናንተ ላይ የደረሰውን የትኛውንም የከፋ ነገር አስቡ፤ ደግሞም ያጋጠማችሁን ከፍተኛ ደስታ አስቡ፤ እንደገናም በእነዚህ መካከል ያጋጠሟችሁንም ነገሮች ሁሉ አስቡ፤ ከነኝህ ነገሮች ሁሉ ይበልጥ መንግስተ ሰማይ እውን ነው" እያልኩ እናገራለሁ::

ወደ ምድር ከተመለስኩ በኋላ፤ ሁላችንም በጉዞ ላይ መሆናችንን ልረዳ ችያለሁ:: ይህንን የሕይወት ዘመናችንን በጨረስን ጊዜ የምንሄድበት ሕይወት ወደ መንግስተ ሰማይ ወይም ወደ ሲኦል፤ አሁን ከምንኖረው ኑሮ ይልቅ እጅግ እርግጠኛ ነው::



አደጋው በእኔ ላይ ከመድረሱ በፊት በፍጹም አስቤው አላውቅም ነበር:: ለኔ መንግስተ ሰማይ እንደ ሀሳብ ነበር፣ የማምነውም እንደዚያ ነበር፤ ደጋግሜም የማላስበው ነገር ነበር::

ከአደጋው በኋላ ባሉት ዓመታት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሸጡና ከመሰቀሉ በፊት ከደቀመዛሙርቱ ጋር ያደረገውን የመጨረሻ ምሽት ደጋግሜ አስበዋለሁ:: ወደ መንግስተ ሰማይ ጉዞ ለመጀመር ጥቂት ሰዓታት ብቻ ሲቀረው በላይኛው ክፍል ውስጥ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ:: በምንም ነገር እንዳይጨነቁና በእርሱ እንዲያምኑ ለመናቸው:: እንደሚሄድ ከነገራቸው በኋላ "በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፤ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ" (ዮሐ 14፥2-3)

ከዚያ በፊት ይህን በእውነት አስተውዬው አላውቅም፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ሁለት ጊዜ "ስፍራ" የሚል ቃል ተጠቅሟል፤ አድራሻን ያመለክታል:: ምናልባት ይህ ብዙ ሰዎችን ላያነቃቃቸው ይችላል፤ ነገር ግን ይህን ቃል ደጋግሜ አስበዋለሁ:: እውነተኛ የሆነ ስፍራ ነው፤ ደግሞም ያንን ስፍራ እንደማውቀው ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ:: እዚያ ነበርኩ:: መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነ አውቃለሁ::

ከደረሰብኝ አደጋ በኋላ፤ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ትኩረትን መስጠትና በጥልቀት ማሰብ ይሰማኛል:: አንድ ዓመት ያህል በሆስፒታል የቆየ ማንም ሰው እንደዚያ ሊሰማው ይችላል፤ ነገር ግን ይህ ከዚያም የዘለለ ነገር ነው:: እነዚያ የዘጠና ደቂቃ ቆይታዎቼ ደግሜ የቀደመውን አይነት ሰው እንደማልሆን የሚያስረግጡ ስሜቶችን ትተውብኝ

አልፈዋል:: በዚህ ምድር ላይ ሙሉ ለሙሉ ራሴን ጥዬ ዳግመኛ አልኖርም፤ ምክንያቱም አሁን የምኖረው መጭውን እየተጠባበቅኩ ነው::

የሰው ልጅ ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ ስቃይ እንደተቀበልኩ አስባለሁ፤ ዛሬም የምኖረው ስለዚያው ነገር ለመናገር ነው:: በነዚያ ወራት ወሰን የሌለው ስቃይ ቢደርስብኝም እንኳን እኔ ከተቀበልኩት መከራ ይልቅ የመንግስተ ሰማይ እውነታ እጅግ እጅግ በላጭ መሆኑ ይሰማኛል::

እጅጉን በስሜቱ የምነዳና ዝግ ለማለት በጣም የምቸገር ሰው በመሆኔ ምክንያት፤ ብዙ ጊዜ የተወሰኑ ነገሮችን ማድረግ ያልቻልኩበትን ምክንያት መግለጽ መቻል እንደሚኖርብኝ ይሰማኛል:: ሙሉ ልብስ በለበስኩ ጊዜ፤ አብዛኞቹ ወገኖች በከባድ አደጋ ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሰብኝ ፈጽሞ አይመስላቸውም:: ይሁን እንጂ ይህ እንደገና የተጠጋገነ አካሌ ማድረግ የማይችላቸው አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ሲያጋጥሙኝ አብዛኛውን ጊዜ ምላሼ ያልተለመደ ነው የሚሆነው:: አብዛኛዎቹ እነዚህ እንቅስቃሴዎች በጣም ቀላል የሆኑ በመሆናቸው ብዙ ሰዎች ይደነቃሉ::

"ጤነኛ ትመስላለህ፤ ምንድን ነው እሱ ችግርህ? " ብዙ ሰዎች እንዲህ ይናገሩኛል::

አልፎ አልፎ፤ ከአንድ ሰው ኋላ ኋላ እየተከተልኩ ደረጃ የምወርድ ከሆነ፤ አንድ አስቸጋሪ ነገር ይፈጠራል፤ ጉልበቶቼ እርስ በእርስ እየተፋጩ ሲንገጫገጩ ድምጽ ይሰማል:: እናም ዘወር ብለው፤ "እንዲህ አይነቱ የሚረብሽ ድምጽ የሚወጣው ከአንተ ነው?" ይሉኛል::



"አዎ እላለሁ" ፈገግ እልና፤ "አስደናቂ ድምጽ አይደለም?!"

አንጻራዊ በሆነ መልኩ እንቅስቃሴዬ ግራ የሚያጋባ ነው:: ምንም እንኳን የማደርጋቸው ነገሮች ውስንነት ያላቸው መሆኑ ለሌሎች ባይታወቅም፤ ማንም ሰው ያደርገዋል ብሎ ከሚገምተው በላይ እንቀሳቀሳለሁ:: በአግባቡ ለመራመድ ጠንክሬ እሠራለሁ፤ ምክንያቱም የሌሎችን ትኩረት ወደራሴ መሳብ ስለማልፈልግ ነው:: ያንን የአጥንት ማጽኛ አድርጌ በነበርኩበት ጊዜ ብዙዎች ወደ እኔ አፍጥጠው እንዲመለከቱ በሚያደርግ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ::

ጤነኛ እንደሆነ ሰው ነገሮችን ለማድረግና ለመምሰልም እንዲሁም ራሴን ወደ ፊት መግፋት አካላዊ ድካሜንና ጉድለቴን ለማሸነፍ የተጠቀምኩባቸው መንገዶች ነበሩ:: ከልምዴ እንዳገኘሁት፤ ራሴን በሥራ በምጠምድበት ይልቁንም ሌሎችን በምረዳበት ሥራ ላይ በሆንኩ ጊዜ ህመሜን እረሳዋለሁ:: ግራ በሚገባ መንገድ የህመም ስቃዬ ህክምና ያገኛል:: መራመድ እስኪሳነኝ ድረስም መሄድን አቅዳለሁ::

ምድራዊ በሆነ ንድፈ ሃሳብ ስለ ጊዜ ባለን ተፈጥሯዊ አመለካከት ተጽእኖ ሥር የወደቅን ነን - ሥርአታችን እንደዚያ ነው:: አስረግጬ ልናገርበት የምፈልገው ጠቃሚ ሃሳብ ይሄ ነው:: ተፈጥሯዊ በሆነ አመለካከቴ ስቃኘው በመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ የተቀበሉኝ እነዚያ የመስተንግዶ አባላት እኔ ወደ ምድር በተመለስኩባቸው በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ምን እያደረጉ እንደሆነ እደነቃለሁ::

ይህንን በአንክሮ ሳስተውለው፤ አቀባበል ያደረጉልኝ ቡድን "ኦ! ያሳዝናል በዚህ አልቆየም" ብለው እንደተናገሩ አላምንም:: አሁንም

በዚያው በመግቢያው በር ላይ ናቸው። አሁንም ይጠብቃሉ። ለእነርሱ ጊዜ የሚያልፍ ነገር አይደለም። አሁን ሁሉም ነገር በዘላለም ውስጥ ነው - እርግጥ ነው ይህንን በቃላት መግለጽ አልችልም፣ ምንም እንኳን አሥር ወይም ሰላሳ ዓመታት ቢያልፉም እንኳን በመንግስተ ሰማይ፣ እንደገና ወደዚያው እስከመለስ ድረስ ያለው ጊዜ የቅጽበት ያህል ጊዜ ነው።

የዚያ የጥር ወር ማለዳ ወደ መንግስተ ሰማይ ያደረግኩት ጉዞ በራሴ ምርጫ አልነበረም። በዚህ ሁሉ ውስጥ ያደረግኩት አንድ ምርጫ፣ አንድ ቀን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቤ እንደ አዳኜ አድርጌ እርሱን መቀበሌ ነው። ምንም እንኳን የማልጠቅም ሰው ብሆንም ወደ መንግስተ ሰማይ እንድገባ ፈቀደ። እናም ዳግመኛ ወደዚያ በሄድኩ ጊዜ በዚያው እንድቆይ አውቃለሁ።

የመሞት ምኞት የለኝም። ራሱን ለማጥፋት እንደሚፈልግ ሰውም አይደለሁም፣ ይሁን እንጂ ሁልጊዜም ተመልሼ ስለመሄድ አስባለሁ። ለመመለስ እናፍቃለሁ። በእግዚአብሔር በራሱ ጊዜ፣ በፍጹም እርግጠኝነት ይህ እንደሚሆን አውቃለሁ። አሁን ያንን ጊዜ እናፍቃለሁ፣ በታላቅ ጉጉት እጠባበቀዋለሁ።

በፍጹም የሞት ፍርሃት የለኝም። ለምን እፈራዋለሁ? የሚያስፈራ አንዳች ነገር የለም በሞት ውስጥ ያለው ደስታ ብቻ ነው።

ቀደም ሲል ገልጬዋለሁ፣ ወደ ምድር ተመልሼ አዕምሮዬ በነቃ ጊዜ ልቆጣጠረው የማልችል ትልቅ ቁጣ በውስጤ አልፎ ሄደ። ወደ ምድር መመለስ አልፈለግኩም፣ ይሁን እንጂ ያም ቢሆን የእኔ ምርጫ አልነበረም።



ለረዥሮም ጊዜ፣ እግዚአብሔር ወደ ምድር መልሶ የላከኝ አይመስለኝም ነበር። ነገር ግን ግራ በሚያጋቡኝ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳን በሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ዓላማ እንዳለው አውቃለሁ። ወደ መንግስተ ሰማይ ስሄድ ምክንያት ነበረው፣ ወደ ምድር መመለሴም ዓላማ አለው። በመጨረሻው፣ እግዚአብሔር ልዩ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንዳሳለፈኝና ዘላለም ምን እንደሚመስል በከፊል እንዳይ ማድረጉን አውቄአለሁ።

ምንም እንኳን ሰማያዊ የሆነውን ቤቴን ብናፍቅም፣ የመጨረሻው ሉአላዊ ጥሪ ወደ እኔ እስኪመጣ ድረስ ለመጠበቅ ተዘጋጅቻለሁ።

በሰላሣ አራት የቀዶ ጥገና ህክምናዎች ውስጥና በብዙ ዓመታት ስቃይ ውስጥ ማለፌ፣ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች፣ "የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። እርሱ በመከራችን ያጽናናናል፣ ስለዚህም እኛ እራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን" (2ቆሮ 1፥3-4)

በዚህ ምድር ላይ እስከቆየሁ ድረስ፣ እግዚአብሔር አሁንም ለእኔ ዓላማ አለው። ያንን እውነት ማወቄ ስቃዬን ታግሼ ለመቋቋምና አካላዊ ጉድለቴን ተቀብዬው እንድኖር አስችሎኛል።

እጅግ አስቸጋሪ በሆኑት ጊዜዎች ቀደም ካሉ ዝማሬዎች አንድ መስመር ትዝ ይለኛል። "ኢየሱስን ባየነው ጊዜ ሁሉም መልካም ይሆናል" እንደሚሆንም አውቃለሁ።

# 18
# ስምን?

"ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፣ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ አውቃለሁ::"

1ቆሮ 13፥12

ብዙ ጊዜ ሰዎች በቴሌቪዥን መስኮት ውስጥ ወደ ሞት እጅግ ተቃርበው እንደነበረ ሲናገሩ አዳምጫለሁ:: በነገራቸው መማረኬ እውነት ቢሆንም ጥርጣሬ ግን አለኝ:: እንደ እውነቱ ከሆነ በጣም ነው የምጠራጠረው:: እነዚህ ሰዎች ንግግር ከማድረጋቸው በፊትም ሆነ በኋላ እንዲህ እያልኩ አስባለሁ፤ "ምናልባት እነዚህ ሰዎች አንጎላቸው ቀስ በቀስ ሥራውን አቁሞ ሊሆን ይችላል:: ወይም ምናልባት በትውስታቸው ካዝና ውስጥ ተቀብሮ የኖረ አንድ ነገር ይኖርና ያንኑ ደግመው እያስታወሱት ይሆናል" እላለሁ:: በሰዎቹ ቅንነት ጥርጥር የለኝም፤ የተናገሩትን ለማመን እንደፈለጉም አውቃለሁ::

በቴሌቪዥን በርካታ ቃለ ምልልሶችን ተመልክቻለሁ፤ በአስደናቂ መንገድ የሞት ሰለባዎች ስለነበሩና ከሞት ስለተመለሱ (ትንፋሻቸው ስለተመለሰች) ሰዎች የተጻፉ ጽሑፎችን አንብቤአለሁ:: ከሞት ጋር ስላደረጉት ትንንቅ የሚያቀርቡት ገለጻቸው ብዙውን ጊዜ በጣም የተጠናና በሚረብሽ መልኩ ልክ አንድ ሰው የመጨረሻው ሰው የተናገረውን በትክክል ገልብጦ የተናገረው እስኪመስል ድረስ



ተመሳሳይነቱ የሚረብሽ ነው:: ከሃያ አራት ሰዓት በላይ ሞቶ እንደነበር የሚናገር አንድ ሰው፤ በጻፈው መጽሐፉ ላይ ከአዳምና ከሄዋን ጋር እንደተነጋገረ ተርኳል:: የመጀመሪያዎቹ ባልና ሚስት ነግረውኛል የሚላቸው አንዳንድ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሲመዘኑ እውነት ያላቸው አይደሉም::

ዛሬም ድረስ አብዛኛዎቹን ምስክርነታቸውን ብጠራጠርም፤ የገዛ ራሴን ሞት ግን በጭራሽ ተጠራጥሬው አላውቅም:: እንደ እውነቱ ከሆነ እጅግ ሃያልና ሕይወትንም የሚለወጥ ስለነበር ከዴቪድ ጀንቲልስ ጋር አደጋው ከደረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ በግል ባደረግነው ጭውውት ከመግለጼ በፊት በጭራሽ ለማንም አልተናገርኩም::

ወደ ሞት ተቃርበው ስለነበሩ ሰዎች የተደረገውን ጥናት ተመልክቼ፤ ለዓመታት ያህል በጉዳዩ ላይ ሳስብበት ቆይቻለሁ:: በቅርቡ በታህሳስ ወር በ2001 በርካታ የሳይንስና የህክምና ሊቃውንት፤ እነዚህን ተውኔታዊ የሆኑ ገጠመኞችን "በምኞት የተሞሉ ሃሳቦች ወይም የኦክስጂን እጥረት ከገጠመው አንጎል የመነጩ የተሳሳቱ እሳቤዎች ናቸው" ሲሉ ውድቅ አድርገዋቸዋል::

በኔዘርላንድስ የተደረገው ጥናት የመጀመሪያው ሳይንሳዊ ጥናት ነው:: አንድ ጊዜ ሞተው ነበር ተብሎ ከተነገረላቸው ሰዎች ጋር ቃለ ምልልስ ከማድረግ ይልቅ የተጠቀሙት፤ በሆስፒታል ውስጥ የሞቱትንና ከሞት የተነሱትን በመቶዎች የሚቆጠሩ ህመምተኞች ማነጋገርን ሲሆን እነዚህም የልብ ምታቸው ፈጽሞ ቆሞ የነበሩ ናቸው:: ይህን አይነቱን መንገድ የመረጡበት ምክንያት፤ ከሞት ከተነሱ ከረዥም ጊዜ በኋላ ያጋጠማቸውን ነገር እያስታወሱ እንዲናገሩ ከማድረግ ይልቅ፤ ሁኔታው

እንደተከሰተ ወዲያውኑ ሁኔታውን እንዲዘግቡ ማድረግ በተሻለ መንገድ ትክክለኛ መረጃን መስጠት ይችላሉ ብለው ተስፋ በማድረጋቸው ነው::

ውጤቱም ይሄ ነበር፤ አስራ ስምንት በመቶ የሚሆኑ በሽተኞች በሆስፒታል ውስጥ በሞቱበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ እንደሚያስታውሱ ተናግረዋል:: ከስምንት እስከ አስራ ሁለት በመቶ የሚያህሉቱ ወደ ሞት ተቃርበው የነበሩ ሰዎች እዘውትረው የሚናገሩትን ለምሳሌ ያህል እንጻባራቂ የሆነ ብርሃን ማየታቸውን፤ በሆነ ሸለቆ ውስጥ ማለፋቸውን ወይም ወደ መንግስተ ሰማይ ተሻግረው ከሞቱ ዘመዶቻቸው ወይም ጓደኞቻቸው ጋር መነጋገራቸውን ገልጸዋል:: አጥኚዎቹ ከሞት በኋላ ወይም ወደ ሞት ተቃርበው የነበሩ ሰዎች ልምምድ፤ "ሌሎች አማራጮችን ሁሉ ፈትሸን ተስፋ ስንቆርጥ ልንቀበለው የምንችል እውነት ብቻ" ሲሉ ጥናታቸውን ደምድመዋል::

በሌላ ወገን፤ ሌሎች ተመራማሪዎች ሞተው በተነሱ በ344፣ ዕድሜያቸው ከሃያ ስድስት እስከ ዘጠና ሁለት በደረሱ ሰዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት ላይ ተመርኩዘው የራሳቸውን ድምዳሜ ሰጥተዋል:: አብዛኞቹ ቃለ ምልልሱን ያደረጉት ክስተቱ ከተፈጸመ ከአምስት ቀናት በኋላ ነበር:: አጥኚዎቹ እነኛኑ ሰዎች ከሁለት ዓመት በኋላና ከስምንት ዓመት በኋላ አግኝተው አነጋግረዋቸዋል::

አጥኚዎቹ በዚሁ ፍተሻቸው የእነዚህ ሰዎች ልምምድ ከተለመዱት ሥነ አካላዊ፣ ስነልቡናዊ ወይም የህክምና መመዘኛዎች አንጻር ሲታይ እየሞተ ያለ የሰው አንጎል ከሚያሳየው ሁኔታ ጋር የማይመሳሰል መሆኑን ደርሰውበታል:: አጥኚዎቹ፣ አብዛኞቹ በሽተኞች ስለ ክስተቶቹ አስደናቂ ትውስታ አላቸው ያሉት ትውስታዎቹ ሀሰት ናቸው የሚለውን ሀሳብ ይሸረሽረዋል::



ለእኔ እጅግ ጠቃሚው ነገር በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ ሰዎች በስብእናቸው ላይ የተገለጠ ለውጥ መታየቱ ተዘግቧል:: ለሞት የነበራቸው ፍርሃት ጠፍቷል:: ርህራሄን የሚያሳዩ፣ ቸርነት የሚያደርጉና ፍቅር ያላቸው ሆነዋል::

ዘገባው ወደ ሞት ተቃርበው ስለነበሩ ሰዎች እውነታ ያረጋገጠው ምንም ነገር የለም:: ከጥናቱ በፊት አንዱ ቡድን፤ ወደ ሞት ተቃርበው የነበሩ ሰዎች፤ በመሞት ላይ ያሉ ሰዎች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ብቻ ናቸው ብሏል::

ሌላው ቡድን ደግሞ ጠንካራ የሆኑ ማስረጃዎች ወደ ሞት የመቃረብን ክስተት የሚያረጋግጡ በመሆኑ፤ ሳይንቲስቶቹ ከአካል ተለይቶ የመውጣትን ጽንሰ ሃሳብ እንደገና እንዲያጤኑት ሃሳቡን አቅርቧል::

በዚህ ጉዳይ ላይ የሚነሱትን ክርክሮች ለመዳኘት አልሞክርም:: እኔ ነገሮችን የማየው በራሴ ላይ ከደረሰው ነገር አኳያ ነው:: አጥኚዎቹ ምንም ነገር ሊነግሩኝ ወይም ላይነግሩኝ ቢሞክሩም፤ እኔ መንግስተ ሰማይ ሄጄ እንደነበር አውቃለሁ::

በእኔ ላይ የደረሰውን ነገር በአንክሮ ስመገንዘብ፤ የደረሰብኝ ነገር ምንድነው? ከሚለው ጥያቄ ይልቅ በእኔ ላይ የደረሰው ለምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለማሰላሰል ሰፊ ጊዜ ሰጥቻለሁ:: የደረስኩበት አንድ ጠንካራ መደምደሚያ ብቻ ነው፤ በመኪና አደጋ ከመገደሌ በፊት ወደ ሞት ስለተቃረቡ ሰዎች ዘገባ በጥርጥር ውስጥ እንዳለሁ ቆይቻለሁ:: በቀላሉ አንድ ሰው ሞቶ ወደ መንግስተ ሰማይ ሄዶ እንደገና ተመልሶ ስላየው ነገር መናገር የሚችልበት ሁኔታ እንዴት እንደሆነ አይታየኝም ነበር:: መሞትን፣ የመንግስተ ሰማይን እርግጠኛነት ወይም ከሞት በኋላ

ሕይወት መኖሩን አልጠራጠርም:: ግን "ወደ ሞት ተቃርቤ" የሚሉ ዘገባዎችን ተጠራጥሬአለሁ:: ታሪኮቹ ሁሉ የተጠኑና ተመሳሳይ ድምፀት ያላቸው ይመስላሉ:: ከዚያም እኔ ራሴ ሞትኩ፣ ወደ መንግስተ ሰማይ ሄድኩ፣ ተመለስኩም:: መናገር የምችለው በእኔ ላይ የሆነውን ነገር ብቻ ነው::

ይህ ለቅጽበት ያህል ያሰብኩት ራዕይ ወይም ህልም አይደለም፣ በአእምሮዬ የተመሰሰ ክስተቶች አይደሉም፣ ወይም የሰማኋቸው ታሪኮች ውጤት አይደለም:: መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነ አውቃለሁ:: እዚያ ነበርኩ፣ ተመልሼም መጥቻለሁ::

ነገሩ እንዲህ ሊቋጭ ይችላል፤ አንድ ሰው ለተወሰነ ጊዜ ያህል ይሞታል፣ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ በተጨባጭ ሁኔታ ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት ከተመለከተ በኋላ ወደ ሕይወት ይመለሳል:: በዚህም ወደ ሞት ተቃርቦ የነበረው ሕይወት የእምነት ጉዳይ ሆኖ ይቀጥላል ወይም ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ በተጨባጭ መንገድ መግለጽ የማይቻል ክስተት ይሆናል:: ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላ፣ አንድ ጓደኛዬ ተናግሮ እንደነበረው፤ "እንግዲህ አዲሱ ነገር ምንድን ነው?"

እንድ ጊዜ የባለቤቴ ቤተሰቦች ኢልዶንና ኢቴል ፔንትኮስት በነበሩበት በአንድ ትልቅ ጉባኤ መካከል የሕይወት ልምምዴን አካፍል ነበር:: እነኝህ ዘመዶቻችን አደጋው በደረሰብኝና ከዚያም በኋላ ረዥም ጊዜ በወሰደው የሕክምና ጊዜዬ የደገፉንና ትልቅ መስዋእትነት የከፈሉልን ናቸው::



ከአገልግሎቴ በኋላ፤ ወደ ቤታቸው ሄድን:: በዚያ ወቅት እኔና ኢልዶን ብቻችንን የሆንበት አጋጣሚ ተፈጠረ፤ እናም እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "ወደ መንግስተ ሰማይ ስላደረግከው ጉዞ ስትናገር ለመጀመሪያ ጊዜ ስለማ ተናድጄ ነበር" አለኝ::

ለምን እንደዚያ እንደተሰማው ምንም አይነት ግምት አልነበረኝም::

"ንግግርህን የጨረስከው ወደ ምድር መመለስህን በፍጹም እንዳልፈለግከው በመግለጽ ነበር::"

በአዎንታ ራሴን ነቀነቅኩ፤ ነገሩ ወዴት እንደሚያመራ አላወቅኩም ነበር::

"በዚያን ጊዜ ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም፤ አሁን ግን ተለውጫለሁ::" አሁን አሁን ስለ መንግስተ ሰማይ ውበት ስታወራ፤ ከልጆና ከልጅ ልጆቼ ጋር እስከጊዜውም ቢሆን ለመለያየት ፈቃደኛ የሆንክበትን ምክንያት በጥቂቱም ቢሆን ተረድቼዋለሁ:: ታውቃለህ - በእውነት ታውቃለህ - አንድ ቀን መጥተው እንደሚገናኙህ አታውቅም?

"ያለ አንዳች ጥርጥር" አልኩ::

የኢልዶን መገለጥ አስደነቀኝ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ትክክል ነበር:: የራሴን ልጆች ሳጠምቃቸውና ባለቤቴም ስትጠመቅ ቆሜ የመመልከት ዕድል ነበረኝ:: እምነታቸውም እውነተኛ የሆነ እምነት እንደሆነም አውቃለሁ:: በእምነት አንድ ቀን የመንግስተ ሰማይ ነዋሪዎች እንደሚሆኑ አውቃለሁ:: በመንግስተ ሰማይ በነበርኩበት ጊዜ ከእነርሱ የመለየቴ ጉዳይ በፍጹም አላሳሰበኝም:: በመንግስተ ሰማይ ያሉ ሰዎች

በቀላሉ አገላለጽ በዚያ ስለሌሉ ሰዎች ግንዛቤ የላቸውም:: የሚያውቁት ነገር ማን እንደሚመጣ ነው::

ዛሬ እንኳን ቢሆን፤ በእውነት እናገራለሁ በመንግስተ ሰማይ ቀርቼ ቢሆን እያልኩ እመኛለሁ፤ ይሁን እንጂ የመጨረሻዋ ቀኔ ገና አልመጣችም:: መንግስተ ሰማይን ለቅቄ ከወጣሁ በኋላ፤ ሁለት ሳምንት በቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ እንደምቆይ፣ በሆስፒታል አንድ ዓመት እንደምተኛና ሰላሣ አራት የቀዶ ጥገና ህክምና እንደሚደረግልኝ ባውቅ ኖሮ በርግጥ በበለጠ በሁኔታው አዝኜ ልቤ በወደቀ ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ የእኔ ምርጫ አልነበረም፤ እናም በአንድ የጸሎት ድምጽ እንደገና ተመለስኩ፣ በሰዎች እግር ወደሚፈጭ የደቀቀ መስተዋት ድምጽ፣ ደግሞም በአደጋ ምክንያት ከተጨፈላለቁ መኪናዎች ውስጥ ሰዎችን የሚያወጣው ጀው ኦፍ ላይፍ (ሕይወት አድን መሳሪያ) በተባለው መሣሪያ አማካይነት በረቀቀ ጥበብ ከመኪናዋ ውስጥ ወጣሁ::

አንድ ጥያቄ ደጋግሞ ይረብሸኛል፤ "ለምን? " የሚመጣው ብዙ መልክ ይዞ ነው::

በመኪና አደጋ የሞትኩት ለምንድን ነው?

ወደ መንግስተ ሰማይ ለመሄድ የተለየ ዕድል ያገኘሁት ለምንድን ነው?

እንደገና ወደ ምድር ለመመለስና መንግስተ ሰማይን በጥቂቱ (ውልብታ ብቻ) እንዳይ የሆነው ለምንድን ነው?



በሆስፒታሉ ውስጥ እንደገና ከመሞት በጥቂቱ ያመለጥኩት ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር፣ ከጥር 18 ቀን 1989 አደጋ ጀምሮ በማያቋርጥ የህመም ስቃይ ውስጥ እንዳልፍ ለምን ፈቀደ?

አጭሩ መልስ፤ "እኔ አላውቅም" የሚል ነው:: እንደዚያም ሆኖ ለምን? የምትለዋ አንዲት ቃል የሰው ልጅ የተሟላ ጥያቄ ሆና ትቀጥላለች:: በተፈጥሯችን ነገሮችን የማወቅ ከፍተኛ ጉጉት አለን:: ማወቅ እንፈልጋለን::

ከእነዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላ፤ አሁንም ቢሆን የሆነውን ነገር አገናዝቤ ለመመልከት ለእኔ ቀላል አይደለም:: ብዙ ጊዜ ይህንን ታሪኬን ራሴ ልጽፈው ሞክሬአለሁ፤ ነገር ግን አልቻልኩም:: ስለዚህም ነው በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት እንዲረዳኝ ወዳጄን ሲሲል ሙርፊን የጠየቅኩት - እንደ እኔማ ቢሆን፤ ይህ መጽሐፍ ጭራሹን ባልተጻፈ ነበር:: ድርጊቶቹን ሁሉ እንደገና ማስታወስ መሞከሩ የሚያስከትለው ስነልቡናዊ ጉዳት አስቸጋሪ ነው:: ከዚህ አስቸጋሪ ስቃይ በመጨረሻው መትረፍ የሚቻለው ከአንድ ሌላ ሰው ጋር በትክክል አብሮ በመጻፍ መስራት ሲቻል ብቻ ነው::

አሁንም ቢሆን እነዚህ ነገሮች ለምን እንደተከሰቱ የማውቀው ነገር የለም::

በሕይወቴ የጨለማ ጊዜያቶች ሁሉ እግዚአብሔር አብሮኝ እንደሆነ አውቃለሁ::

ለምን? እያልኩ ከምጠይቃቸው ጥያቄዎች ባሻገር፤ ሌሎችም ጥያቄዎች አሉ:: እነዚህ ጥያቄዎች በጥልቀት አሰላስላቸው ዘንድ በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ አስባለሁ::

እግዚአብሔር እውነተኛ የሆነ የስቃይ ስሜት ምን እንደሆነ እውቅ ዘንድ የፈለገው፤ የሌሎችን ስቃይ መገንዘብ እንድችል ፈልጎ ይሆን?

እግዚአብሔር መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነች እንዳውቅ ፈልጎስ ይሆን?

ከሞቴና ረዥም ጊዜ ከወሰደው የማገገም ሂደት፤ እግዚአብሔር እማር ዘንድ የፈለገው ነገር ምንድን ነው?

የእኔ የሕይወት ልምምድ ለሌሎች ከፍ ባለ ደረጃ ጥቅም ሊሰጥ የሚችለው እንዴት ነው?

ከእነዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላ፤ ከእነዚህ ጥያቄዎችም ለብዙዎቹ መልስ የለኝም:: በጣም ጥቂት ነገሮችን ልማር ችያለሁ፤ እግዚአብሔር በምድር ላይ እንድቆይ የፈለገበት ምክንያት እንዳለው ልገነዘብ ችያለሁ፤ ምናልባትም የእርሱን ምክንያቶች ላላውቃቸው እችላለሁ፤ ደግሞም እኮ እግዚአብሔር ምክንያቶቹን ለእኔ የመግለጽ ግዴታ የለበትም::

ምንም እንኳን ለብዙዎቹ ጥያቄዎቼ መልስ ባይኖረኝም፤ ሰላም አለኝ:: እግዚአብሔር እንድቆይ በፈለገበት ሥፍራ ላይ እንዳለሁ አውቃለሁ:: እግዚአብሔር የሰጠኝን ሥራ በመሥራት ላይ እንደሆንኩም አውቃለሁ::

በዮሐንስ ወንጌል ላይ በሰፈረው ታሪክ ሁል ጊዜ እጽናናለሁ:: ዓይነ ሥውር ሆኖ የተወለደ ሰው ኢየሱስን አገኘውና ተፈወሰ:: ከዚያ



በኋላ፤ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ዙሪያ ገባውን ሮጠ:: ይሁን እንጂ የዚህ ሰው ፈውስ ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ለማነሳሳት ይፈልጉ የነበሩትን የጊዜውን የሃይማኖት መሪዎች አላስደሰታቸውም:: አስቀድሞ ዕውር የነበረውን አስጠርተው በመጠየቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኛ ሰው እንደሆነ እንዲያምን ሊያስገድዱት ሞከሩ:: በሃሰት እንዲመሰክርበት ማለት ነው::

ሰውዬው በማስተዋል፤ "ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም፤ ዓይነስውር እንደነበርኩ፤ አሁን እንደማይ ይህንን አንድ ነገር አውቃለሁ" ሲል መለሰላቸው (ዮሐ 9፥25):: እንደዚሁም ሁሉ አንዳንዶች ምስክርነቴን ላያምኑት ይችላሉ፤ ምናልባትም ባጋጠመኝ ከባድ አደጋ ጊዜ ውስጥ የተፈጠረ የሆነ ዓይነት ምኞታዊ መሻት እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። የሕይወት ልምምዴን አምነው እንዲቀበሉ አልከራከራቸውም::

በእኔ ላይ ስለሆነው ነገር አውቃለሁ:: መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነች እምነት ላለን ለእኛ፤ ምንም አይነት የማስረጃ ጋጋታ አያስፈልገንም:: በሕይወት የተለማመድኩት ምን እንደሆነ አውቃለሁ::

እግዚአብሔር በመንግስተ ሰማይ ዘላዓለማዊ ሕይወት ምን እንደሆነ ጥቂት ማስገንዘቢያ (ጥቆማ) እንደሰጠኝ አምናለሁ::

እንዲሁም ደግሞ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት አሁን በምድር በሕይወት ያለሁበት ከፊል ምክንያት ሰዎች ለእኔ በመጸለያቸው እንደሆነ አምናለሁ:: ዲክ ዋንሪከር ወደ ሕይወት ተመልሼ እንድመጣና ያለ አንጎል ጉዳት እንድኖር ጸልዮልኛል:: ዴቪድ ጀንቲሊስና ሌሎችም በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ወደ መንግስተ ሰማይ መልሶ እንዳይወስደኝ ጸልየዋል::

እነሆ አሁን በዚህ አለሁ፤ በሕይወትም አለሁ፣ እናም ምክንያቱ ደግሞ እግዚአብሔር በሕይወቴ ሊያደርገው ያለው ዓላማው ገና ባለመፈጸሙ ነው:: እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ያለውን ጉዳይ ሲጨርስ መሆን ወደምናፍቅበት ሥፍራ እመለሳለሁ:: በመንግስተ ሰማይ ስፍራ ተዘጋጅቶልኛል፤ እናም አንድ ቀን ለዘለቄታው ተመልሼ እሄዳለሁ::

ከእናንተም ጋር በዚያ እንድንተያይ እጸልያለሁ::